« ደህና ፡ ነኝ » ስል ፡ ጻፍኩለት ።

« ጉድ ! » አለና ፡ ራሱን ፡ በፈገግታ ፡ ነቀነቀ ። በማግሥቱ ፡ ወደሌላ ፡ ክፍል ፡ እንድዛወር፡ ተደረገ ። ዶክተሩ፡ አእምሮዬ ፡ በድንገት ፡ መመለሱን ፡ ለመረዳት ፡ አላስቸገረውም።ከፊቱ ፡ ላይ፡ አንብቦታል።ከአጠያየቄ፡ ተገንዝቦታል።

በኋላ ፡ እንደተረዳሁት ፡ የተዛወርኩበት ፡ ክፍል ፤ ወደ በሩ ፡ ተጠግቶ ፡ የሚገኘው ፡ ሦስተኛው ፡ ደረጃ ፡ ነበር። ድነው ፡ ለመውጣት ፡ የሚጠባበቁት ፡ ወይም ፡ ተስፋ ፡ ያላቸው ፡ የገመምተኞች ፡ ክፍል ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የበሽተኞቹ ምድብ ፡ በሦስት ፡ ይከፈላል ። ከታች ፡ ከደቡብ ፡ ዘርፍ ፡ በኩል ፤ የመዳን ፡ ተስፋ ፡ የሌላቸው ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ለመለየት ፡ የማይችሉ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ የአእምሮ፡ በሽተኞች ፡ ይገኛሉ ። በሁለተኛው ፡ ደረጃ ፤ ለመዳን ፡ ተስፋ ፡ ያላቸው ፤ ግን ፡ ሕክምናው ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚወስድ ፡ በሽተኞች ፡ አሉ ። በሦስተኛው ፡ ደረጃ ፡ ገመምተኞች ፡ ናቸው ። በጽዳትም ፤ በጸጥታም ፤ በሁናቴም ፡ ይህ ፡ እንደሌሎች ፡ ሆስፒታሎች ፡ አንደኛ ፡ ማዕረግ ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ። ግቢው ግን ፡ አንድ ፡ ነው ።

ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ዶክተሩ ፡ ሕክምና ፡ ክፍል ፡ ተጠራሁ ። «አሁን ፡ ደህና ፡ ነህ ? ተሽሎህ ፡ የለም ፡ እንዴ ?» እያለ ፡ በማጽናናት ፡ እንደማይከረፍን ፡ የመሰለውን ፡ የኤሌትሪክ ፡ መተኮሻ ፡ በሁለቱ ፡



ጆሮ ፡ ግንዴ ፡ ሰካው ። ትኩሳቱ ፡ ከአንድ ፡ ሴኮንድ ፡ የበለጠ ፡ አይወስድም ። በዚያች ፡ አንድ ፡ ሴኮንድ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ በሽተኛ ፡ አልፎት ፡ የሚመለሰው ፡ ሥቃይ ፡ ሊገለጽ ፡ አይቻልም ። በዚያ ፡ በሚፍለቀለቀው ፡ የገሃነም ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ተዘፍቆ ፡ መውጣት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አምፖል ፡ ስንለውጥ ፡ የሚሰማን ፡ «የኤሌትሪክ ፡ ሾክ» በዚያ ፡ ግምት ፡ የእናት ፡ ቁንጥጫ ፡ ነው ። ይህ ፡ በቀጥታ ፡ የሚተኩሰው ፡ አንጎልን ፡ ነው ።

ዶክተሩ፡ መተኮሻውን ፡ ከጭንቅላቴ ፡ ላይ ፡ አውልቆልኝ፡ ከወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተዘርሬ፡ ትንሽ፡ ከተነፈስኩ፡ በኋላ፡ አሁንም ፡ ወረቀት ፡ አንስቼ ፡ « ሌላ ፡ የኤሌትሪክ ፡ ሕክምና ፡ እንዲደረግልኝ ፡ ፈጽሞ ፡ አልፈልግም ። ደህና ፡ መሆኔ ፡ በትክክል ፡ ይሰማኛል ። ይታወቀኛል ። በዚህ ፡ የምሠቃይበት ፡ ምክንያት ፡ ከቶ ፡ የለም ፡ » ብዬ ፡ ጻፍኩና ፡ ሰጠሁት ። ተተረጎመለት ። ትክ ፡ ብሎ ፡ ከፉኛ ፡ አስተዋለኝ ።

በኤሌትሪክ ፡ መተኮሱን ፡ ስቃወም ፡ እኔ ፡ የመጀመሪያው ፡ በሽተኛ ፡ አይደለሁም ። ወደዚያ ፡ ክፍል ፡ በተጠራ ፡ ቁጥር ፤ የማያለቅስ ፤ የማይወራጭ ፤ የማይጮህ ፡ በሽተኛ ፡ የለም ። ዶክተሩ ፡ ወይም ፡ ረዳት ፡ አስተዳዳሪው፡ ሲያልፉ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ከጉልበቱ ፡ ወድቀው ፡ « እንዲያው ፡ ምን ፡ አጠፋሁ !» እያሉ ፡ የሚለምኑ ፡ ሞልተዋል። አንዳንዶቹም ፡ ሥቃዩ ፡ እንደፈረማ ፡ በአንጎላቸው ፡

ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚያወሩት ፡ ስለርሱ ፡
ነው ። ከመኝታቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፤ መተኮሻው ፡ የተሰ
ካባቸው ፡ ይመስል ፡ ጀሮ ፡ ግንዳቸውን ፡ ይዘው ፡ ያቃስ
ታሉ ። አውቆ ፡ አበዶቹ ፡ ደግሞ ፡ አንዴ ፡ ሲያቀምሱዋ
ቸው ፡ ይናዘዛሉ ፡ ይባላል ። የኤሌትሪኩ ፡ ትኩሳት ፡ በሽ
ታቸውን ፡ ያባሰባቸውም ፡ አይጠፉም ። የለመነው ፤ ያለ
ቀሰው ፤ የተንገበገበው ፡ ሁሉ ፡ አይቀርለትም ፡ ነበር ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አጠያየቄ ፡ ልመና ፡
ሳይሆን ፡ በጥሞና ፡ የቀረበ ፡ ምክርና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡
ጭምር ፡ መሆኑን ፡ ዶክተሩ ፡ በመገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ጤን
ነቴን ፡ በማስተዋሉ ፡ ይሁን ፡ እንጃ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኤ
ሌትሪኩ ፡ ትኩሳት ፡ አልነካኝም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ከመ
ኝታ ፡ ክፍላችን ፡ ተሰ ብስበን ፡ ስንጫወት ፡ አንዱ ፡ በሽ
ተኛ ፡ መጥቶ ፡ ሰው ፡ ይፈልግሃል ፡ አለኝ ። በጥያቄ ፡
መልክ ፡ ራሴን ፡ ነቀነቅሁ ። «አንዲት ፡ ሴትዮ ፡ ናቸው ፡»
አለ ። አ ! ሴት ! ሴት ? የምን ፡ ሴት ? የማን ፡ ሴትዮ ?
በእጇ ፡ ይዝው ፡ የነበረውን ፡ የካርታ ፡ ወረቀት ፡ ከአል
ጋው ፡ ላይ ፡ ዘረገፍኩና ፡ ወጣሁ ። ያስጠራችኝ ፡
ሴት — ቀን ፡ ቆጠራውን ፡ ረሳሁት ፡ እንጂ — አንድ ፡
ጊዜ ፡ ቤቱን ፡ ዘግታ ፡ ጥላኝ ፡ የሔደችው ፡ ባለቤቴ ፡ ነበ
ረች ። የእንጀራ ፡ ሳሕን ፡ እንደታቀፈች ፡ ወደኔ ፡ ቀረበ



ችና ፤ « እንደምን ፡ ሰነበትክ ? ሐኪሙ ፡ በጣም ፡ ተሽ
ሎታል ፡ አለኝ ። አልተገናኘንም ፡ እንጅ ፡ ሁል ፡ ጊዜኮ ፡
እመጣለሁ » አለች ፡ አንገቷን ፡ ደፋ ፡ አድርጋ፡ በጣም፡
በለሰለሰ ፡ አንደበት ። «ታዲያ ፡ ምን ፡ ይጠበስ ?» አልኩ፡
በሆዴ ። ቁጣ ፡ ሳይሆን ፡ ስሜቴ ፡ የኃፍረት ፡ ነበር ።
ለምን ፡ መጣች ? ሕሊናዬን ፡ ለመኰርኰር ፡ ነው ? ለብዙ
ጊዜ ፡ ያህል ፡ እንደዚሁ ፡ ቆምን ። በሙሉ ፡ ዓይን ፡ ለዓ
ይን ፡ ስንኳ ፡ አልተያየንም።በመጨረሻ ፡ ሰሐኑን፡ ሰጥታ፡
ተሰናብታኝ ፡ ሔደች ። ሳሕኑን ፡ ይዠ ፡ ወደክፍሌ ፡
ስገባ ፡ ሰሞኑን ፡ ሲከነክነኝ ፡ የሰነበተው ፡ እንቆቅልሽ ፡
ተፈታልኝ ። ከሦስት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፤ ከአራት ፡
ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የቤት ፡ ምግብ ፡ በሳሕን ፡ ይመጣል
ኛል ። ከየት ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ዘበ
ኛው ፡ ስሜን ፡ ይጠራና ፡ ይሰጠኛል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡
የቤት ፡ ምግብ ፡ የሚመጣላቸው ፡ በሽተኞች ፡ በጣም ፡
ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በዚያ ፡ መናኛ ፡ እንጀራና ፡ ዝብጥብጥ
ወጥ ፡ መካከል ፤ ዘወትርም ፡ ባይሆን፡ ክሽን፡ ያለች፡ ወጥ ፤
የነጭ ፡ ጤፍ ፡ እንጀራ ፡ ምግብ ፡ በሳሕን ፡ የሚደርሰው ፡
በሽተኛ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የሚታየው ።
እኔም ፡ በዚሁ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አፍርቻበት ፡ ነበር ።
ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ማን ፡ እንደሚልክልኝ ፡ አላ
ውቅም ፡ ነበር ። ዘበኛውንም ፡ አልጠየቅሁትም ።
ማንበብ ፡ አይችልም ። « ለካ ፡ እሷ ፡ ናት ! » ፡ አልኩ ፡

በሆዴ ። የሚደርሰኝ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ሳሕን ፡ ነበር ። አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

በማልስቱ ፡ እንደዚሁ ፡ መ ጣችና ፡ አስጠራችኝ ። ጤንነቴን ፡ ጠየቀችኝ ። ከዚያም ፡ ሳንነጋገር ፡ እንደዚሁ፡ ቆመን ፡ ቆየን ። በመጨረሻም ፡ ያመጣችውን ፡ ሳሕን ፡ ሰጥታኝ ፡ የሰነበተውን ፡ ይዛ ፡ ሔደች ። ጉብኝቷ ፡ በዚህ፡ ሁናቴ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተደጋገመ ፡ ቀጠለ ።

ትመጣለች - - እጠራለሁ -´- እወጣለሁ - - «ደህና፡ ሰነበትክ ? » ስትል ፡ ሰላምታ ፡ ታቀርብልኛለች ። ስለደ ህንነቴ ፡ ደንታ ፡ እንደሌለኝ ፡ ትከሻዬን ፡ ነቅነቅ ፡ አደር ጋለሁ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የጐሪጥ ፡ እየተያየን ፡ እንቆማ ለን ። ሳሕኑን ፡ ሰጥታኝ ፡ ባዶውን ፡ ሳሕን ፡ ይዛ ፡ ትሔዳ ለች ። በመካከላችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የማያስተያይ ፡ አንድ ዓይነት ፡ መጋረጃ ፡ ነበር ። በኔ ፡ በኩል ፡ አጉል ፡ መግደርደርና ፡ ኀፍረት ፡ ጭምር ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አስመርሬ ፡ ያባረርኳት ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ባለውለ ተኛ ፡ አሁን ፡ የኔ ፡ አስታማሚ ፡ መሆኗ ፡ የሚያኮራ ፡ ወይም ፡ የሚያስደስት ፡ ስሜት ፡ አልሰጠኝም። ንዴትም ፤ ፀፀትም ፡ አለበት ። እርስዋ ፡ ግን ፡ አንገቷን፡ ማቀርቀርና፡ መሽኮርመም ፡ ተፈጥሮዋ ፡ ነው ።

ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የጐብኝቷን ፡ ቀን በናፍቆት፡ መጠባበቅ፡ ጀመርኩ። አንድ፡ ጊዜ፡ እስከ፡ አም ስት፡ቀን፡ ሳትመጣ፡ ቀረችና፡ ሰውነቴ፡ ሲታወክና፡ ሲጨነቅ፡



ሰነበተ ። « ምን ፡ ነካት ? » « ተሰፋ ፡ ቆርጣ ፡ ተወችኝ?» « ሰላምታ ፡ ስንኳ ፡ ስነፍጋት ! » « እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ማን ፡ አለኝ » እያልኩ ፡ አሰላስልኩ ።

በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ይፈልግሃል ፡ ስባል ፡ ልቤ ፡ ዳንኪራ ፡ እየመታ ፡ በጥድፊያ፡ ወጣሁ ። አሁንም፡ ሰላምታ ፡ አልሰጠኋትም ። ግን ፡ ፊቴ ፡ ላይ ፡ ከበፊቱ ፡ የተለየ ፡ ፈገግታ ፡ እንዳለበት ፡ ይታወቀኝ ፡ ነበር ።

«ሳልመጣ ፡ የሰነበትኩት ፡ እንፍልዊንዛ ፡ አሞኝ ፡ ነው » አለች ፡ ይቅርታ ፡ በመጠየቅ ፡ ዓይነት ። በእርግ ጥም ፡ ሰውነቷ ፡ ገርጥቷል ። እኔን ! ትክ ፡ ብዬ ፡ ተመለከ ትኳት ። ዓይኗን ፡ ድንገት ፡ ቀና ፡ ስታደርግ ፡ ዓይንና ፡ ዓይን ፡ ተጋጨን ። ፈገግ ፡ አልኩ ። ፈገግ ፡ አለች ። ተፋ ጠን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆየን ። ከዚያም ፡ ከኪሴ ፡ ወረቀት ፡ አወጣሁና ፡ «ልጆቹስ ፡ ደህና፡ ናቸው ?» ብዬ፡ ጠየቅኋት። ከኔ ፡ በኩል ፡ መጋረጃው ፡ ሲገለጥ ፡ ገና ፡ የመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። በአወንታ ፡ ራሷን ፡ አወዛወዘች ። ዕንባ— የደስታ ፡ ዕንባ — ሲተናነቃት ፡ ከጉሮሮዋ ፡ ላይ ፡ ያስታ ውቃል። ስንሰነባበትም ፡ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ የእጅ ፡ ሰላ ምታ ፡ ተሰጣጣን ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ አዲስ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ያዘው ፡ ሰው ፡ ሲያቁነጠንጠኝ ፡ ዋለ ። « ቆንጆ ፡ ነች ፡ እኮ ! ለኔ ፡ ያላት ፡ ፍቅር ፡ ከዓይኗ ፡ ላይ ፡ በገሐድ ፡ ይነ በብ ፡ የለም ፡ እንዴ !» እላለሁ ፡ ብቻዬን ።

በሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ ስትመጣ ፡ ላስጐብኝሽ ፡ ብዬ፡ በእጀ ፡ ጋበዝኳት ። ከዚያም ፡ ኃላፊውን፡ አስፈቀድኩና ፡

በመጀመርያ ፡ ወደኛው ፡ ክፍል ፡ ወሰድኳት ። ለማስ
ጐብኘት ፡ የሚያሳፍር ፡ ክፍል ፡ አልነበረም ። ብርድ ፡
ልብሱ ፡ ባና ፡ ቢሆንም ፤ የአልጋው ፡ ረድፍ ፡ የተስተካ
ከለ ፤ አንሶላው ፡ ነጣ ፡ ያለ ፡ ነበር።ጢት ፡ ጢት ፡ በሚገባ፡
ተነጥፎ ፡ ይውላል ። ጫጫታና ፡ ጩኸት፡ አይሰማበትም።
የዚህ ፡ ክፍል ፡ በሽተኞች ፡ አብዛኞቹ ፡ የረጉ ፡ ናቸው ።
ቢበዛም ፡ ጐብኝን ፡ የሚያስቸግሩት ፡ ሲጋራ ፡ ስጠን ፡
እያሉ ፡ ነው ። የኔን ፡ መኝታ ፡ በእጀ ፡ አመለከትኳት ።
ከወለሉ ፡ መካከል ፡ ቆመችና ፡ ዙሪያውን ፡ በጥሞና ፡ካስ
ተዋለች ፡ በኋላ ፡ « ደህና ፡ ነው » አለች ።

ቀጥዬ ፡ ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ ወሰድኳት ። ዕብ
ደት ፡ የሚያስቅ ፡ ቢሆን ፡ ከሌሎቹ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያስ
ቀው ፡ ይህ ፡ ክፍል ፡ ነው ። በሰላሳ ፡ ዓመቱ ፡ አእምሮው፡
እንደአምስት ፡ ዓመት ፡ ሕፃን ፡ የሚያስበው ፡ በሽተኛ ፡
አለ ። እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልንፏቀቅ ፡ ይላል ። እንደሕፃን ፡
ይኮላተፋል ። «ዕብድ» ፡ እያለ ፡ የሚያሽሟጥጠው ፤ የሚ
ሸልለው ፤ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ጠባይና ፡ አድ
ራጎት ፡ ይታያል ። በዚህ ፡ ክፍል ፡ ያሉት ፡ በሽተኞች ፡
ልብስ ፡ የሚለብሱ ፡ ቢሆንም ፤ መኝታ ፡ ቤቱ ፡ ከሦስተ
ኛው ፡ ደረጃ ፡ የቆሸሸ ፤ አልጋው፡ ግማሹ ፡ ተነጥፎ ፡
ግማሹ ፡ የተዝረከረከ ፡ ነው ።

ይህንን ፡ አልፈን ፡ ከአንደኛው ፡ ደረጃ ፡ ስንደርስ ፡
ከበራፉ ፡ ላይ ፡ አቆምኳት ። በስተምዕራብ ፡ የሚገኘው ፡



ክፍል ፡ አእምሮዋቸው ፡ ተቃውሶ ፡ ወንጀል ፡ የፈጸሙ ፤
ወይም ፡ አሰቃቂ ፡ ወንጀል ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ አእምሮ
ዋቸው ፡ የተቃወሰ ፡ በሽተኞች ፡ የሚገኙበት ፡ ነው ።
ልጁን ፡ አርዶ ፡ የቀበረው ፤ የደመኛውን ፡ ደም፡ የጠጣው፤
ሕፃን ፡ የሚያሳርደው ፡ ቃልቻ ፤ ዲኮሚንት ፡ የቀደደው ፡
ሠራተኛ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ይገኛሉ ። የክ
ፍሉ ፡ ጽዳት ፡ ከሁለቱ ፡ የባሰ ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡
ሌላ ፡ የተለየ ፡ መልክ ፡ አለበት ። የዚህ ፡ ክፍል ፡ በሽተ
ኞች ፡ ሁሉ ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ይታሠራሉ ። ገና ፡ ከውጭ
ሆኖ ፡ እግር ፡ ብረቱ ፡ ሲንጨላጨል ፡ ይሰማል ። አንገ
ቷን ፡ ብቅ ፡ አድርጋ ፡ ጥቂት ፡ እንደተመለከተች ፡ መለስ
ኳት ። አደገኛ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ይባላል ።

የመጨረሻውን ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ አላስጐበኘኋትም ።
የመዳን፡ ተስፋ፡ የሌላቸው፡ በሽተኞች፡ የሚገኙበት፡የዚህ፡
ክፍል፡ ትርኢት፡ ስንኳን፡ ሴት፡ ልጅን፡ ይቅርና ፡ ኮስታራ፡
ወንድን ፡ ያስቅቃል ። ሁሉ ፡ ከእናቱ ፡ ሆድ ፡ እንደወጣ፡
ዕርቃኑ ፡ ሥጋውን ፡ ነው ። አንዱ ፡ አልጋውን ፡ ትቶ ፡ ከአ
ልጋው ፡ ሥር ፡ ይንከባለላል ። ሌላው ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡
ኩርትም ፡ ብሎ ፡ ይቀመጣል ። እንደወጋግራ ፡ ቀኑን ፡
ሙሉ ፡ ከአንድ፡ ሥፍራ፡ ተገትሮ ፡ የሚውለው፡ በሽተኛ ፡
አለ ። ከውጭ ፡ በጀርባ ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ራቁታቸ
ውን ፡ ከአፈሩ ፡ ሲንከባለሉ ፡ የሚታዩት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ከነርሱ ፡ መካከል ፡ የከረመ ፡ ጤነኛ ፡ ባሙቱ ፡ ራሱ ፡ ታሞ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

እኔም ፡ በተሻለ ፡ አእምሮ ፡ ይህንን ፡ ክፍል ፡ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ስመለከት ፡ ክፉኛ ፡ ሳልደነግጥ ፡ አልቀረሁም ፡ ነበር ። ሰው ፡ መሆንን ፡ ያስጠላል ። ክቡሩ ፡ ሰው፡ እንደዚህ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ?

በፊቷ ፡ እንደተረዳሁት፡ ከጉብኝቱ፡ በተለይ፡ ልቧን፡ የነካው ፡ የሴቶች ፡ ክፍል ፡ ይመስለኛል ። ሴት ፡ በመሆኗ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ይህ ፡ ክፍል ፡ በተለይ ፡ ኀዘን ፡ የሰፈነበት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ « ሸዋዬ ፡ አንቺ ፡ ሸዋዬ ? » እያለች ፡ እንደቅዠት ፡ ልጇዋን ፡ ስትጣራ ፡ የምትኖረው፡ በሽተኛ ፡ የማንንም ፡ ልብ ፡ ትነካለች ።

አንዷ ፡ በሽተኛ ፡ « ሻሼን ፡ ነጠቁኝ , እኮ » ፡ ብላ ፡ እንደዋዛ ፡ ብታዋያት ፡ ጸጉሯን ፡ ያሰረችበትን ፡ ሻሽ ፡ ፈትታ ፡ ሰጠቻት ። ጉብኝቱ ፡ ሲጨረስ ፡ እንደማቃሠት ፡ ያህል ፡ በከባዱ ፡ ተነፈሰች ። ጉብኝቱ ፡ ስሜቷን ፡ ክፉኛ ፡ አሰቃይቶት ፡ ነበር ።

ከዚያ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ የኔንም ፡ ክፍል ፡ ገብታ ፡ አረገጠችም ። ከውጭ ፡ ሆና ፡ ታስጠራኛለች ። ከዚያም ፡ በግቢው ፤ ወደታችኛው ፡ ሠፈር ፡ ሳንወርድ ፡ ጥቂት ፡ እንንሸራሸራለን ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኔ ፡ ጤንነት ፡ ለፈተና ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። ወደሦስተኛው ፡ ደረጃ ፡ የተዛወሩ ፡ የአእምሮ፡ በሽ



ተኞች ፡ ሁሉ ፡ የዕለት ፡ እንቅስቃሴያቸው ፤ አድራጎታቸው ፤ ንግግራቸው ፤ የፊት ፡ ገለጣቸው ፡ የቅርብ ፡ ቁጥጥር ፡ ይደረግበታል ። ዘበኞቹ ፤ ቤት ፡ ጠራጊዎቹ ፤ አልጋ ፡ አንጣፊዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ለዋናው ፡ ዶክተር ፡ በእያንዳንዱ ፡ በሽተኛ ፡ ላይ ፡ ሪፖርት ፡ ያቀርባሉ ። ከዚህም ፡ በተቀር ፡ በተለይ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የተመደቡት ፡ የሶሺያል ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ሠራተኞች — በሆስፒታሉ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ አንዲት ፡ ሴትና ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ናቸው — ዋናው ፡ ተግባራቸው ፡ ገመምተኛው ፡ ወደማኅበራዊ፡ ኑሮ ፡ እንደገና ፡ ለመግባት፡ የሚያስችለውን፡ ምክር፡ መስጠት፡ ሲሆን ፤ በሌላው፡ በኩል፡ ደግሞ፡ ከሐኪም፡ ቤቱ፡ ለመውጣት ፡ የበቃ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፡ ይመረምራሉ ። ከውጭ ፡ ዘመድ ፤ አዝማድ ፤ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ይጠይቃሉ ። ከውስጥ ፡ በሽተኛውን ፡ እንደዋዛ ፡ እያጫወቱ ፡ ሁናቴውን ፡ ይመዘግባሉ ። አንዳንዱ ፡ በሽተኛ ፤ ከእነጋገር ፡ እንዳይስት ፡ በመጠንቀቅ ፡ ዝምታ ፡ አብዝቶ ፡ ፈተናውን ፡ ይወድቃል ። ሌላው ፡ ጮሌነቱን ፡ ለማሳየት ፡ ሲቀባጥር ፡ አለመዳኑን ፡ ይገልጣል ። በሦስተኛውም ፡ ደረጃ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ የቆዩ ፡ በሽተኞች ፡ አሉ ። አንዱ ፡ ሊያመልጥ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው፡ በአንዲት ፡ ስሕተት፡ ይወድቃል። ሌላው ፡ እየቆየ ፡ በሽታው ፡ ያገረሽበትና፡ ወደሁለተኛው፡ ደረጃ ፡ የሚዛወር ፡ አለ ። ብዙዎቹ ፡ በሽተኞች ፡ የሚታይባቸው ፡ አንዱ ፡ ትልቅ ፡ ጉድለት ፡ የውጪኛውን ፡ ኅብረ

ሰብ ፡ መፍራትና ፡ በራስ ፡ እምነት፡ ማጣት ፡ መሆኑ፡ ይነገራል ። እኔ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድዳ ፡ ብሆን፡ ከባለቤቴ፡ ጋር፡ እንደገና ፡ ከተገናኘሁ ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ እምነትና ፡ ተስፋም ፡ ይሰማኝ ፡ ስለነበር ፡ ከደንበኛው ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ አላሳየሁም ። በየቀኑ ፡ እምነቴ ፡ እየጠነከረ ፤ የርሷም ፡ አስተያየትና ፡ ሰላምታ ፤ ከፊቷም ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ ፍቅር ፡ እያጽናናኝ ፡ ሔደ ። ከጓደኞቼ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ባልነጋገር ፡ ዲዳነቴ ፡ ታውቆ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

ግማሹን ፡ ጊዜ ፡ ስለማላስታውሰው ፡ እንደነገሩኝ ፡ በአማኑኤል ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከፈጀሁ ፡ በኋላ፡ አእምሮዬ፡ ደህና ፡ ስለተመለሰ ፤ ቢያስፈልግ ፡ እየተመላለስኩ ፡ ልታከም ፡ መውጣት ፡ የምችል ፡ መሆኑን ፡ ሐኪሙ ፡ ፈቀደ ። ባለቤቴ ፡ ዜናውን ፡ እንደትልቅ ፡ ምሥራች ፡ ነገረችኝ ። በእርግጥም ፡ ትልቅ ፡ ምሥራች ፡ ነበር ። ፒያሳ ፡ እንዴት፡ ሆኖ ፡ ይሆን ? አዲስ ፡ ከተማስ ? ተሻሽሏል ? ከማይጮህ ፤ በሥንሥለት ፡ ከማይታሠር ፤ ልብሱን ፡ በሚገባ ፡ ከሚለብስ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ መዋሉን ፡ ስንኳ ፡ አያሀለውም ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ተሠቀቅሁ ። ሰውስ ፡ እንዴት ፡ ይቀበለኛ ፡ ይሆን ? «ከአማኑኤል ፡ በቅርቡ ፡ የወጣው ! » እያለ ? የሰውን ፡ አፍ ፡ ገና ፡ በመፍራት ፡ አማኑኤል ፡ ተዘግቼ ፡ አልቀርም ።



አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ባለቤቴ ፡ የአባቷን ፡ አውቶሞቢል ፡ ከነሹፌሩ ፡ ተውሳ ፡ ልታወጣኝ ፡ መጣች ።

መጻሕፍቶቼን ፡ —ወደመጨረሻ፡ ጊዜ፡ግድም ፡ ማንበብ፡ ጀምሬ ፡ ነበር ፡ —— ልብሶቼን ፤ የምግብ ፡ ማመላለሻ ፡ ዕቃዎችን ፡ ሳሰናዳ ፡ የክፍል ፡ ጓደኞቼ ፡ ዙሪያውን ከበው ፡ ተመለከቱኝ ።

«አየለ ! ጥለሽን ፡ መሔድሽ ፡ ነዋ ! » አለ ፡ አንደኛው ። አማኑኤል ፡ ከገባ ፡ አምስት ፡ ዓመቱ ፡ ነበር ። ግን፡ ገና፡ አልተሻለውም ። በርሱ፡ ቤት ፡ ሁሉ፡ «አንቺ» ነው ።

«ምን ፡ ያስቀባጥርሃል ! ከዚህ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ሲላዝን ፡ ይኖራላ ! » ሲል ፡ ሌላው ፡ ተቆጣው ።

« እኔምኮ ፡ ሳምንት ፡ ልወጣ ፡ ነኝ ! » አለ ፡ ከሽኔ ፡ የተባለው ፡ ወጣት ። ሁልጊዜ ፡ ሳምንት ፡ እወጣለሁ ፡ እንዳለ ፡ ነው ። በጣም ፡ ያሳዝነኛል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቻውን ፡ እየተቀመጠ ፡ ሲያለቅስ ፡ ዓይቸዋለሁ ። አማኑኤል ፡ የገባው ፡ ገና ፡ በልጅነቱ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጐብኚ ፡ መጥተው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ሲጠይቁን ፡ በአመላለሱ ፡ ተደስተው ፡ ሲያመሰግኑት ፡ «አለቻ ! » አለ ፤ « ምን ? » ብለው ፡ እንደገና ፡ ቢጠይቁት ፡ ጭንቅላቱን ፡ በጣቱ ፡ እየጠቆመ ፡ « ኩላሊት ! » ያለው ፡ ከሽኔ ፡ ነበር ። ሠንሠለታቸው ፡ ያልወለቀው ፡ ስንኳ ፡ ሲስቁበት ፡ ይኖራሉ ።

ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ዕቃዬን ፡ ስከውን፡ ተኰንብሶ፡ እየረዳኝ፡ «ከእነዚህ፡ ዕብዶች፡ ጋር፡ ይኖራል ፡ ሰው ፡? መጥኔ !»

ሲል ፡ እንደጤናማ ፡ ተማረረ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፤
ባለቤቴ ፡ ከበረንዳው ፡ ላይ ፡ ቆማ ፡ ትጠብቀኝ ፡ ነበር ።
የምትጠላው ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ አንዱ ፡ ከክፍላችን ፡ መማ
ባት ፡ ነው ። ዕብደት ፡ ተጋቢ ፡ ይመስል ፡ ራሴን ፡ ያመኛል
ትላለች ። በዚያ ፡ ሁሉ ፡ ወራት ፡ አልጋዬን ፡ የጐበኘ
ችው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በተረፈ ፡ ግን ፡ ተኝ
ቼም ፡ እንደሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሆና ፡ ታስጠራኛለች ።

ጓዜን ፡ ጠቅልዬ ፡ ለሹፌሩ ፡ አሸከምኩና ፤ « በሉ ፡
ደህና ፡ ሁኑ ፡ ልጆች » ብየ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኞቼን ፡ እጃቸ
ውን ፡ እየጨበጥኩ ፡ ተሰናበትኳቸው ። ከሌላው ፡ ትልቅ
ክፍል ፡ ገባሁና ፡ ከወለሉ ፡ ላይ፡ ቆሜ፡ በስንብት ፡ እጄን ፡
አወዛወዝኩላቸው ። ያስተዋለኝ ፡ ግን ፡ አልነበረም ።
ግማሹ ፡ ይጨፍራል ። ግማሹ ፡ ተኝቷል ። ግማሹ ፡ ከቦ ፡
ያወራል ። መቀባዠሬ ፡ መስሏቸው ፡ ይሆናል ።

«አየለ ! » አለኝ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያልተናገረው፡
አንዱ ፡ የክፍል ፡ ጓደኛዬ፡ «መልካም ፡ ዕድል ! እንደገና ፡
እንዳትመለስ ፡ እጸልይልሃለሁ ! ። » እጄን ፡ ሲጨብጥ ፡
በዓይኑ ፡ ዕንባ ፡ ቺፍፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

«እኔም ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ» ፡ አልኩት፡ እንደዋዛ።
ግን ፡ አነጋገሩ ፡ ልቤን ፡ ነክቶት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ የበለጠ፡
መልካም ፡ ምኞት ፡ ምን ፡ አለ ? በተለይ ፡ እንደኔ ፡ ላለው ።

አብዛኞቹ፡ የክፍል፡ «ጓደኞቼ ፡ ሊሸኙኝ ፡ እስከበረን
ዳው ፡ ድረስ ፡ ወጥተው ፡ ነበር ። ከአውቶሞቢሏ ፡ ከመማ



ባቴ ፡ በፊት ፡ ባሕር ፡ ማዶ ፡ እንደሚዘምት ፡ መንገ
ደኛ ፡ ፊቴን ፡ መለስኩና ፡ ክንዴን ፡ አወዛወዝኩላቸው ።
በአጸፋው ፡ አርገበገቡልኝ ። አውቶሞቢሉ ፡ ውስጥ ፡ ስገ
ባም፡ ስለነርሱ ፡ አሰብ፡ ጀመር። - - - ጥቂቶቹ - - የልብ - -
የቅርብ ፡ ጓደኞቼ ፡ ናቸው ። ከውጪኛው ፤ ከጤናማው ፡
ዓለም ፡ ይልቅ ፡ በዚያ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እውነተኛ ፡ ጓደ
ኞች ፡ አግኝቸአለሁ ። ለገንዘብ ፡ ሲሉ ፡ የማይጠጉ - - - -
የልባቸውን ፡ የሚገልጡ - - - - - ስለኔ ፡ መሔድ ፡ ምን ፡
ይሰማቸው ፡ ይሆን ? ግማሾቹ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ይመ
ኙልኝ ፡ ይሆናል ። ግማሾቹ ፡ የኔን ፡ ዕድል ፡ በጉጉት ፡
ይጠባበቁ ፡ ይሆናል ። በኔ ፡ መውጣት ፡ አእምሮዋቸው ፡
የሚያፈዝም፡ አይጠፋም። አዎ፡ ከኔ፡ የተሻለ፡ ጤናማ፡ አእ
ምሮ ፡ ያላቸው ፡ አሉ ። እንዲያውም፡ ከውጪኛው፡ ዓለም፡
የተሻለ ፡ ጤናማ ፡ አእምሮ፡ አላቸው። ምናልባት፡ በጣም፡
ትክክለኛው ፡ ጤናማ ፡ አእምሮዋቸው ፡ ከውጪኛው ፡
ዓለም ፡ ጋር ፡ ስላልተስተካከለ ፡ ዕብዶች ፡ ተብለዋል ።
ሌላው ፡ ይሥቅባቸዋል። እነርሱም፡ በሌላው ፡ ይሥቃሉ ፡
ያሾፉሉ - - - ።

ከሐሳቤ ፡ የነቃሁት ፤ ግቢውን ፡ ወጥተን ፡ ቀጭኗን፡
ኮረኮንች ፡ መንገድ ፡ ዘልቀን ፡ ከአዲስ ፡ ከተማው ፡ ትር
ምስ ፡ ስንገባ ፡ ነበር ። ባለቤቴ ፡ የመውጫውን ፡ ፈቃድ ፡
ለዘበኛው ፡ ስትሰጥ ፡ አላየሁም። ሰላምታ፡ ገጭ፡ አድርጎ ፡
«እሺ ፡ እመቤቴ » አለ ? - - - ደህና ፡ ሁን ፡ ብዬ ፡ መሰና

በት ፡ ይገባኝ ፡ ነበር። --- ከዚያም ፡ ዘበኛውን ፡ አፍነን ፤ በሩን፡ሰብረን፡ለማምለጥ፡የተማከርንበት፡ጊዜ፡ ታወሰኝ ---። አብዛኞቻችን ፡ አማኑኤልን፡ የምናየው ፡ እንደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ አለም ፡ በቃኝ ፡ ነበር ።

ጋሪው ፡ ይጋፋል ። ሰይቾንቶው ፡ ይባረራል ። እግረኛው ፡ ይተራመሳል ። ሹፌራችን ፡ ክላክሱን ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይነፋል ። እንጨት ፡ የተሸከመው ፡ ሰው ፤ ኩበት ፡ የተጫነው ፡ አህያ፤ በጥድፊያ ፡ የሚራመደው፤ እያዘገመ ፡ የሚጓዘው ፤ ተቀምጦ ፡ የሚለምነው ፤ ሻጩ ፤ ገዥ ፤ ደላላው ፤ ዕቃው ፤ -- ጩኸቱ ፤ እንቅስቃሴው --- እንዴ ! ፀጥታው ፡ ከአማኑኤል ፡ ምንምኮ ፡ አይሻል ! የሚል ፡ ስሜት ፡ አደረብኝ ። ከዚህ ፡ ተርመስማሽ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ስንቱ ፡ ነው ፡ ከነዚያ ፡ ጓደኞቼ ፡ የተሻለ ፡ አእምሮ፡ ያለው ? ብዬ ፡ ራሴን ፡ ጠየቅሁት ።

«አየለ ! » ስትል ፡ ባለቤቴ ፡ ጠራችኝ ፡ በሐሳብ ፡ መዋጤን ፡ አይታ ። ቀና ፡ ብየ ፡ አየኋት ። ተያየን ። ከዚያም ፡ በአባቆራ ፡ ሠፈር ፡ ከጋሪው ፡ ጋር ፡ እየተጋፋን ፡ አልፈን ፤ በዮሐንስ ፡ ዘልቀን፡ በመስፍን፡ ሐረር ፡ መንገድ፡ ወጣንና ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ ግቢ ፡ አመራን ። አፈርኩ ። ፊታቸውን ፡ እንዴት ፡ ላየው ፡ ነው ? ከቃገሩ ፡ ሁሉ ፡ ምነው ፡ የዛሬን ፡ ብታልፈኝ ፡ ስል ፡ በሆዴ ፡ ጸለይኩ ። ነገር ፡ ግን፡ እንደፈራሁት ፡ ወደ ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ አልገባንም ። ከግቢው ፡ ዳርቻ ፡ ፊቷን ፡ ወደውጭ ፡ ሰጥታ ፡ ከምትገ



ኘው ፡ ቤት ፡ ስንደርስ ፤ አውቶሞቢሉ ፡ ቆመና ፡ ባለቤቴ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ ወጥታ ፡ «ጓዙን ፡ አቀብለኝ» አለች ። ከዚያም ፡ እየመራችኝ ፡ ቤቱን ፡ ከፍታ ፡ ገባን ። ግሩም፡ ነው። ከዚያ ፡ ጫጫታ ፤ ትርምስና ፡ የመንጋ ፡ ኑሮ፡ በኋላ ፤ ሌላ፡ ተጋሪ ፡ በሌለበት፡ ክፍል፡ መግባት፡ እንዴት፡ ያስደስታል ! ፀጥ ፡ ያለ ፡ ክፍል ! አረንጓዴ፡ ፎቴ ! እፎይ ! እንደቸኮለ ፡ ሰው ፡ ሄጄ ፡ ዘርፈጥ ፡ አልኩበት ። ጓዙን ፡ ይዛ ፡ ወደ፡ ሌላው ፡ ክፍል ፡ ገባች ። ተከትያት ፡ ሄድኩ። መኝታ፡ ቤቱም ፡ እንደሳሎኑ ፡ ያማረበት ፡ ነበር ። አዲስ ፡ ቁም ፡ ሣጥን --- ራዲዮ ! የኔ ፡ ዓይን ፡ ግን ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ አረፈ ። የሚውጥ ፡ ፍራሽ ፤ አዲስ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፤ ንጹህ አንሶላ ! መዓዛው ፡ ብቻ ፡ ሰውነቴን ፡ አረካው። «እፎይ!» አልኩ ፡ አሁንም ፡ በናፍቆት ፡ ከአልጋው ፡ ላይ፡ እየተገረደስኩ። ምናልባት፡ በአድራጐቴ፡ ሕፃን ፡ መስዬ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ደረቅ ፡ አልጋ ፤ ከዚያ ፡ የኮረንቲ ፡ ሕክምና ፤ ከዚያ ፡ ሠንሠለት ፤ ከዚያ ፡ ሁከት ፡ በኋላ ፡ አይፈረድብኝም ። አዲስ ፡ ሕይወት ፡ ነው ። ፀጥ ፡ ያለ ፡ አካባቢ ፤ የጸዳ ፡ ክፍል ፤ የሚታዘዝ ፡ አሽከር ፤ በኮረንቲ ፡ የሚተኩሰው ፡ ሐኪም ፡ ሳይሆን ፡ በፈገግታ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ የምታቆላምጥ ፡ ወይዘሮ -- የጓደኞቼ ፡ ዕድል ፡ አሳዘነኝ ።

ባዲሱ ፡ ንጹህ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ጭልጥ፡ ያለ ፡ ዕንቅልፍ ፡ ወሰደኝ ። ስነቃ ፤ መታጠቢያ ፡ ሙቅ ፡ ውሃ ፤ መለወጫ ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ጠበቀኝ ። ሰውነቴ ፡

የታደሰ ፡ መሰለኝ ። ራት ፡ በልተን ፡ ጥቂት ፡ እንደተዝናና
ሁም ፡ አባቷ ፡ ሊጠይቁኝ ፡ መጡ ።

«እህ ! ልጄ ፡ እንደምን ፡ ከረምክ ? » አሉ ፡ ሩቅ ፡ አገር
ንግድ ፡ ደርሸ ፡ እንደተመለስኩ ፡ ነጋዴ ። ከዚያም ፡ አከታ
ተሉና ፡ «መቸም ፡ ስላልጠየቅሁህ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግ
ልኝ» ፡ አሉኝ ።

ስለጤንነቴም ፤ ስለአኗኗሬም ፡ እምብዛም ፡ አልጠየ
ቁኝም ። እኔን ፡ ላለማስከፋት ፡ ይሁንም ፡ እንጃ ፡ ወይም ፡
በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ስለኔ ፡ መነጋገር ፡ አልፈለጉም ። አባ
ትና ፡ ልጁ ፤ ስለሚታደሰው ፡ ቤት ፤ ስለልጆቹ ፡ ትምህ
ርት ፤ ስለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ከተጨዋወቱ ፡ በኋላ ፤ « በሉ ፡
ደህና ፡ እደሩ» ብለው ፡ ወጡ ።

በሳሎኑ፡ ሁለታችን ፡ ተቀምጠን፡ ሳለ፡ «ልጆቹስ ? »
ብዬ ፡ ጻፍኩና ፡ ሰጠኋት ።

«መገናኘት ፡ አፈሩ» ፡ ስትል ፡ ተነሣችና ፡ ከጥቂት፡
ጊዜ ፡ በኋላ ፡ በክንዳቸው ፡ እየጐተተች ፡ አመጣቻቸው ።
ክንዴን ፡ ዘረጋሁላቸው ። ግን ፡ እነርሱ ፡ አንገታቸውን ፡
አቀርቅረው ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።

«አባባን ፡ ሳሙት ፡ እንጂ ! » ብላ ፡ ስታዛቸው ፡
አሁንም ፡ እየተሽኮረመሙ ፡ ቀረቡኝ ። ለነርሱ ፡ እንግዳ ፡
ሰው ፡ ሆኜባቸዋለሁ ። በአባት ፡ ፍቅር ፡ ዕቅፍ ፡ አድርጌ ፡
ልሞጨሙጫቸው ፡ ፈለግሁ ። ግን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡
በሙሉ ፡ ልብ ፡ እንደማይቀበሉኝ ፡ ተሰማኝ ። በንግግር ፡



እንዳላማባባቸው ፡ አንደበት ፡ የለኝም። የትምህርት ፡ ቤት፡
ጓደኞቻቸውስ ፡ « የዕብድ ፡ ልጆች ! » እያሉ ፡ ሲሳለቁባ
ቸው ፡ ኖሮ ፡ ይሆን ? ብዬ ፡ አሰብኩ ። ባለቤቴ ፡ የስሜቴን፡
ጭንቀት ፡ የተረዳች ፡ ይመስል ፡ «በሉ ፡ ልጆች ፡ ሂዱና ፡
አጥኑ» ፡ ስትል ፡ ወዲያው ፡ አሰናበተቻቸው ።

ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ደረቅ ፡ አልጋና ፡ የመንዝ ፡
ብርድ ፡ ልብስ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ በምቹ ፡ አልጋ ፡ ውስጥ
መተኛት ፡ መቸም ፡ የሚጠገብ ፡ አይመስልም ። ከሁለት፡
ዓመት ፡ ብቸኝነት ፡ በኋላም ፡ እንደገና ፡ ከሴት ፡ ገላ ፡ ጋር
መነካካት ፡ ገነት ፡ መግባት ፡ ነው ። ከአማኑኤል ፡ የወጣ
ሁበት ፡ የመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ አለቀ ።
ግን ፡ አዲሱን ፡ ሕይወት ፡ ገና ፡ መጀመሬ ፡ ነበር ። የአማኑ
ኤሉ ፡ ጓደኛዬም ፡ « እንዳትመለስ ፡ እጸልይልሃለሁ» ሲል
ተመኝቶልኛል ።

ሁለት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሕፃን፡ ልጅ፡ ተያዝኩ።
የቀረኝ ፡ መኃረስና ፡ መጋት ፡ ነበር ።

«አየለ ! ተነሥ ፡ ፊትህን ፡ ታጠብ »

«ቁርስ ፡ ደርሷል ፡ አየለ ! »

«ጺምህን ፡ ተላጨው ፡ እንጂ » ።

«ዛሬ ፡ ልብስህን ፡ ቀይር ። » ባለቤቴ ፡ የምሠራው
ንና ፡ የማልሠራውን ፤ የዕለት ፡ እንቅስቃሴዬን ፡ ሁሉ ፡
ስትመራ ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ አልነበረም ። ትእዛዝ ፡ እን
ዳይመስል ፡ በጣም ፡ ተጠንቅቃ ፡ ነው ። «እንዲህ ፡ ብታ

ደርግስ ? » ትለኛለች ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ የአማኑኤሉን ፡ ዶክተሬን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ጐበኘሁትና ፡ መረመረኝ ። ጤንነቴም ፡ እየተሻሻለ ፡ በመሔዱ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ። አእምሮዬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሰውነቴም ፡ እንደዚሁ ፡ መታደስና ፡ መለምለም ፡ ጀመረ ። ጧት ፡ ቁርሴ ፡ ቅንጨ ፡ ነው ። ቀን ፡ ጥብስ ፡ ይቀርባል ። ማታ ፡ ሾርባ ፡ አለ ። ከዚያም ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፤ በአማቼ ፡ አውቶሞቢል፡ እንደ ፡ መ'ኳንንት ፡ ከኋላ ፡ ተቀምጠን ፡ በሹፌር ፡ እያስነዳን ፡ በገፈርሳ ፤ በሾላ ፤ - - - በቦሌ ፡ ተንሸራሽረን ፡ እንመለሳለን ። ከሳሎኑ ፡ ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ መጽሐፍ ፡ በማንበብና ፡ ሙዚቃ ፡ በመስማት ፤ ከአውቶሞቢል ፡ የኋላ ፡ ወንበር ፡ ተንፈላስሸ ፡ የሀገር ፡ ውበት ፡ በመመልከት ፡ ሕይወትን ፡ በእርጋታ ፡ ማጣጣም ፡ ጀመርኩ ። ሳምንት ፡ ያህል፡ በሶደሬና ፡ በቢሾፍቱ ፡ እንድሰነብት ፡ ተደረገ ። ሰውነቴም በአስደናቂ፡ ፍጥነት፡እየዳበረ፡ ከመሔዱ፡ የተነሣ፡ ቅርጼን፡ በመስታወት፡ስመለከተው፡ እንዳልወፍርና ፡ እንዳልበላሽ ፡ ሳልሠጋ፡አልቀረሁም፡ከተፈጥሮዬ፡ ውፍረት፡ አልወድም ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የቤታችን ፡ ወጭ ፡ የሚመጣው ከአባቷ ፡ ቤት ፡ መሆኑ ፡ ይታወቀኝ ፡ ነበር ። ባለቤቴ ፡ ሌላ ፡ ገቢ ፡ እንደሌላት ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ይህም ፡ ባንድ በኩል ፡ የመዝናናት ፡ ስሜት ፡ አልሰጠኝም ። የሰብአዊነትና ፡ የወንድነት ፡ ክብሬን ፡ ለማግኘት ፤ ጤናማነቴንም ፡ ለማስመስከር ፡ ብፈልግ ፡ ከጥገኝነት ፡ ኑሮ ፡ መውጣት ፡



እንዳለብኝ ፡ ተሰማኝ ። አዎ ! ራሴን ፡ መቻል ፡ አለብኝ ። ካለበለዚያ ፡ አለኝታዬ ፡ የተሟላ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ምንም ፡ ሁናቴው ፡ የተለየ፡ ቢሆንም ፡ ጥገኝነት ፡ የት ፡ እንዳደረሰኝ ፡ አስታውሳለሁ። ራሴን፡ ካልቻልኩ፡ ሌሎች፡ ለኔ ፡ የሚገባውን ፡ ክብሬታ ፡ አይሰጡኝም ። ግን ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ? ይህ ፡ ጥያቄ ፡ በአእምሮዬ ፡ መመላለስ ሲጀምር ፤ ባለቤቴ ፡ ስሜቴን ፡ ከፊቴ ፡ ላይ ፡ አንብባው ፡ ይሆናል ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ «እየለ ፡ ሥራ ፡ ብትጀምርስ ?» ስትል ፡ ጠየቀችኝ ። በመገረም ፡ ትክ ፡ ብዬ ፡ ተመለከትኋት ። ምን ፡ ሥራ ? ንግድ ? ከገበያተኛው ፡ ጋር ፡ በምን እንደበት ፡ ልገናኝ ፡ እችላለሁ ? በወረቀት ? የሚጽፈውና ፡ የሚያነበውስ ፡ ስንት ፡ ነው ? የመቋቋሚያውስ ፡ ገንዘብ ፡ ከየት ፡ ይመጣል ? ያው ፡ ከአባቷ ፡ ንብረት ፡ ጥገኛ ፡ ሆኘ ፡ ልጀምር ? ዓይኔን ፡ ጭፍን ፡ አደረግሁና ፡ ማሰብ ፡ ጀመር ።

«ማለቴ ፤ ሥራ ፡ ፈልግና ፡ ተቀጠር ፡ እስቲ ! » አለች እንደጠንቋይ ፡ ሐሳቤ ፡ የታያት ፡ ይመስል ።

ራሴን ፡ አወዛወዝኩ ። ከዚያም ፡ ወረቀት ፡ ሳብኩና፡ «ማነው ፡ ዲዳ ፤ ከዚያውም ፡ ከአማኑኤል ፡ የወጣ ፡ ሰው ፡ የሚቀጥር ? እንዲያውም ፡ ዛሬ ፡ ሥራ ፡ በተወደደበትና ፡ ሠራተኛ ፡ በረከሰበት ፡ ጊዜ ! » ስል ፡ ጻፍኩላት ።

«ሳትሞክር ! » አለች ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፤ «ምናለ፡ ሞክር ! ራዲዮኑ ፡ የሚፈለጉ ፡ ሠራተኞች ፡ ይዘረዝራል። ስለሞከርክ ፡ የምትጐዳው ፡ ነገር ፡ የለም ። ካለመናገር ፡

ደጃዝማችነት ፡ ይቀራል ፡ ይባላል ፡ ባገራችን » ፡ ስትል፡ አግባባችኝ ። ተረታኽ ! አልኩና ፡ በልቤ፡ ሳቅሁ ። ዋናው ችግሬ ፡ አለመናገሬ ፡ አይደለም ?

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሐሳቧን ፡ ተቀብዬ ፡ ሥራ ፡ ፍለጋ፡ ጀመርኩ ። በሥራ ፡ ፍለጋ ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ለሚበልጡ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ደብዳቤ ፡ ማስገባቴ ፡ ይታወሰኛል ። ግማሾቹ ፡ ሠራተኛ ፡ ይፈለጋል ፡ ሲሉ ፡ በማስታወቂያ ፡ ያስነገሩ ፡ ናቸው ። ግማሾቹ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ ሲባል ፡ በሰው ፡ ሰው ፡ ሰምቸ ፡ ነው ። የኔ ፡ ማመልከቻ ፡ ተራ ፡ ሲደርስ ፡ ግን ፡ ሠራተኛ ፡ የሚፈልጉ ፤ ወይም ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ያላቸው ፡ ሆኖ ፡ አላገኘኋቸውም ።

«እናዝናለን ! አሁን ፡ ቀጠርን» ይሉኛል ።

«ስሕተት ፡ ነው ። ባጀት ፡ አልተፈቀደም» ፡ የሚል መልስ ፡ ይሰጠኛል ። ከሁሉም ፡ የሚያናድደኝ ፡ የአሉታውን ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ የማደርገው ፡ ደጅ ፡ ጥናት ፡ ነበር ። ማመልከቻው ፡ ከሹሙ ፡ ወደ ፡ ፔርሶኔል ፤ ከፔርሶኔል ፡ ወደ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፤ ከመዝገብ ፡ ቤት ፡ ተመልሶ፡ ወደ ፡ ፔርሶኔል ፤ ከዚያም ፡ ከሹሙ ፡ ጠረጴዛ ፡ ተመልሶ ፡ ይመጣል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቦታ ፡ የለም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ።

ከሁለት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያህል ፡ ማመልከቻዬን ተቀብለውኝ ፤ የጽሑፉን ፡ ፈተና ፡ አልፌ ፡ በቃል ፡ ጥያቄው ፡ ጊዜ ፡ አስናብተውኛል ።



«ሥራውን ፡ ልትሠራ ፡ ትችል ፡ ይሆናል ። ግን ፡ ከሁን ፡ ቀደም ፡ በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ፈጽሞ ፡ ያልተደረገ ፡ ነገር ፡ ነው ። አልተለመደም» አለኝ ፡ አንዱ ፡ የክፍል ፡ ኃላፊ ፤ ዲዳነቴን ፡ ከገለጥኩለት ፡ በኋላ ።

ሌላው ፡ ደግሞ ፤ «የሚቀበልህ ፡ የምታገኝ ፡ ፈጽሞ፡ አይመስለኝም ። በከንቱ ፡ ነው ፡ የምትለፋው » ሲል ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥ ፡ ምክሩን ፡ አካፈለኝ ። ግን ፡ ተስፋ አልቆረጥኩም ። ከቤት ፡ ተቀምጦ ፡ ከመዋሉም ፡ ሥራ ፡ ሲፈልጉ ፡ መዋል ፡ የሚሻል ፡ ነበር ። ጊዜ ፡ ያሳልፋል ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አካውንታንት ፡ ይፈለጋል ፡ ሲባል ፡ በሬዲዮ ፡ ሰማሁና ፡ ማመልከቻየን ፡ እንደዋዛ ፡ አስገባሁ ። በቀጠሮ ፡ ሐያ ፡ የምንሆን ፡ ሥራ ፡ ፈላጊዎች ፡ ለፈተና ፡ ተቀመጥን ። ሁሉም ፡ ገና ፡ ከትምህርት ፡ የወጡ ፡ መሆናቸው ፡ አኳኋናቸው ፡ ያስታውቃል። ከመካከላቸው ፡ በዕድሜ ፡ በሰል ፡ ያልኩ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነበርኩ ። የቀድሞ ፡ ሥራየም ፡ ሂሳብ ፡ ነክ ፡ ስለነበር ፡ ፈተናውን ፡ በግማሽ፡ ጊዜ ፡ ማጠናቀቅ ፡ አላቃተኝም ። ውጤቱን ፡ ለማወቅ ፡ ከሳምንት፡ በኋላ፡ ተቀጠርን።

በተባለው ፡ ቀን ፡ «የፈተናውን ፡ ውጤት ፡ ለማወቅ ነበር » ብዬ ፡ ስሜን ፡ ከሥሩ ፡ አስፈርኩና ፡ እንኳኩቼ ፡ ገብቼ ፡ ለክፍሉ ፡ ኃላፊ ፡ ሰጠሁት ።

ከፊቱ ፡ የነበረውን ፡ ፋይል ፡ አገላበጠና ፡ ስሜን ፡ አገኘ ። ከዚያም ፡ ቁመናዬን ፡ ከእግር ፡ እስከራሴ ፡ ተመለ

ከተና ፡ ፈተናውን ፡ በጥሩ ፡ ውጤት ፡ አልፈሃል ! ቁጭ ፡ በል » አለኝ ። ቀጥሎ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ተነሥቶ ፡ ከፊቴ ፡ ከእንግዳው ፡ መቀበያ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ አረፈና ፡ «የት ፡ ነው ፡ የተማርከው ? ካሁን ፡ ቀደምስ ፡ የት ፡ ትሠራ ነበር ? » ሲል ፡ ጠየቀኝ ። ከንቱ ፡ ነው ! የከንቱ ፡ ከንቱ ነው ! ፈተናውን ፡ ወድቄአለሁ ! ስውየው ፡ ዲዳ ፡ መሆኔን ፡ ገና ፡ አላወቀም ። ጥያቄየን ፡ በማስታወሻ ፡ ማቅረቤንም ፡ እንደ ፡ አክብሮት ፡ ቆጥሮት ፡ ይሆናል ፡ አልኩ ፡ በሆዶ ። ቢሮውን ፡ በርግጀ ፡ መፈትለክም ፡ አማረኝ ። ግን ፡ ከመናገር ፡ ደጃዝማችነት ፡ ይቀራል ፡ ብላኛለች ፡ ባለቤቴ—ከመሞከር ፡ ልበለው ? — ሐሳቤን ፡ ለወጥኩና ፡ ወረቀት ፡ ከኪሴ ፡ አውጥቼ ፡ «መናገር ፡ አልችልም ፡ ዲዳ ነኝ» ብየ ፡ ጽፌ ፡ ሰጠሁት ።

ጽሑፉን ፡ ሲያነብ ፡ ስሜቱ ፡ ድንጋጤ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። የአዘኔታ ፤ የመገረም ፤ የመደንገጥ ፡ ቅልቅል ፡ ነበር ። ዓይኑ ፤ ከጽሑፉ ፡ ወደኔ ፡ ከኔ ፡ ወደ ፡ ጽሑፉ ፡ ተመላለሰ ።

«ከልጅነትህ ፡ አንሥቶ ፡ ነው ? » ሲል ፡ ጠየቀኝ ። ራሴን ፡ በአሉታ ፡ አወዛወዝኩ ።

«እንዴት ፡ እንደደረሰብህ ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ፤ ልትነግረኝ ፡ ትፈቅዳለህ ? » ሲል ፡ ጠየቀኝ ። ወዲያው ግን ፡ መናገር ፡ አለመቻሌ ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ « አዝናለሁ ! » ሲል ፡ እጁን ፡ አራገበ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ወረቀት ፡ ቶሎ ፡ ሳብ ፡ አደረግሁና ፡ «ጽፌላመጣልዎ ፡ እችላለሁ» ስል ፡ አቀበልኩት ።

«ጥሩ ፤ እንግዲያውስ ፡ ሰኞ»፡ አለ ፡ ፈገግታ፡ እያሳየ።

ታሪኬን ፡ ሳልደብቅ ፡ ጻፍኩለት ። የአባቴን ፡ ውርስ እንዴት ፡ እንዳባከንኩ ፤ የሰው ፡ ቤት ፡ ሳሳድድ ፡ እንዴት አንደበቴን ፡ እንዳጣሁ ፤ መክሰሬን ፤ አማኑኤል ፡ ገብቼ ፡ መውጣቴን—ከዚያ ፡ በፊት ፡ ለማንም ፡ ባዳ ፡ ያላዋየሁትን ፡ ሁሉ ፡ ያለአንዳች ፡ ኃፍረት ፡ ዘረዘርኩለት ።

ምናልባትም ፡ «ታሪክህን ፡ ልሰማው ፡ እፈልጋለሁ» ሲል ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ አዘኔታ ፡ አደፋፍሮኝ ፡ ይሆናል ። ታሪኬን ፡ ሲረዳ ፤ ስሜቴ ፡ ሊገባው ፡ የሚችል ቢኖር ፡ እርሱ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ወይም ፡ ደግሞ ፤ ከብዙ ጊዜ ፡ እፍናትና ፡ ዝምታ ፡ በኋላ፡ እንድተነፍሰው፡ ሥውር ሕሊናየ ፡ ገፋፍቶኝ ፡ ይሆናል ።

ያም፡ ሆነ፡ ይህ፡ሰባት፡ሉክ፡ ወረቀት፡ ሞላሁና፡በፖስታ አሽጌ ፡ ሰጠሁት ። ፖስታውን ፡ ሲከፍት ፡ ሻይ ፡ ጋበዘኝና የጽሑፉን ፡ ብዛት ፡ ገምቶ ፡ «ነገ ፡ ትመጣ ? » ሲል ፡ እንደምክር ፡ ቀጠረኝ ።

በበነጋው ፡ ስሄድ ፡ እጁን ፡ በወዳጅነት ፡ ዘርግቶ ፡ በፈገግታ ፡ ተቀበለኝ ።

«ግሩም ፡ ታሪክ ፡ ነው ! » አለ ፡ ራሱን ፡ በመደነቅ፡
እያወዛወዘ፡ «በመጨረሻ፡ ደህና፡ መውጣትህም፡ ዕድለኛ፡
ነህ፡ እላለሁ» ከዚያም ፡ አነጋገሩን ፡ ወደቁም ፡ ነገር ፡ ለወ
ጠና ፡ «መቸም ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ሐሜት ፡ እንደ
ሚፈጥሩበት ፡ ይሰማኛል ። ግን ፡ ግዴለኝም ። ሥራውን ፡
መሥራት ፡ ከቻልክ ፤ እንደበትህም ፡ ሆኑ ፡ ያለፈ ፡ ታሪክህ
ዕንቅፋት ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ አይታየኝም ። እን
ተም ፡ ሌላ ፡ ዕድል ፡ እንድትሰጥ ፡ ይገባል ። መቸ ፡ ለመ
ጀመር ፡ ትችላለህ ? »። ተቀጠርኩ ፡ ማለት ፡ ነው ! ጆሮ
ዬን ፡ ማመን ፡ አዳገተኝ ። ትከሻዬን ፡ ነቀነቅሁ ። «በማን
ኛውም ፡ ጊዜ ! » ማለቴ ፡ ነበር ።

«መልካም ፤ በአዲሱ ፡ ወር ፡ ትጀምራለህ ! »
አለኝ ። በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ሲሸኘኝም ፡ «ካልሆነልህም ፡ የም
ስት ፡ ወር ፡ሙከራ ፡ ጊዜ ፡ ነው» አለኝ ፡ እንደቀልድ ።
መሸሹ ፡ ወይም ፡ ማስፈራራቱ ፡ ሳይሆን ፤ እኔንም ፡ እርሱ
ንም፡ማበረታታቱ ፡ ነበር ።

በሙሉ ፡ ተሰናድቶ ፡ ቢሮ ፡ እንደተሰጠኝ ፡ በተቀ
ዳሚ ፡ ያቀረብኩት ፡ ጥያቄ ፡ ቴሌፎኑ ፡ እንዲቆረጥልኝ ፡
ነበር ። ሌሎች፡ ሠራተኞች ፡ ቴሌፎን ፡ እንዲገባላቸው ፡
ይነዘንዛሉ ። የኔው ፡ ጥያቄ ፡ ደግሞ ፡ ፈጽሞ ፡ አዲስና ፡
የሚያስገርም ፡ ይመስላል ። ግን ፡ እንደሚያውቁኝና ፡
እንደሚያሠቃየኝ ፡ ታወቀኝ ። እኔ ፡ ደውየ ፡ ለመነጋገር



ኩቶ ፡ አልፈልገውም ። እርግጥ ፡ ከውጭ ፡ ወደኔ ፡ ትእዛዝ
ለማስተላለፍ ፡ ይመች ፡ ነበር ። ግን ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡
ቴሌፎኑን ፡ ሳነሣ ፡ «ሃሎ ! » ማለት ፡ አለብኝ ። ግን ፡ ይህ
ንኑም ፡ አልችልም ። ምን ፡ አስቸገረኝ ። የሚያስፈልገው
ትእዛዝ ፡ በማስታወሻ ፡ ሊተላለፍልኝ ፡ ይችላል ።

ከሥራዬ ፡ ጋር ፡ በቀላሉ ፡ ተላመድኩ ። አስቸጋሪ ፡
ነገር ፡ አልገጠመኝም ። መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ንግድ ፡ ነክ ፡ ስለ
ሆነ ፤ የገቢና ፡ የወጭ ፡ ሰነዶች ፡ እየተጠራቀሙ ፡ ይመጡ
ልኛል ። እኔም ፡ ከሰነዶቹ፡ ወደትልቁ ፡ መዝገብ ፡ እያዛወ
ርኩ ፡ ሒሳቡን ፡ አጠናቅቃለሁ።ማሥመሪያ ፡ጭቃ ፡ ቀለም፡
የሒሳብ ፡ መኪና ፡ አንደበት ፡ አያስፈልጋቸውም ።

ታሪኬ ፡ ወዲያው ፡ በመላው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተዳ
ረሰ ። ከፊሎቹ ፡ ሠራተኞችም ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ትሕትና
ያሳዩኝ ፡ ጀመር ። ሌሎችም ፤ «ይህኔ፡ ዘመዱ ፡ ቢሆን ፡
ነው ፡ እንጅ ፡ በማን ፡ አገር ፡ ዲዳና ፡ ዕብድ ፡ ይቀጠራል ?»
ብለው ፡ የክፍሉን ፡ ኃላፊ ፡ ሳያሙት ፡ አልቀሩም ። አብዛ
ኛው ፡ ወሬ ፡ ስለኔ ፡ እንደሆነ ፡ ይሰማኛል ።

ከዚያም ፡ ልደታ ፡ መጣች ! የመጀመርያው ፡ ደሞዜ
ቀን ! እንደአጋጣሚ ፡ ቢሮዬ ፡ ከግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት
ነበር ። በአራት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ገደማ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡
የገዙ ፡ ትልቅ ፡ ፖርሳ ፡ ይዞ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱን ፡ ሲከፍት ፡ «ሂ !

ልጆች ፡ ደሞዝ ፡ መጣ !» የሚል ፡ ድምፅ ፡ አንዱ ፡ አሰማ። መምጣቱን ፡ የሚያውቀውም ፡ ለማዳነቅ ፡ ደሞዝ ፡ መጣ ፡ እንዴ ? » እያለ ፡ ያገኘውን ፡ ሲጠይቅ ፤ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ «ደሞዝ ፡ አትቀበልም ?» እያለ ፡ ሲያሳስብ ፡ ግቢው ፡ አንድ ጊዜ፡ ተንቀሳቀሰ ። አንዱ፡ ከክፍሌ ፡ ድረስ፡ መጥቶ ፡ «ደሞዝ መክፈል ፡ ጀምረዋል ፡ አቶ፡ ---» ብሎ ፡ እንደትልቅ ፡ ቁም ነገር ፡ አበሰረኝ ። በሩብ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ የግምጃ ፡ ቤቱ ፡ በራፍ ፡ በሰው ፡ ጢቅ ፡ ብሎ ፡ ሞላ ። ክፍሉ ፡ በጣም ፡ ጠባብ ነው ። ደሞዝ ፡ ከፋዩ ፡ ከበራፉ ፡ አጠገብ ፡ አንዲት ፡ ጠረጴዛ ፡ ዘርግተው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ለመክፈል ፡ ሩብ ፡ ሰዓት ፡ ይወስድባቸዋል ። በኋላ ፡ እንዳየሁት ፡ አንዷን ፡ ብር ፡ ሁለት ፡ ሶስቴ ፡ ይቆጥሯታል ። በዚህ ፡ ላይ ፡ የብድር ፡ ሊስት ማስተያየት ፡ አለ ። የዕድር ፡ ሹሙ ፡ ካርኒውን ፡ ይዞ ፡ ካንድ በኩል ፡ ያጋፍራል ። የመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ አራጣ ፡ አበዳፊዎች ፡ «ቆይ ! የት ፡ ነው ፡ የምትሾልከው !» እያሉ ፡ ከበራፉ ላይ ፡ ይፈጠርቃሉ ።

ከውጭ ፡ ምድረ ፡ ሠራተኛ ፡ አሰፍስፎ ፡ ተገጥግጧል ፡

«እባክህ ፡ ምን ፡ ትጋፋለህ !»

«ሰውዬ ፡ ተራህን ፡ ጠብቅ !»

«ምን ፡ ትወድቅብኛለህ ! ራስክን ፡ ቻል !»

ጫጫታው ! ትርምሱ ፤ አንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ሠራተኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረሳል ። ሰዎች ፡ ለወር ፡



ደሞዝ ፡ እንደዚያ ፡ ሲንሰፈሰፉ ፡ አይቸ ፡ አላውቅም። ዓመት ሙሉ ፡ ደሞዝ ፡ የወሰዱ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ።

ከሁሉም ፡ የሚገርመው ፡ በዚያ ፡ ከሚጋፋው ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ አብዛኛው ፡ የወር ፡ ደሞዙን ፡ አስቀድሞ በብድር ፡ የጨረሰ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ብዙዎቹ ፡ አዲስ ፡ የብድር ፡ ሞዴል ፡ ይዘው ፡ ቀርበዋል ። ግማሾቹ ፡ ከደሞዛቸው ሩቡን ፤ አምሾውን ፡ ይወስዳሉ ። ከአንድ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ይዘው ፡ የሚወጡ ፡ መኖራቸውን ፡ አውቂአለሁ ።

አንዳንዶቹ ፡ « አረ ፡ እባካችሁ ፡ የዛሬን ፡ እለፉን » እያሉ ፡ ሲጨቃጨቁ ፤ «እባክህ ፡ ጊዜ ፡ አትፍጅብን» እየተባሉ ፡ በሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ እየተገፉ ፡ ይወጣሉ ። መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚመሰገንበት ፡ ደህና ፡ የሥራ ፡ ቅልጥፍና ፡ ሲኖረው፤በደሞዝ፡አከፋፈልና፡ በብድር፡ አሰጣጥ፡ረገድ፡ በጣም፡ የተዝረከረከ፡ ነበር። ለምሳሌ፡ ያ ፡ ሁሉ፡ ሠራተኛ፡ ሥራ ፈትቶ ፡ ከሚውል ፡ በፖስታ፡ አዘጋጅተው ፡ ቢያድሉትስ ? ይህም ፡ ቢቀር ፡ ፈጠን ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣሪ ፡ ቢቀጠርስ ?።

እኔም፡ ከቢሮዬ፡ ተቀምጬ፡ ይህን፡ ሁሉ፡ በመመልከት፡ ባንዱ ፡ ሲገርመኝ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከዚያ ፡ ግፊያ መካከል ፡ ገብቸ ፡ ደሞዜን ፡ ቶሎ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡ ሳያሰኘኝ አልቀረም ። ግንስ ፡ ሌሎቹ ፡ ሠራተኞች ፡ እንዴት ፡ ይታዘቡኝ ? ገና ፡ አዲስ ፡ ሠራተኛ ፡ ነኝ ። ያውም ፡ ልዩ ፡ ሐሜት ያለው ። ይሉኝታ ፡ ተሰማኝ ። «ትዕግሥትህን ፡ ለማሳየት፡ የምትችለው ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ የመጀመርያው ፡ አጋጣሚ» ብዬ

ራሴን ፡ ተፈታተንኩት ።

ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ አልቆ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላም ፡ እንደዚሁ ፡ ቀጠለ ። ወደ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓቱ ፡ ገደማ፣ ቀለል፣ አለ። ሦስት፣ ሰዎች፣ ያህል፣ ብቻ፣ ቀርተዋል። እኔም ፡ ቀራ ፡ ይገኙ ፡ ስጠባበቅ ፡ ቆየሁና ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ደሞዜን ፡ ተቀበልኩ ። አቤት ! ስንት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ፡ ደሞዝ ፡ በሥርዓት ፡ ስወስድ ? እንደአዲስ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ተሰማኝ ።

ጠረጴዛዬን ፡ አሰናድቸ ፤ ቢሮዬን ፡ ቆልፌ ፡ ወደቤቴ ፡ ጉዞ ፡ ስጀምር፤ ጨለማው ፡ ለዓይን ፡ ይዞ፣ ወደአንድ ፡ ሰዓት፣ ተጠግቶ ፡ ነበር ።

በአውቶቡስ ፡ ወይም ፡ በሰይቸንቶ ፡ ለምን ፡ እንዳል ተሳፈርኩ ፡ አይገባኝም ። ይሻለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የካቦርቴን ፡ ክሳድ ፡ ወደላይ ፡ ቀንፌ ፤ እጆቸን ፡ ከኪሴ ፡ ከትቼ በቀስታ ፡ የሽርሽር ፡ አረማመድ ፡ ወደቤቴ ፡ ጉዞዬን ፡ በእግሬ ፡ ቀጠልኩ ።

በአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ ታጥፌ ፤ ከፒያሳ ፡ አንድ የማነበው ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ገዝቼ ፤ የኤደንን ፡ መንገድ ፡ በደህና ፡ ስሜት ፡ ዘለቅሁ ። ሰዓቱ ፡ ገፍቶ ፤ ወደቤቱ ፡ ከሚገባውና ፤ ለአዳሩም ፡ ከሚወጣው ፡ አንዳንድ ፡ ተላላፊ በተቀር ፡ አደባባዩ ፡ ጭልል ፡ ማለት ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ከታች በኩል ፡ የኤሌትሪክ ፡ መብራት ፡ ቢብለጨለጭም ፤ ከላይ



የጠራች ፡ ጨረቃ ፡ ወለል ፡ ብላለች ። ቀለል ፡ ያለ ፡ ለስላሳ አየር ፡ ይነፍሳል ። ለሽርሽር ፡ የሚያስደስት ፡ ምሽት ፡ ነበር ።

የጊዮርጊስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አልፌ ፡ የመስፍን ፡ ሐረርን ፡ መንገድ ፡ እንደተያያዝኩት ፡ ሙማማቱ ፡ ተጀመረ። መጀመርያ ፡ ድምጹ ፡ መጣ ። ያ ፡ የማውቀው ፡ የዳንስ ፡ ሙዚቃ ፡ በሩቁ ፡ እንደሚጣራ ፡ የዛር ፡ ፉጨት ፡ ጆሮዬን ፡ ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገው ። ከዚያም፣ እኔ ፡ ወደሠፈሩ ፡ ስጠጋ— የማልፈው ፡ በርሱ፣ በኩል ፡ ነበር—ድምፁ ፡ እየጐላና ፡ እየበዛ ፡ ሄደና ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያፍነኝ፡ጀመር ። አማርኛው፤ የሱዳኑ ፤ የዓረቡ ፤ የፈረንጁ ፡ ሙዚቃ ፡ በዓየር ፡ ውስጥ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ያስተጋባል ። ጩኸት ፡ ነው ፡ ጫጫታ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ እርምጃዬ ፡ ሥቃይና ፡ ጭንቀት ፡ ሆነብኝ ። ጆሮ ፡ ያደነቁራል ። ራስ ፡ ያማል ። «ምን ፡ አመጣኝ ፡ በዚህ ሠፈር ?» ብዬ ፡ ተጸጸትኩ ። በዚያን ፤ ሰዓት ፡ በእግሬ ፡ በዚያ ሠፈር ፡ ሳዘግም ፡ የመጀመርያ ፡ ጊዜዬ ፡ ነበር ። ግን ፡ ወደኋላ፡ አልተመለስኩም ። ፈሪ ! የምን ፡ ሽሽት ፡ ነው ? ራስክን ፡ አታምነውም ? አልኩት ፡ ራሴን ።

በመጨረሻም ፡ ከሠፈሩ ፡ መካከል ፡ ስገባ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሰጠምኩ ፡ መስሎ ፡ ተሰማኝ ። የድምፅ ፡ የሽታ ፤ የትርኢት ፡ ባሕር ። አዎ ! ጩኸቱ ፡ የጆሮን ፡ ነጋሪት ፡ የሚነድል ፡ እስኪመስል ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይደበደባል ፤

ሽታው...የቡናው...የዕጣኑ...የኡዱ...የሽቶው.. አፍንጫን
ያፍናል ። ትርኢቱ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡ ነው ።
ቢጫ ፤ ቀይ ፤ አረንጓዴ ፡ ኅብረ ፡ ቀለም ፡ መብራት ፤ መቅ
ደስ ፡ የሚመስል፡ መጋረጃ፤ ዙሪያውን፡ የሚብለጨለጨው፤
የሚንቦገቦገው ፤ ደብዛዛ ፡ ብሉ ፡ ምሥጢር ፡ የሚመስለው
ትርኢት ፡ ዓይንን ፡ ያጭበረብራል ። ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ልብንም
ያጭበረብራል ። አንዷ ፡ ከጉራጌው ፡ ኪዎስክ ፡ ሲጋራ ፡
ገዝታ ፡ ከፊቴ ፡ ላይ ፡ መንገዱን ፡ ታቋርጣለች ። ሌላዋ ፡
ከፊቴ ፡ እንደትዊስት ፡ እየታጣች ፡ ትወዛወዛለች ። በየሥ
ፍራው ፡ ወንድ ፤ በየሥፍራው ፡ ሴት ፡ ውር ፡ ውር ፡ ይላል ።
ግማሾቹ ፡ ሴቶች ፡ የየበራፋቸውን ፡ መጋረጃ ፡ ገለጥ ፡ አድር
ገው ፡ ቆመዋል ። ሌሎቹ ፡ ከደጃፉ ፡ አጠገብ ፡ ወንበር ፡ ዘር
ግተው ፡ ተቀምጠዋል ። የድመትና ፡ የአይጥ ፡ ድብብቆሽ፡
ጨዋታ ፡ ይመስላል ። ማንኛው ፡ አይጥ ፤ ማንኛው ፡ ድመት
እንደሆነ ፡ አይታወቅም ።

ድንገት ፡ ሳይታወቀኝ ፤ ያስመጠኝ ፡ የአካባቢ ፡ ባሕር፡
ስሜቴን ፡ እየሰረጸው ፡ ገባ ። በዚያ ፡ መጋረጃ ፡ ጀርባ ፡ ከስ
ንቶች ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ ተጫወትኩ ? መጠጥስ ፡ እንዴት ፡
ያለ ፡ ሙቀትና ፡ የትልቅነት ፡ ስሜት ፡ ይሰጠኝ ፡ ነበር ?
ስዕሉ ፤ ትዝታው ፡ ከፊቴ ፡ ላይ ፡ ይደቀንብኝ ፡ ጀመር። ኪሴን
በመዳፌ፡ ዳበስኩት። አሁንም ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ስልሣ፡ ሶስት፡
ብር ፡ በኪሴ ፡ አለ ። ያቺ፡ ሽንጣሟ ፡ ኮረዳ ፤ ያቺ ፡ ወገቧን ፡
የምትሰብቀው ፡ ቆንጆዬ ፡ በመጠጡና ፡ በጭጋው ፡ ከተገባ
ባን ፡ የፈለግሁትን ፡ አገልግሎት ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለች !



አሁን ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ ! ምስኪኖች ! አሁንም ፡ ልጫወት
ባቸው ፡ እችላለሁ ! የጥንቱ ፡ ጋሼ ፡ በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡
ሲንቀሳቀስ ፡ ተሰማኝ ። ገንዘቡ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ከአማ
ኑኤል ፡ ከወጣሁ ፡ አንስቶ ፡ ያንን ፡ ያህል ፡ በክብካቤ ፡ ሲያዝ፡
ገንዘብ ፡ ከቶ ፡ በእጄ ፡ ገብቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ባለቤቴ ፡
አውቃ ፡ የተጠነቀቀችበት ፡ ይመስላል ።

የሚያስፈልገኝ ፡ ሁሉ፡ ይቀርብልኛል።ከዚህ፡ በተረፈ፡
ግን ፤ ምናልባት ፡ ለሰይቸንቶ ፡ መሣፈሪያ፡ የምትሰጠኝ፡ከአ
ንድ ፡ ብር ፡ አይበልጥም ፡ ነበር ። አንድ ፡ ብር ፡ ደግሞ ፡
ብዙ ፡ የሚያሳስብ ፡ ገንዘብ ፡ አይደለም ። እንሆ ፡ ከሁለት ፡
መቶ ፡ ሃምሳ፡ ብር፡ በላይ፡ በኪሴ፡ አጭቄ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ከለ
ከፈኝ ፡ አካባቢ ፡ ውስጥ ፡ ራሴን ፡ አገኘሁት ። ፍትወተ ፡
ሥጋዬ ፡ አልተነሣም ። ብቻ ፡ መንፈሴ ፡ ተማታብኝ ።
የቆሙት ፤ የተቀመጡት ፤ ውር ፡ ውር ፡ የሚሉት ፡ ሴቶች ፡
ሁሉ ፡ በተለይ ፡ እኔን ፡ የሚጠቅሱኝ ፡ መሰሉ ፡ ታየኝ ። ይስ
ቁብኛል ! ይስቁልኛል ! እጃቸውን ፡ ያርገበግባሉ ፡ ና !
እያሉኝ ! ና ፡ እንጂ ! የት ፡ ጠፋህ ! መዚቃው ፡ «ግባ ?
ግባ! »የሚል ፡ ምት ፡ አለው። ሰውነቴ ፡ ከበደኝ። እንደተጫ
ነች ፡ አህያ ፡ ትንፋሼ ፡ በጭንቀት ፡ እየተቆራረጠ፡ ሲወጣ፡
ይታወቀኝ ፡ ነበር ። እንደትዝት ፡ ጉዞ ፡ ዓይኔን ፡ ከአንዱ ፡
መጋረጃ ፡ ጀርባ ፡ ተክዬ ፡ ሳልፍ—ቾፍ ፡ ቾፍ ! - የተረጨ ፡
የባሕን ፡ ውሀ ፡ አስደነገጠኝ ። ነጃባ ! አልኳት፡ በእንቅልፍ፡
ልብ ። ራሴን ፡ አመመኝ—ራሴ ፡ ሲዞር ፡ ነው ! «—እዬ ፡

ፈጣሪዬ——ተስፋ ፣ የለኝም —— ከንቱ ፣ የከንቱ ፣ ከንቱ ፣ ነኝ——» አልኩ ። ዓይኔን ፣ ጨፈንኩት ። ሴቶቹ ፤ ሙዚቃው——ሽታው ፣ ጠርሙሱ፣ ከዚያው፣ አለ ። ከዓይኔ፣ ሥር፣ ይታየኛል ። ጭንቅላቴን ፣ በሁለት ፣ እጄ ፣ ደግፌ ፣ ቆምኩ ። ይሀ ፣ ራሴ ፣ ምንድን ፣ ነው ? ጤነኛ ፣ አይደለም ? የአማኑኤሉ ፣ ጓደኛዬ ፣ «እንዳትመለስ ፣ እጸልይልሃለሁ ?» ሲል ፣ የመረቀኝ ፣ ትዝ ፣ አለኝ ። በዚህ ፣ ሁናቴማ ፣ ምኑን ፣ ቀረሁት ! እንደገና ፣ ወደዚያ ፣ ኮረንቲ ፤ ወደዚያ፣እግር፣ ብረት፣ ወደዚያ፣ ጫጫታ——ወደዚያ ፣ ብረት ፣ አልጋ ! የለም ! አልመለስም ! ፈጽሞ ፣ አላደርገውም ! ያ ፣ የጸዳ ፣ ቤት ፤ ያ ፣ ንጹሕ ፣ አንሶላና ፣ ምቹ ፣ ፎቴ ፣ ታየኝ ። ባለቤቴ ፣ ምን ፣ ትለኝ ? አሁንም ፣ ትጠብቀኛለች ። ያ ፣ ልማድ ፣ ቀመስነቷ ፣ አይለቃትምና ፣ ምናልባት ፣ የልደታ ፣ ቆሎ ፣ ቆልታ፣ ጉዝጓዝ ፣ ጣል ፣ ጣል ፣ አድርጋ ፤ ቡና ፣ አፍልታ ፣ በራፍ ፣ በራፉን ፣ ታይ፣ ይሆናል ። የለም ! ወደአማኑኤልስ፣ ፈጽሞ፣ አልመለስም ። የለም ! የለም ! መንፈሴ ፣ እርስ ፣ በራሱ ፣ ሲታገል ፣ አረማመዴ ፣ ጠዕረ ፣ ሞት ፣ ዓይነት ፣ ነበር ። ግን ፣ ከሠፈሩ ፣ ዳርቻ ፣ ደረስኩ ። ጩኸቱም ፤ መዓዛውም ፣ እየቀለለ ፣ ሄደ ። ትርኢቱ ፣ ወደኋላዬ ፣ ቀረ ። ከእፍናቴ ፣ ትንሽ ፣ ተነፈስኩ ። ግን ፣ ራሴ ፣ ምታቴ ፣ አልተወኝም ። የጤንነቴ ፣ ምልክት ፣ ይሆን ? ሰውነቴም ፣ ብርቱ ፣ ድካም ፣ ተሰማው ። ቤት፣ በደረስኩ፣ ጊዜ፣ ከግንባሬ፣ ላይ፣ ደረቅ፣ ወዝ፣ ፍፍ ፣ ብሎ ፣ ነበር። በመጨረሻ ፣ ተወጣሁት ! ዘለቅሁት !



«ይሔውልሽ !» አልኩና ፣ ጥቅሉን ፣ እንዳለ ፣ ሰጠኋት ፣ ከሳሎኑ ፣ ላይ ፣ እየተዘረገፍኩና ፣ ባንድ ፣ እጄ ፣ የግንባሬን ፣ ላብ ፣ እየጠረግሁ ።

ከዚያም ፣ ጫን ፣ ተነፈስኩና ፤ «ታክስ ፣ እንደሚቆረጥለት ፣ ታውቂ ፣ የለም ? ሁለት፣ ብር ፣ ካምሳ፣ ደግሞ፣ ለመጻፍ፣ መግዣ፣ አንስቼለታለሁ» አልኳት።አልቆጠረችውም። ከፎቴው ፣ ካንድ ፣ በኩል ፣ እንደዋዛ ፣ አስቀመጠችውና ፣ በፈገግታ ፣ ተመለከተችኝ።ገንዘቡ ፣ ሳይሆን ፤ ኩራቷ ፣ በኔ ፣ እንደሆነ፣ ከፊቷ ፣ ላይ ፣ ይነበብ ፣ ነበር። «እስከዚህ፣ ድረስ ፣ የሚኮራብኝ ፣ ነኝ ? ዋ ! ያለፍኩትን ፣ ጭንቅ ፣ አለማወቅ ! ግን ፣ እንዳላሳፍርሽ ፣ እሞክራለሁ !» አልኩ ፣ በሆዴ ።

ተ ፈ ጸ መ ።

# ጨረቃ ስትወጣ

# የጅሎች መታሰቢያ

አፈቀርን ተፋቀርን
ዓለምን አየን ተስፋ
ሕይወት ለምልሞ እንደ ልጅ ሲፋፋ
መልሶ ሲረግፍ
እንደ በጋ ቅጠል ድራሹ ሊጠፋ ፤
ተባባልን ፍቅር ነው የመኖር አለኝታ ፤
የጸደይ ጨረቃ
ስታበራ ደምቃ ፤
ቃላችን ተሰርቆ ልባችን ሲመታ ፤
አለኝታችን መጥቆ ጽርሐ አርያም ከፍታ ፤
ደስታ ፤
ፍጹም ደስታ ፡፡
ነበር እምነታችን የፍቅር ሃይማኖት
ለራሳችን ዓለም ፈጥረን የኖርንበት ።
ፍቅር መስሎን ነበር
እንደ ወንዝ እንደ ሐይቅ እንደ ተራሮቹ
ቋሚ ገሐድ ነገር ።

ለካስ እሳት ኖሯል ችቦው ቦግ ብሎ
እኛን ዓመድ ሊተው ሲያበቃ ተቃጥሎ ።
ሕይወት ውርጭ ሲሆን በሞት ተበርዞ
ማገዶ እንዳለቀ ምድጃ ቀዝቅዞ ።
መከሩን ብልጦቹ ጅሎቹን ሲያጽናኑ
እንደቅዝቃት እርሱት በፍቅር አትመኑ ።
ፍቅር ጅልነት ነው ፤ ይሁን ! ከተባለ
ያሸነፈው ብልጠት አሳዩን የታለ ?



## ምዕራፍ ፭

## የመጨረሻው መጀመርያ ።

በቀለ ፤ አበልጅ ጸሐፊውንና ይዛት የመጣቻትን ልጃገረድ በደጃፉ በኩል ሸኝቶ ተመለሰና ከመስኮቱ ላይ ተጠግቶ ግቢውን እስኪወጡ በዐይኑ ተከተላቸው ። ከግቢው ውጭ አውራ ጐዳናውን ይዞ ሕዝቡ ይትርመሰመሳል ። ከአዲስ ከተማ ለጥቆ ሕዝብ የሚበዛበት ሰፈር የጥንቱ ቄራ መሆኑን የማዘጋጃ ቤቱ ቁጠራ ይገልጻል ። ግንበኛው ፣ አናጢው ፣ እንጨት ፈላጩ ፣ የቀን ሠራተኛው -- የሠራተኛ ሰፈር ነው ። ሌላም ሞልቶበታል ። ምስት ሰዓት ካለፈ በኋላ የኤሌትሪኩን ምሰሶ እየተደገፉ አላፊ አግዳሚውን ምጽዋት የሚጠይቁ የሚመስሉት ሕፃናት ሴቶች ፣ ራቴን አብላኝ እያለ የሚያንገራግረው ዱርዬ ፣ መስኮት ሰብሮ የሚገባው ሌባ -- ሁሉም ዐይነት በዚህ ሰፈር ታጉሯል ። በተለይም እሑድ ከሰዓት በኋላ ፣ ሠራተኛው ፣ ወስላታው ፣ ሥራ ፈቱ ቡና ለቃሚዋ --- ሴቱ ፣ ወንዱ ሁሉም የሳምንቱን ጥግት በአ

ኅድ ቀን ጠጅ ስካር ለመወጣት የሚሻማ ሲመስል ፤
ግርግሩ ፣ ጠቡና አምባጓሮው አይጣል ነው ።

በቀለ ከመስኮቱ ላይ ቆሞ አንዱ እንጀራ ነጥቆ
ሲሮጥ ፣ ሌላው እየተንደፋደፈ ሽሮ ሲደፋ ፤ ሴቶች ጸጉር
ሲናጩ ፤ አሳላፊዎና ጠጪው ክፈል አልከፍልም -
ሲጓተቱ ብዙ ጊዜ በመመልከት ፤ ብዙ ጊዜም ሰፈሩን
ሊለቅ አስቦ ነበር ። ግን ግቢውን ይወደው ነበር ። በአ
ጉራ ዘለልነት የሚያሳጣው የባለቤት ጎረቤት የለበትም ፤
እያመሸ ከእንቅልፉ የሚያውከው ላጤም የለም ። በግ
ቢው ውስጥ ሌላ ቤት አልተሠራም ። ለብቸኝነት ስሜቱ
በጣም የሚስማማ ነበር ።

ሁለቱ ሴቶች በዚያ የእሑድ ግብስብስ ሕዝብ መካ
ከ ተውጠው ሲጠፉ ፊቱን ወደ ክፍሉ መለሰና
«ልፋት ነው ፤ ከንቱ ልፋት ነው» አለው ከፍቴው ላይ
ለተቀመጠው አንጎቱ ። ከወለሉ ላይ ጥቂት ቆሞ በሐሳብ
ተከዘና ድንገት ራሱን መሸከም የታከተው ይመስል
ሰውነቱን እንደ ዕቃ ከፎቴው ላይ ዘረገፈው ። እነጋገሩ
ተስፋ የመቍረጥ ቅላጼ ነበረበት ። ሳይሰለችስ ይቀራል ?
ከብዛታቸው የተነሣ እያመጡ ያማረጡትን ልጃገረዶች
ቍጥር አጥፍቶታል ። ከቤቱ ድረስ የመጡለት ብቻ ከን
ምሳ በላይ ይሆናሉ ። ጓደኞቹ እንደ መከሩት በሥራ
መውጫ ሰዓት ላይ ከባንክ ቤት ፣ ከአውራ ጎዳና ፣



ከአየር መንገድ ፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤቶች ደጅ
ላይ እየጠበቀ የተመለከታቸውማ ስፍር ቍጥር የላቸ
ውም ። ሰውን እንደ ዕቃ መፈለግ ሞኝነት ያሰኛል ።
ግን የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ሆኖበት ነው ። የሚፈ
ልጉትን ሴት ዐይነት ከማግኘት ጋራ ሲነጻጸር ደግሞ ፤
አንዱ ዲቃላ ያስቋጠራትን ርጉዝ ማግኘት የመጨረሻው
ቀላል ነገር መሆን አለበት ።

በቀለ ከእነዚያ መዓት ሴቶች ሁሉ አንዳቸውም
ሊማርኩት አልቻሉም ። አንዷ ሞጋጋ ናት ። ሌላዋ አላጤ
መሆኗ ከፊቷ ያስታውቃል ። አንዷ ደደብ ትሆንበታለች ።
ጐደሎ ጐደሎ ! ያልተስተካከለ ብቻ ! ስንቱን የሴት ዐይ
ነት አሳዩት ? ስንት ዐይነቱ ጉድ አለ ? የኛው ትውልድ
ብቻ ነው ፤ የትናንቱም ትውልድ እንደዚሁ በጠጣ ፤
በጉድ የተሞላ ነበር ? ገና ተዋውቃው ከሳሎን እንደተቀ
መጡ ፤ ቀሚሷን ከፍ አድርጋ የጭኗን ቅርጽና ነጸብራቅ
ያስመረቀችው ነበረች ። ምናልባትም ሥራ የተቀጠረ
ችው በዚሁ ይሆናል ። ፐርሶኔሉ ልቡ እንዴት ተሰው
ሮበት ይሆን ? ምስኪን ! የደሞዝ ጭማሪውስ በዚያው ሳይ
ገኝ ይቀራል - ? ከዚህ ላይ ዲሬክተሩ ወይም የክፍል ኃላ
ፊው ድርሻውን ማግኘት አለበት ። ምናልባትም - መቼም
የጾረ ፍትወት ዘመን ነው ፤ ባልም ለማጥመድ ያው
የመሥሪያ ቤት መሣሪያ የሚጠቅም መስሏታል ።

መናጢው በቀለ ግን ወዲያው በነእምሮው የመጣበት
« አሁን ይህን ጭን ስንቱ መርቆታል ? » የሚል ሐሳብ
ነበር ። ብዙ ሳያንጋግር ሸኛት ። ሌላዋ ደግሞ ጨዋታ
ገና ከመጀመራቸው አምስት መቶ ብር ደሞዝ የምታ
ገኝ መሆኗን ገልጣለታለች ። ደሞዟ የሚያስጐመጀው
መስሏታል ። የዘመኑን የጋብቻ አዝማሚያ በመከተል
ነው ። ሕይወት ራሱ በገንዘብ ሊተረጐም ምን ቀረው ?
ግን በቀለ ከጋብቻ የሚጠብቀው ሀብት ቢሆን ኖሮ ፣
ባለደሞዟ ሳይሆን ፣ ባለጋሻ መሬቷና ባለቪላዋ ትበል
ጥበት ነበር ።

አብዛኞቹ ግን በማፈርም ይሁን ጭውነታቸውን
በዝምታ ለማሳመን እንገታቸውን አቀርቅረው ጥፍራቻ
ውን እየቀነጣጠቡ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ሁሉ «አዎ»
«የለም» የሚል መልስ እየሰጡ የተሰናበቱ ናቸው ። ብዙ
ባናና በተዋወቀ ቍጥር ጕድለታቸው በዚያው መጠን
እየጨመረ ይሄድበታል ።

ይህችኛዋም ልቧገረድ ከርሷ በፊት በምርጫ ፊት
ናው እየተቀመጡ ከወደቁት የተለየች አይደለችም ። ከእ
ያንዳንዱም ፈተና በኋላ ሰውነቱ ይታወክበታል ። ተስ
ፋቸውን ቀስቅሶ መልሶ ማኰማተር ኃጢአት ነው ።
እንደ ዕቃ መገምገም ባልተገባ ነበር ።

« ታዲያስ አልጣመችህም ? » ሲል አጎትዬው በፈገ
ጠየቀው ።



« አልቀመስኳትም » አለ ። መልሱ ቀልድም ፣
ውስጠ ወይራም ነው ። በቀለ ከነገሩ ሁሉ ከአንጻቸውም
የቅርብ ግንኙነት ለማድረግ ፈጽሞ አይሞክረውም ።
ጸጸቱን ያውቀዋል ።

« ኧረ እንዲያው » አለ አጎትዬው መዳፉን ከፎቴው
አግዳም ላይ እየጠበጠበ « ምን ዐይነቱን ሴጸ በለስ ብታ
ቀምስህ ነው ወንድሜ ? »

በቀለ ቱግ አለበት ። ለምን ለቀት አያደርጓትም ?
አልያረሰችባቸው ። « ወንድምህ ጠፍቶ እንደሆን ማር
ካቶ ሂደህ ጠይቀው » ሲል አሾፈ ። በዕድሜ እኩያ ስለ
ሆኑ በጨዋታ ይደፋፈራሉ ።

« እኮ ታዲያ እንዲህ የሚያስጨንቅህ ? ጋብቻ ባንተ
አልተጀመረ » አጎትየው አነጋገሩን ለማለዘብ ሞከረ ።

« ርግጥ ! ርግጥ ! » በቀለ ሲጋራ እያቀጣጠለ ያፈገ
ጀመር ። « ጋብቻ በኔ አልተጀመረም ። ትርጓሜ ካለው
አዳሜ ይጋባል ፣ ይዳበላል ልበለው ? እናንተምኮ ለግብ
ታችኋል ፤ ወልዳችኋል ፤ ከብዳችኋል ። ታዲያ ጭልም
ሲል በየጉራው እያነፈነፋችሁ እኛኑ መጋራታችሁ አል
ቀረ ። የት ላይ ነው ጋብቻችሁ ? ወግ ነው ። የይስሙላ
ጭውነት »

« አላበዛኸውም በቀለ ! »

« ራስክን እራቁቸ እንዳሳይህ አይደል የፈለግኸው ?»
ሲል በቀለ ጠየቀና መልሶ « እንደማታየው ጋብቻ

ብዙ ዐይነት ነው ። ግማሹ ለጥቅም ይጋባል ። ሽርክና እንበለው ። ግማሹ ለሥጋ ፍትወት ይጋባል ። ስሙን የለወጠ ሽርሙጥና ነው ። ሌላው ፤ ወጉ እንዲደርሰው ብቻ በይምሰል ይኖራል ። አዝናለሁ ፤ እኔ ይህንን ሁሉ አልቀበለውም ። የማገባት ወይም የምታገባኝ በሥጋና በመንፈስ ጠቅ፡ ላ የምትውጠኝ መሆን አለባት ። ታውቃለህ ? ዳሩ ምን ታውቃለህ ፤ በፍቅር ለፍቅር ፣ ስለፍቅር የምኖርላትና የምኖርባት ናት የኔ ሚስት » አለ ።

« አረጋዊ ነህ ፈላስፋ ? » አንትዬው ራሱን ነቀነቀ ። በቀለ ግራ ፍጡር ሆኖበታል ።

« ሁለቱንም ብሆን አያስነውርብኝም » አለ በቀለ ሲጋራውን ቡንን እያደረገ ። ከዚያም ቀጠለና « ምነው ዛሬ ካስ ሜዳ ሄደህ ትንሽ አትላዝንም እንዴ ? እሑድኮ ነው ። ሳንጆርጅ የተሸነፈ እንደሆን ደውልልኝ ፤ አስፐሮ ገዝቼ እቆይሃለሁ ። አሁን እኔ ትንሽ ማንበብ እፈልጋለሁ ። » ሂድልኝ ማለቱ ነበር ። መጽሐፍ ማንበቡ ግን ሲያብል ነው ።

« በቀለ ለምን አትሞክርም ? ችግሩኮ አለመሞከርህ ነው » አለ አንትዬ ሊወጣ በሩን በጁ ይዞ ። ከምክር ይልቅ ልመና ነበር ።

« አልሞከርኩም ትለኛለህ ? ከዚህ የበለጠ ምን ላድርግ ? » ሲል በቀለ ትካዜ በተሞላው አንደበት መለሰለት።



« ማለቴ ፤ ለማፍቀር እኮ አትሞክርም ። አስቀድመህ ልብህን ዘግተኸዋል » አንትዬው መልስ ሳይጠብቅ እጁን አወዛውዞ ሄደ ።

በቀለ ብቻውን ሲቀር ፣ ሸሚዙን ለወጠና በቁም ሣጥኑ መስታወት እየተመለከተ ክራባቱን አስተካከለ ። ከመስታወቱ ውስጥ ያለውን « እሱነቱን » ብዙ ጊዜ ያህል ካስተዋለው በኋላ « አንተ ምስኪን ! » ብሎ ራሱን ነቀነቀ ። አካላዊ ሰውነቱ እስከዚህም ቅር የሚያሰኘው አልነበረም ። መልከ መልካም ነው ። እሁን አሁን እያሰበ አንገቱን ይደፋ ጀመር እንጂ ፤ በዚያ ቁመቱ ፤ በዚያ የቀይ ዳማ ደም ግባቱ የሚጥል በሽታ ነበር ። በልጅነቱ ከብርዘበኛ አገባለሁ እያለ ወላጆቹን ያስቸግረውም ባለዛላው ይመለመላል ሲሉ ሰምቶ ነበር ። ሰዎች የሚነግሩት ጉድለት « ትንሽ ሥጋ ብትጨምር » የሚል ብቻ ነው ። የሰው ሥጋ ይበላል ፤ ፀሐይ ፤ ሰውነት ፤ ሥጋ ብቻ ሆኖ ቀረ ።

በዚህም በዚያም ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰውነቱን እየተጸየፈው ተቸግሯል ፤ ራሱን «አንተ ምስኪን» እያለ ሲያጥየው የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም ። በተለይም እንደ አሁኑ ሴቶች ከሸኙ በኋላ። ምናልባት ወጥቶ አንድ ሁለት መለኪያ ቢጎነጭ ይቀለዋል ። ከዚያም — ሳያሰኘው አልቀረም ። ቦርሳውን አውጥቶ ገንዘቡን ቈጠረ ። ይበ

ቃል ። አዎ ! ሕይወት ይኸው ነው። ለርሱማ፣ ነገር ዓለሙን ቢተወው ይሻለው ነበር ። ግን የሚያስተወው አላገኘም ። ቤተ ሰቦቹ መቆሚያ ፥ መቀመጫ ያሳጡታል ። ለአርጊት አክስቶቹ ፥ ለትልቅ እህቶቹ ከርሱ ሕይወት የሚፈልጉት ጌሾ አስጥተው ፥ ብቅል ወቅተው ፥ መንደሩን በወሬ ሲያዳምቁ ሰንብተው በሠርጉ ቀን ሽር ጉድ ማለታቸውን ነው ። « ግብዣው ቀለጠ ። ዘፈኑ ደመቀ ። ልጃችን ቄንጀ ልጅ አገባ » ከዚያ በኋላ የሚከተለው ግን እምብዛም አያስጨንቃቸውም ። በእነርሱ የዋህ አስተያየት አስጨናቂ ነገር የለበትም ። የምትቀናጣ ሚስት መልካም ዱላ ልክ ያስገባታል ። የማይበጅ ባል ራቱ ሽሮ ነው ። የተቀረው መጠበብ ሳይቸግር ጤፍ ብኖር ያሰኛል ።

ደግሞ የአካባቢው ይባስ ። ያላገባ ዱርዬ ነው ። ለትልቅ ኀላፊነት አይገባም ።

አዎ ፣ በያረ ፍትወት ምክንያት የተገኙ ሦስት ማጨቶችና አንዲት ሴት በግቢው የረዳ ወይስ የተረዳ እንበል ? የአስተዳደር ችሎታውን አስመሰከረ ማለት ነው ። አንዲት ከቤቱ አስቀምጦ ሌላ የሚሰርቅ ጨዋ ይባላል ። ጨዋዎች እርስ በርሳቸው ይሰራረቃሉ ። ወንደላጤውን የሚጠሉት የየራሳቸውን እንዳይሰርቃቸው በመፍራት ብቻ ነው ። ሴት አዳሪንስ የሚያደፋፍሩ እነርሱ ሳይሆኑ



ይቀራሉ ? በአንድ በኩል መለወጫ ናቸው ። በሌላው በኩል ደግሞ ፥ እነርሱ ባይኖሩ ወንደላጤው ምን ይበጀው ነበር ። አጥር መዝለል ነዋ !

በቀለ ኮቱን ለበሰና ገንዘቡን እንደ ገና ቈጠረው ። ሕይወት መቼም ንግድ ሆኗል ። መጠጡ ይገዛል ፤ ሌላውም ይገዛል ። የሰብአዊነት አለኝታን መርሳት ብቻ ነው ።

« ደግሞ አልሞከርከም ይለኛል !» አለ ትርጁን በድጋሚ በመስታወቱ እየቃኘ « እግዚአብሔር ያሳያችሁ ፍቅር በሙከራ ይሆናል ? ገበጣ ነው ቤት ተቈጥሮ የሚደረስበት ? በመፈቀር በደለኛ አደረጋት ። ሌላ ለማፍቀር ባለመቻሌ እንደ ጅል ቈጠሩኝ ፤ እስቲ እናንተ አግልክት ብትኖሩ ፍረዱኝ ፥ አይታችሁ ፍረዱብኝ » ።

እግር ከጣለው ሊገባ በራፉን ቈልፎ ወጣ ።

ምዕራፍ ፲ ።

## የጨቤት ጀምበር ።

ነጸነት ተብላ ትጠራለች ። ግን ስም ብቻውን ምን ትርጓሜ አለው ? ። ጽጌ ረዳ በሌላ ስምም ቢሆን መዓዛውንና ውበቱን አይለውጥም ። ስሙ ስሜት የሚሰጠው የባቤቱ ዋጋ በቀደምትነት ሲታወቅ ነው ። ፀቀለ ፥ ከፀ

ሐይ በታች ለርሷ የሚበቃ ስም ፈልጎ አላገኘላትም ። ነጸነት ፤ ቤተ ሰቦቿ ያወጡላት ስም ስለ ሆነ ፣ ብቻ በዚሁ ዘለዓለም ሲጠራት ይኖራል ።

አዎ ! ለርሱ ተፈጥሮውን የሠረፀች ዘለዓለማዊ መንፈስ ናት ። በአካለ ሥጋዋ ሕይወቱን አቋርጣ ያለፈችው ለአጭር ጊዜ ነበር ። ግን ምን ጊዜም የማይደበዝዝ ምልክት ትታበታለች ። ተመልሶ የጥንቱን ሊሆን ከቶ አይችልም ። እንደ ከዋክብት ግጭት የአጋጣሚ ውጤት ነው ? ይህ ከሆነ ፣ ሕይወት ፣ ዓለም ፤ መሠረታዊ ሥርዐት የሌላቸው የዝብርቅርቅ ግጭቶች ድምር ናቸው ማለት ነዋ ! በአጋጣሚ ሒሳብ አንድ ጊዜ የተጋጩ ከዋክብትም ድጋሚ ዕድል እስኪያፈርፅቸው ጐልቂ ዘመናት ያስጠብቃል ። ሰው ደግሞ እንደ ከዋክብት ዘለዓለማዊ ፍጡር አይደለም ። ሰዎች ስለ ሥነ ፍጥረት ሥርዐት ይሰብኩናል ። ሥርዐቱን ለምን በሕይወታችን ላይ አናየውም ? ወይስ ደግሞ የርሱ ድርሻ በላይኛው አእምሮ ተስልቶ የተከናወነ ነበር ? የመንግሥቱ ለማያት ደስታ ፣ የኋለኛው ሕይወት ፣ የፍቅር አምላክ --- ፍቅር ቅኀፀት ከሆነ የፍቅር አምላክ ሕልውና በምን ይመሰከራል ? ወይስ በሰው ነፍስ ይጫወታል ? በቅለ የፍቅርን አምላክ የሚያፈቅርበት ምክንያት አላገኘም ። ሳይጠይቀው የሕይወትን ጸጋ አሳይቶ ነሣው ። በስቃዩ ለማፌዝ ?



በቀለ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሲመራመር በሞከረ ቊጥር የባሰ ግራ ይገባዋል ። ባለፈው ለመኖር የሚችል ይመስል መልካሙን ትዝታ መላልሶ ቢያጠነጥን ይሻለዋል ። ስንት ጊዜ አጠነጠነው ! ሁል ጊዜም የሚነሣው ከመጀመሪያው ቀን ነው ። ሰቀቀኑ ሲያይልበት « ጥፋት እንዳለብኝ ይቅርታ ፤ ንገሪኝ ምንድነው ትዝታ » እያለ ያንጐራጕራል ። ግንኙነታቸው ወይም የሕይወታቸው ግጭት አስደናቂ ተአምር ዐይነት አልነበረም ። ፈተት ያለ የመስከረም ሰኞ ጧት ነበር ። ቢሮትም አይረሳው ። ቢሮው ውስጥ ገብቶ ጥቂት ሲሠራ እንደ ቋየ ወረቀት የሚቈራርጥበት መቀስ አስፈለገውና ወደ ባልንጀራው ክፍል ሄደ ። የተጋጩት ያን ጊዜ ነው ። በክፍሉ ውስጥ ሌላ ሰው አልነበረም ። ከታይፑ ላይ ዘርግታ ጋዜጣ ታነብ ነበር ። እንደ ዋዛ አንድ ጊዜ ቀና ብላ መልሳ አቀረቀረች ። ለቅጽበት ብቻ ነው ያያት ። ግን እንደ አንድ ነገር ሰውነቱ ሲለወጥ ተሰማው ። የመጣበትን መቀስ ትቶ የወረቀት መስፊያ ይዞ እየተደናበረ ወጣ ።

«ማነች እርሷ ? » ሲል ከውጭ ተላላኪውን ጠየቀው።

« አዲሷ ጸሐፊ ናት » አለው ። ሌላ ምን ልትሆን ትችላለች ? አዲስ ጸሐፊ መቀጠሩን ያውቅ ነበር ። ስሞኑን ልጃ ገረዶች እየተመላለሱ ሲፈተኑ እርሱም አንዲት ልጅ አስፈትኖ ነበር ።

ከቢሮው ገብቶ ሲቀመጥ « ቡዶች ! ከየት አባታቸው አገኟት ? » ሲል በሆዱ አምቷል ። ከተዋወቁ በኋላም ስለ አቀጣጠሯ « አሁን ግ- ይሙት በፈተና ከሁሉ በል ጠሽ ነው ? » ብሎ ሲያጫውታት ፤

« በቄንጥ ነዋ ! ብቻ ተጠንቅቀው ያረሙልኝ ወይም ያረሙብኝ አይመስለኝም » ። « እንኳን ግዴለም ። ለዚህ ጊዜ ብቻ ይቅርታ እድርገንላቸዋል » እየተባባሉ በመቀ ለድ ተግሥቀውበታል ።

እንደ ሌሎቹ በሩቅ ለመተዋወቅ ረጅም ጊዜ አል ወሰደበትም ። ያንኑ ቀን ስሟን ያዘ ። ቢሮዋቸው ጐን ለጐን ነበርና እርሷም ብትሆን ፤ የሥራ ጓደኞቹ ከየትም ሆነው « በቀለ - በቄ » እያሉ ሲጠሩት ሳትሰማ አልቀ ረችም ።

ቁም ነገር መጫወት ይወዳል ። ሲፈልግ ቀልድም አይጠፋውም ። ግን ከጓደኞቹ መካከል ስንኳ የቤት ፣ የፓርቲ ፣ የግብረ ሥጋ ጨዋታ የተነሣ እንደ ሆን ከቡ ድኑ ውጭ ይሆናል ። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለ አንዳንድ የዳንስ ውዝዋዜዎች አጥንቶ ነበር ። ሥራ ይዞ ፣ ደሞዝ አግኝቶ እንደ ልቡ ለመጨፈር በሚችልበት ጊዜ ግን ያንኑም ረስቶታል ።

መቼም ሰኞ ጧት የመሥሪያ ቤቱ ጐረምሶች ሥራ ስለ ቤት ጨዋታ ነው ።



« የሳምንቱ መጨረሻ እንዴት ነበር ? » ሲል አንዱ ይጠይቃል ።

« ተወኝ ! ግሩም ነበር ። እንትናን ታውቃት የለም እንዴ ? አንድ ቀን አሳይቻሃለሁ ። ተወኝ ገላ አላት » ብሎ ሌላው ይመልሳል ።

« እኔስ አንዲት ነፍራቃ አምቦ ይዠ ሂጄ ስትነፋ ረቅብኝ ዋለች »

« እኔስ ፍራንክ አልነበረኝም ሲኒማ ገባኋት » ብሎ ሦስተኛው ያማርራል ። ባንደኛው ቢሮ ተሰብስበው ሁሉም ጀብዱን ወይም በደሉን ይተርካል ።

« በቄስ ፤ » ይላል አንደኛው በማፌዝ ።

« ቤተ- ክርስቲያን ሱባኤ ገብቶ ነበራ !» ሲል ሌላው ያዳንቃል ። እንዴ ሲዛበቱበት ተነጥሎ ቢሮው ውስጥ ይዘጋል ። እርሱም ብቻውን ይሥቅባቸዋል - ምን ጊዜ ነው አድገው ቁም ነገር የሚያወጉት ?

ከሴቶችም ጋራ ከዚህ የተሻለ ግንኙነት አልነበረውም።

በጠቅላይ ግዛቱ የመጀመሪያ ደረጃ በኋላም በአ ዲስ አበባ የሁለተኛ ደረጃ አብረው በክፍሉ ውስጥ የተ ቀመጡ ብዙ ልጃ - ገረዶች ያውቃል ። ግን ከአንዳቸ ውም ጋራ የቅርብ ግንኙነት አላበጀም ነበር ።

በኋላም ሥራ ይዞ በአጋጣሚ መንገድ ላይ ሲያገኛ ቸው በተራ ሰላምታ ልውውጥ ይሸኛቸዋል ።

« ኦ ! እንደምነሽ ? » ይላል ።

« እግዚአብሔር ይመስገን ! »

« ጤናሽስ ? »

« በጣም ደኅና ነኝ »

« እሺ በይ እስቲ ! አሁንማ መጠያየቅም ቀረ ! » ከአውቶሞቢሉ ሳይወርድ እጁን ይሰጣል ።

ከዚህም የተነሣ አብረውት በተማሩት ልጃ—ገረዶች መካከል ስሙ በቁልምጫ ተወስቶ አያውቅም ።

« ብጥስጥስ አላለብኝም እንዴ ! » ትላለች አንዷ ።

« እባክሽ ተዪው አጋጣሚ አነጋውና ! » ትላለች ሌላዋ ።

« አይ — ቲንክ አንድ ጉድለት አለበት መሰለኝ » ስትል ሦስተኛዋ በማሰብ ጣቷን ትነክሳለች ።

« ልጆች ! የሴት ዐይነ ጥላ ይዞታል ። » ከብዙ ጊዜ በኋላ ብዙዎቹ የሚያውቁት ልጃ—ገረዶች ይህንን እምነት ሳያጸድቁበት አልቀሩም ።

ግን ዐይነ ጥላ የሚባል ነገር ቢኖር በቀለ የሴትም ሆነ የወንድ ዐይነ ጥላ አልነበረበትም ። አካሉ ሙሉ ፤ አእምሮውም ትክክለኛ ወጣት ነው ። እርግጥ ስለ ሴት እምብዛም አያስብም ። ስለ ሥራው ፡ ስለ ሕይወት ትርጓሜ ፡ ስለ ሀገሩ ዕድል ሌላም ብዙ ብዙ የሚያስበው ነገር አለ ። ካለጊዜው ያረጀ ጐልማሳ ነበር ። ከዚህም



በተቀር ዘወትር በሚሰማው ሐሜት አስተያየቱ ተረት ተም ይሁን በትክክለኛ ምርምር ፈልጎ ፣ ዋጋና ግምት የሚሰጣት ሴት አላገኘም ። ሁሉም ከሚጠብቀው ደረጃ በታች ይሆኑበታል ። ምናልባት ራሱን ከፍ አድርጎ ስለሚገምት ይሆናል ። ትዕቢተኛ አይደለም ። ግን የተፈጥሮ ኩራት አለው ። እንደማንኛውም ጤነኛ ጾታዊ ፍጡር አልፎ አልፎ ፍትወተ ሥጋ ሲነሣበት ከዚሁ ሙያተኞች ይወጣዋል ። ይህም ሲሆን በአድራጎቱ እየተጸየፈ ነው ።

ከመቅጽበት ዐይኑ ሲያርፍባት የሚፈልገውን ዕቃ የምታሳስት ልጅ እነሆ በድንገት ወረደችለት ። በአካል ቅርብ ናት ። ከክፍሉ ሠራተኞች ጋራ ትጫወታለች ። እርሱም አብሮ ይጫወታል ። አንዳንዶቹ ጓደኞቹም ገና ከመጀመሪያው ሳምንት እንሥቶ ! « ነጻነትን እኔ ነኝ የማገባት ። በሞቴ እንጋባ ! » እያሉ መዳራት ጀመሩ ። በቀልዳቸው አብሮ ይሥቃል ። ግን ሆዱ እየተኮማተረበት ነው ። እርሱ ለርሷ የተለየ ፤ እርሷ ለርሱ የተለየች መሆኗን እንዴት አድርጎ ይከሥትላት ? ችግር ነበር ። ከሌሎቹ ነጥላ ልትገምተው አትችልም ። ሁሉም አተኩረው ያዩዋታል ። ልዩነቱ የርሱ ዐይን መነጥር ስለተንጠላጠለበት ብቻ ነው ። ሁሉም ከሌሎቹ ልጃ—ገረዶች ጋራ ይዳለቃሉ ። እርሷስ ከነርሱ መለየቷ በምን ይሰማታል ?

« እስቲ ቴሌፎኑን አዙሪልኝ ! »

« አንድ ፖስታ ላገኝ እችላለሁ ? »

« ጊዜ እንዳለሽ ይህችን ብትመችልኝ - - »

« እንትና የት ሄደ ? » —ምክንያት እየፈጠረና እየፈለገ ወደ ጓደኞቹ ወደ ነጻነት ቢሮ መመላለስ አዘወተረ ፤ ግን ምልልሱ ምንም ያህል አላቀረበውም ። ከቢሮው ተቀምጦ ፣ ሌሎቹ በቀልዳቸው ሲያሥቋትና ሲያውካኩ እየሰማ ጣቱን ይነክሳል ።

« ሁሉንም በጅምላ ነው የሚገምቱት ? ምናምንቴዎች ! » ይላል ብቻውን ።

አንድ ቀን ዕድል ጣለለት ። በስድስት ሰዓት ገደማ ላይ የአዲስ አበባው የመስከረም ሰማይ መጥቆር ጀመረና ለሰባት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ከረጢቱ ተፈታ ። የሆድ ነገር ነውና አንዱ ባለመኪና ሽመልስ ፣ ወረቀት ከጭንቅላቱ ላይ ደፍቶ ዘሎ ገባና እስኪሥቶ ተፈተለከ ። ታደሰም መላጣውን በኮቱ ከድኖ አመለጠ ። በቀለ ግን ሲጋራውን እያቀጣጠለ በቢሮው ውስጥ ሲንቈራጠጥ ቈየ ። ሰባት ሰዓት ከሩብ ላይ ሰማዩ ገለጥ ቢልም ዝናሙ አላባራም ነበር ።

« ልጆች ይህ ዝናም አልተጨማለቀብንም ? » አለ በቀለ ወደ ሌላው ክፍል ገብቶ « መቼስ ጠማችንን አንውል ። ከኔ ጋር ሊዋብ የሚፈልግ አለ ? »



« እየ በቴ ! ካላንት ማን አለን » አለና ተሾመ የተባለው አቀላመጠው ። ነጻነት የዝናሙን ፐላስቲክ ታጠልቅ ነበር ። ወንዶቹ እየተንደረደሩ ሲወጡ አንደኛው ዘወር አለና « ነዪ እንጂ » ሲል ጠራት ።

የተቀመጠችው ከኋለኛው ወንበር ነበር ። በመስታጦቱ በኩል አያት ። እርሷም አይታው እንዳላየች መሰለች ። ሌሎችን ፣ በየተራ ጉዊዶና ቤልትራሜ ጣላቸውና በመጨረሻ ሁለቱ ብቻ ቀሩ ።

« የት ነው ቤትሽ ? » አለና ጠየቃት ።

« አይ ! እኔ ከዚሁ እወርዳለሁ» ብላ መለሰችለት ።

« የት — ነው እኮ ? » ደገመና ጠየቃት ።

« ሾላ ነው ። ብቻ ግዴለም በአውቶቡስ ? ሄዳለሁ ሾላ » አለች ።

እሽታዋን ሳይጠብቅ የሾላውን አውቶቡ፡ መቆሚያ አለፈና ጒዞውን ቀጠለ ። በጒዞአቸው ላይም ሊያጫውታት ሞከረ ። ግን ሰውነቱ ተቅበጥብጦ ስለ ነበር እምብዛም አልሆነለትም ።

« ታዲያ ሥራው ተስማማሽ ? »

« ምንም አይል »

« አይዞሽ ትለምጅዋለሽ ። ለምን ትምህርትሽን አቋረጥሽ ? »

« እንዲሁ » ትከሻዋን ነቅንቅ አደረገች ።

« ትምህርት ይበልጥ ነበር ። ግን ሥራም ቢሆን አይከፋም ። »

ልቡ ሲሙቱ የአዲስ አበባን ሕዝብ የሚያስከትት መሰለው ። ግን በጨዋታው ብዙም ሳይቀርብ ድንገቱ « ከዚያ ላይ ነው የምወርደው » አለችው አንድ ተገን ጣይ መንገድ እያሳየች ።

« ቅርብ ኖሯል » አለ ቶሎ በመድረሱ ቅር እየተሰኘ « የትኛው ነው እርሱ ? »

« ትንሽ ገባ ይላል ብቻ ከዚህ በግሬ እሄዳለሁ » አለችና ለመውጣት ተሰናዳች ።

« መኪና ያስገባ የለም ? » ሲል ጠየቃት ።

« ማስገባትስ ያስገባል ። ግን ግዴለም ። »

« ጭቃ ነው ። በሀገራችንም ሲተረት ከጻድቁ አይቀር --- » ፀረፍተ ነገሩን ሳይጨርስ በሆዱ ተቈረቈረ ። ካልታጣው ቀልድ ብልግናውን ምን አስለደፈው ?

« እግዚአብሔር ይስጥልኝ » ብላ አመሰገነችው ከመኪናው ስትወርድ ።

« ምንም አይደል » ሲል መለሰላት ።

« በጣም ነው ያስቸገርኩት »

ይህችን ያህል ትሕትና ያስፈልጋል ? ብሎ አሰበ ።

ከቤቷ አድርሶ ሲመለስ እሱነቱ በዚህ ዝቅተኛ ዓለም ውስጥ ፣ በዚያ የሚራራጥ ትራፊክ ፣ የሚተርመሰ



መስ ሕዝብ መካከል አልነበረም ። በአንድ የማያውቀው ዓለም ውስጥ የተንሳፈፈ መሰለው ። አሁንም — አሁንም በመኪናው መስታወት በኩል ከራሱ ጋራ እየተፋጠጠ « እሺ በቄ ምን ይመስልሃል ? ተቀፈደድክ ። ታዲያ ምን ትሻለህ ? » እያለ ብቻውን ይጫወታል ። ግን ባርነት መግባቱ አልቈጨውም ። በማንኛውም ዐይነት ነጻነት ያስ እያለው የሚለውጠው ምርጫ ነበር ። ጥንጨ በስውር ጉጠት ወደ ጆሮ ግንዱ የተለጠጠ ይመስል ጥርሱን ለመስከረም ፀሐይ እንዳሰጣ ሆቴል ቤት ደረሰ ። ምግብ አላሰኘውም ነበር ። መብላት ፣ መጠጣት ፣ ምግቡ ባንድ በር ገብቶ ፣ ተለውጦ በሌላ በር ይወጣል ። አንዱን እንወደዋለን ። ሌላውን እንጠየፈዋለን ። እውነተኛው ሕይወት ይህ ነው ? በጣም ሳይበስል ከነደሙ ተጠብሶ ከፊቱ ላይ የተቀመጠውን ቢስቴክ ሲመለከት « ምግብማ ሞልቷል » የሚለው ዘፈን በአሳቡ መጣበት « ዘወትር ብበላ ብጠጣ ምንድን ነው ፣ በእህል ብቻ አልኖርም ሕይወቴ ፍቅር ነው » በሆዱ ያንጐራጕር ጀመር ።

በሆቴሉ ውስጥ አንድ ሐያ ያህል ተመጋቢዎች ነበሩ ። ቦዮቹ « እስፓጌቲ ሱጎቦለኛ ፣ አሮስቶ ቢቴሎ ! » እያሉ ላንቃቸው እስኪነቃ ሲጮሁ የሁሉን ሆድ ድምር አቤቱታ የሚያሰሙ ይመስላል ። ስንቱ ነው

በሆዱ ለሆዱ የሚኖረው ? ስንቱስ ነው ምግቡ የሚስማማው ? ሲል በቀለ አሰበ ። የሰው ስሜት በአበላሉ የሚገለጽ ከሆነ ብዙ ዐይነት ሥዕል አለ ። ከአጠገቡ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠው ጐልማሳ ፣ ችግሩን ፣ ጣጣውን በዓለም ላይ የጠላውን ነገር ሁሉ በሆዱ ውስጥ ለመቅበር የሚፈልግ ይመስል ግንባሩን አኰፋትሮ እስፓጌቲውን እየጠቀለለ ወደ ጕሮሮው ይሰገስገዋል ። ራቅ ብሎ አንድ ሌላ ወጣት ጕማጁን ሥጋ እንደ ጠላት ይቈራርጠዋል ። በስሜቱ ማንን እየተበቀለ ይሆን ? ብቻቸውን ያቀረቀሩ አንድ ጠና ያሉ ሰውዬ የዓሣ እሾህ ይለቅማሉ ። ምን አለፋቸው ? ሰው ፤ ሆነ ብሎ ከእሾህ ጋራ ምን አታገለው ? አራት ዘመናውያን ዛላዎች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ጨዋታውንና ሾርባውን ፣ ቢራውን እያቀላቀሉ ያወርዱታል ። ይገርማል ! አለ በቀለ በሆዱ ፤ ሾርባም መለቃለቂያ ያስፈልገዋል ? ለእነዚህ ጐልማሶች የሕይወት ጣዕም በዚያ ጣሕን ሾርባና በዚያ ብርጭቆ ቢራ ብቻ ተቀምጧል ማለት ነው ። አንዱ ማዕዘኑን ይዞ በአስደናቂ ጥንቃቄ ሙዝ ይልጣል ። አያያዙ ጥበብ አለበት ። የበቀለ አስተያየት ግን በተለይ ያረፈው በሁለት ፍቅረኞች ላይ ነበር ። በዚህ የቅባትና የክብካቤ ዘመን ፊት ዕድሜን የሚነግር ከሆነ ልጅቱ ወደ ዐሥራ ዘጠኝ ፣ ወጣቱ ወደ ሐያ ስምንት ዓመት እንደሚሆናቸው ገመተ ። እንገታ



ቸውን አቀርቅረው ይንሾካሾካሉ ። በእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር ፈገግ እያሉ ይተያያሉ ። ለእነዚህ ፍቅረኞች ከፊታቸው የተደረደረው ድንችና ሥጋ ፣ ትርፍ ነገር ነው ። እርሱስ ሙቼ ይሆን ከነጻነት ፊት እንደዚህ ቁጭ ብሎ የሚጫወቱት ? መንፈሱ ተራበ ። ሆዱ ግን ለምግብ አልጓጓም ።

« አልጣፈጠዎትም እንዴ ? » ብሎ ቦዩ ጠየቀው ። ከሳሕኑ ላይ እንዳለ የቀረውን ምግብ እየተመለከተና ሒሳቡን እያነሣ ፤

« የለም ! ጥሩ ነበር » አለ በቀለ ። አለመከፋቱንም ለመግለጥ ስሙኒ ጉርሻ ሰጥቶት ወጣ ። አውቶቡስ ስትጠብቅ እንደሚያገኛት በመገመት በዘጠኝ ሰዓት ላይ ሂዶ ሊያመጣት አስቦ ነበር ። ግን በቅሌት ትታዘበኛለች ብሎ ተወው ።

የአዲስ አበባ ዝናም የሕይወት ዕድሉን የሚወስን ሆኖ በቀለ የተሰማው በዚያን ጊዜ ነበር ። እንደማንኛውም ከተማ አደግ ወጣት ቢዘንም ባይዘንም ደንታ አልነበረውም ። እንዲያውም ከዚያ በፊት ዝናም ባካፋ ቍጥር ጥላ ሳይዙ አውቶቡስ ለሚጠብቁት ፤ መንገድ ዳር ይዘው ሲጓዙ የጐርፍ ውሃ ለሚረጫቸው መንገደኞች ከፉኛ ያዝን ነበር ። አሁን ግን ዝናም አስፈለገው ። « በሏ ልጆች ! ሙቼስ እንደፈረደብኝ » በማለት ነጻነትን

ለማድረስ ፤ ለመቅረብ እንዲችል መዝነብ ነበረበት ። ይህ የሱ ፍላጎት ነው ። ተፈጥሮ ደግሞ የራሱን ሥር ዐት ይከተላል ። ሁለቱ ዘወትር አልተባበሩም ። ብቻ አንድ ቀን ጥሩ ዘነበለት ።

የጀመረው በዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ከቢሮ ከመውጣታቸው ትንሽ ቀደም ብሎ ነበር ። የምኒልክን ሆስፒታል አልፈው ወደ እንግሊዝ በር ሲጠጉ መዓቱን ያወርደው ገባ። የመስከረሙ ዝናም እንደ ጥይት መኪናውን በኀይል ይመታዋል ። አስፋልቱ መንገድና የእግረኛው መተላለፊያ በጐርፍ ተጥለቅለቀ ፤ ዝናሙ ነጐድጓድ እያደባለቀ ጉልቄ መሳፍርት እንደ ሌለው ጅራፍ ወደ ታች ሲወረወር ፣ ሰማይ ተቈጥቶ መሬትን የሚገርፍ ይመስል ነበር ። የሚንቀሳቀስም እግረኛ የለም ። አንዳንድ ሰዎች በየዛኒጋባው ተዛንበ ተጠግተዋል ። ብዙ ተሽከርካሪዎች አይተላለፉም ። ጐርፉን እየሠነጠቁ ያዘግሙ የነበሩት ጥቂት አውቶሞቢሎችም በመጨረሻ የመንገዱን ከፈፍ እየያዙ ቆሙ ።

« አቤት ጌታዬ መዓቱን አላወረደውም እንዴ ! » አለ በቀለ ። ፍሬን ይዞ ማርሹን አወለቀና ሞተሩን አጥፍቶ ተዝናንቶ ተቀመጠ ። ምሽቱ ድግዝግዝ ብሏል ። የቀረውንም ብርሃን የዝናሙና የጭፍናው ግድግዳ ጋርዶት ከውጭ በኩል ከጥቂት ሜትር ርቀት በላይ ምንም ነገር አይታይም ። ከውስጥ በኩል የአውቶሞቢሉ መስታወት በትንፋሻቸው መወለብ ጀምሯል ። ሙቀት ይሰማል ። ዝናሙ የአውቶሞቢሏን ጣራ ሲደበድበው ጩኸቱ ጆሮ ያደነቍራል ። በዚህ የተፈጥሮ ማዕበል መካከል የበቀለ መንፈስ ፍጹም ጸጥታና እርጋታ ተሰማው ። ሰማይ ተገርድሶ ቢወድቅ ደንታ አልነበረውም ። ከውጪኛው ዓለም በመጋረድ እንደዚህ ሲቀራረቡ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ።

ከጥቂት ጸጥታ በኋላ ነጻነት « እጭ እቴ ! ምን መከራ ነው እባካችሁ » አለችና አገጩን በመዳፏ አስደግፋ አቀረቀረች ። በኤሌትሪኩ መብራትና ከምሽቱ ወጋገን ድብዝዝ ብሎ በገባው ብርሃን የፊቷን ቅርጽ አተኩሮ አስተዋለው ። ውበቷ የት ላይ እንደ ሆነ ለማወቅ መሞከሩ ነበር ። ግን ይህ ነው ብሎ መጠቆም አልቻለም ። ጐረድ ያለው አፍንጫዋ ? ወደ ጠይምነት መለስ ያለው ደም ግባቷ ? ደጐስ ያለው ከንፈር ? ፊቷ ከበድ ያለ ነው ? ወይስ ከቆዳ በታች የሠረጸ ውበት ነው ? — እኔ አላውቅም ። የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ቴያትር የቁንጅና ውድድር ዳኞች ምሥጢሩን ይንገሩኝ አለ በሆዱ ። እነርሱ በሜትር ነው የሚለኩት ። የጣቷን ቀለበት ያየው ያን ጊዜ ነው ። የመጥፎ ዕድል ጨለማ ኮከብ መስሎ ታየው ።

« ቀለበት አሰረሻል እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ።

« አይ ! የሰው ነው ። ወርቅ ሠሪ ቤት ወስጄ ላስጠብበው ነው » አለችና እንደ ዋዛ እጅዋን ቀና አድርጋ ቀለበቱን አሻሸችው ። መልሷን አላመነም ። በጣቷ ተለክቶ መሠራቱ ያስታውቃል ። በተቻለ መጠን ሽምቅቅ ብላ ተቀመጠችና በርሷ በኩል ውጪውን ትመለከት ጀመር ። ፍርሀት ነው ? ዐይነ አፋርነት ?

« አልበዛም እትየ ! » አላት በሆዱ ።

« አሁን ብስማትስ ? — ወይድ ርኩስ ! » ብሎ ራሱን ሲደበው ። « እወድሻለሁ ብላትስ ? ቅሌት ነው ። ;ታሾፍብኛለች » ሲል አሰበ ። ፍቅር በረከሰበት ፤ ሴት በቁና በሚሰፈርበት ዘመን ከልብ ፍቅር ይዞኛል ማለት ጅል እያሰመሰልም ? እውነት ነጻነት ፍቅር ይዞኛል ካንቿ ! እርሱን ተወው ! ጉረኛ ! ነጽየ የኔ ናት ! እውን ነጹ ?» ይባባላሉ ሌሎቹ የቢሮው ጐረምሶች ።

ብዙ ቈይተው በመጨረሻ « ነፃነት » አለ በጣም በለሰለሰ አንደበት ። አነጋገሩ ፡ ጥሪ ፣ ጥያቄም ልመናም ዐይነት ነበር ።

ከሐሳብ እንቅልፍ ድንገት የተቀሰቀሰች ይመስል ወደርሱ ፊቷን መለስ አደረገች ። « አቤት ምንድነው ? » ብላ ጠየቀች ። የርሷም ድምፅ ደከም ያለ ነበር ። የጥሪ መልስ እንጂ ጥያቄ አልነበረም ።



« ምንም አይደል » አለና አውቶሞቢሏን አስነሥቶ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። እንዳስተያየቷ ጭንቀቱ የገባት መሰለው ። አንዳንድ ጊዜ-ኮ ዝምታም ብዙ ይናገራል ። ስሚን ጠርቶ ምንም አይደል ሲል ሊገልጸው ያልቻለ ነገር መኖሩ ያስታውቅ ነበር ። ምንም እንኳ ሁለቱም በግልጽ ባይጨዋወቱትም በመካከላቸው የሐሳብ ግንኙነት የተመሠረተው በዚያን ጊዜ ነው ።

ፊተት ያለ ምሽት ነበር ። ቀላል አየር ይነፍሳል ። ጀምበሯ ጠልቃለች ። ብቻ በምዕራብ በኩል ሰማዩን ድብዝዝ ያለ ቅላት እንደ ሸፈነው ነው ። በቀለና ነጻነት ከእንጦጦ ጋራ ላይ ከአውቶሞቢል ውስጥ ሆነው አዲስ አበባን ቍልቍል ይመለከታሉ ። በሩቁ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ከምልክቱና ከመብራቱ ጋራ እሳት የተለቀቀበት መንደር ይመስል ሲንቦገቦግ ይታያል ። ከመካከል የአፍሪቃ አዳራሽ ከግርማው ጋራ ጐላ ብሎ ይታያል ። የጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ፣ ፒያሳን ፣ አዲሱ ከተማን በአቅራቢያ መለየት ይቻላል ። ሌላው ተንቀሳቃሽ ዝርዝር ነገር ግን በርቀትና በጨለማ ተሸፍኗል ። አዲስ አበባ ስንቱን ጉድ በሆድ ዕቃው ይዞታል ? ሃምሳ ሺሕ ሴትኛ አዳሪዎች ፡ ሐያ ሺሕ መጠጥ ቤቶች ፡ ስንቱ ይሰክራል ? ስንቱ ለማኝ በዐደባባይ ወድቋል ? እነዚያ ደሳሳ ጐጆዎች ሁሉ በዚህ ጊዜ አይታዩም ። አዲስ

አበባ በምሽት እንጦጦ ላይ የሚያስደንቅ አንጸባራቂ ውበት አላት ። ከዋክብቶች የረገፉበት ሜዳ ትመስላለች ። ሙሉዋ ጨረቃም እንደ በቀለና እንደ ነጻነት አዲስ አበባን ቁልቁል የምትመለከት ትመስላለች ። ለፍቅረኞች ወይም ለአፍቃሪዎች ለመሣቅም ፡ ለማልቀስም ተስማሚ ጊዜ ነበር ።

« ግሩም ነው እንዴት ያምራል ! » አለች ነጻነት በአድናቆት ።

« ልጅ ሆኜ የማደንቃትና የማፈቅራት ፣ ከድንጋይ ላይም ተጉልቼ ሳስተውላት የማመሽ ያችን ጨረቃ ነበር ። » በቀለ በጣቱ ጠቆመ « ዛሬ ደግሞ » አለና ፊቷን በእጁ ወደርሱ መልሶ « አይቼ የማልጠግባት የኔ ጨረቃ » ፈዞ አስተዋላት ።

« ምንድን ነው ሰውን እንደዚህ ማየት ! » አለች በቀለድ ቍጣ ግንባሯን ኮፍተር አድርጋ « ሰው ቢያዩት ዝንጀሮ ነው ። »

« አላውቅም » አለ በቀለ አሁንም ዐይኑን ከፊቷ ሳያጥፍ « የጨረቃ ውበት የት ላይ ነው ? የአንቺም እንደዚሁ ነው ነጻነት ። ደግሞ የሚገርመኝ ነገር አለ ። ይህን ያህል ሳፈቅርሽ ፍትወተ ሥጋ አያቅበጠብጠኝም ። ሳይሽ በአቅራቢያሽ ስሆን ብቻ አንድ ዐይነት የመንፈስ እርካታ ይሰማኛል ። »



እንገቷን ደፋ አድርጋ ከአዳመጠችው በኋላ ገጥታዋ ወደ ትካዜ ተለወጠ ። ትንሽ ቈይቶ በዐይኗ ፅንባ ችፍፍ አለ ።

« ምን ሆንሽ ነጻነት ? » ሲል ጠየቃት ።

« ምንም » አለችው አንገቷን እንደ ደፋች ።

በተረብና በጨዋታ ሊያሣሥቃት ሞከረ ። ግን አል ሆነለትም ። በመጨረሻ መቻል ቢያቅተው «እኮ ምን ሆንሻል ? » ሲል ምርር አድርጎ ጠየቃት ።

« ምንም አልሆንኩ አልኩህ ! » አነጋገርዋ ቈጣ ያለ ነበር ።

በቀለ ሲጋራ አወጣና አቀጣጠለ ። « የማየውን ነገር ብታስተባብይኝ አይ፤ባኝም » እራሱን ነቀነቀ ። «ነጻነት — ነጻነት ። አስከፋሁሽ ? አስቆጣርኩሽ ? ይታወቀኛል ፤ መንቻካ አፍቃሪ ነኝ ። » ከርስዋ ሳይሆን ከአሳቡ ጋራ የሚነጋገር ይመስል ነበር ።

« ለምን የባሰውን ታሠቃየኛለህ ! አንተ ምን በደልከኝ አልኩህ » ከትከሻው ላይ ተደግፋ ዕንባዋን ታዝረከርከው ጀመር ። ከዚያም መሐረሟን አውጥታ ጠራረገችና ቀና ብላ ፊቱን በጥያቄ እየቃኘች « እንደ ሌሎቹ ብትሆን ግዴለኝም ነበረ በቀለ ። ግን ልዩ ስለ ሆንክ

እውነት አትመስለኝም ። ይህ ግሩም ፍቅራችን ቅዠት እንዳይሆን በጣም እፈራለሁ ። አንዳንድ ጊዜ ለመሸሽም የቃጣሁበት ጊዜ አለ ። ውብ መሆኑ ብቻ በጣም ያስጨንቀኛል ። ጥሩ ሕልም አይቶ ሲነቁ ከመሳቀቅ ፣ ከነጭራሹ አለማለም ይሻላል ። በቅዬ ! » በዐይኗ ተማጠነችው ።

ጭንቀቷ ገባው ። « ግን-ኮ ውብ መሆኑን ካወቅን ይኸው ይበቃል ነጻነት ! » እነጋገሩ እሹሩሩ ነበር « ይህ የምናየው አዲስ አበባ እውነት ነው ። ዳስሽኝ ፣ ጨብጭኝ --- እኔ እውነት ነኝ --- አንቺም እውነት ነሽ ፤ ቅዠትስ ፤ ቅዠት ይሆናል ብለሽ ማሰብሽ ነው » አላት ።

« ውበቱን -ኮ እኛ ነን የፈጠርነው »

« እኛ የፈጠርነው ዓለም ውብ ከሆነ ሌላ ምን ፈለግን ? ሌላው የፈለገውን ይሁን ! » ሳይነጋገሩ እንደዚሁ ለብዙ ጊዜ ተቀመጡ ። ከዚያም ጭንቅላታቸውን አንተራርሰው ራሳቸው በፈጠሩት ዓለም ውስጥ ረክተው በቀስታ አነዳድ ወደ ከተማ ተመለሱ ። የራሳቸው ዓለም ከሌላው ሊከልላቸው እንደማይችል አላሰቡም ። ወይም በቀለ ሊያስበው አልፈለገም ነበር ።



ምዕራፍ ፫ ።

## የ ቢ ሮ ጭ ጋ ግ ።

በቀለና ነፃነት በራሳቸው ዓለም ውስጥ ተከልለው ለመኖር አለመቻላቸውን ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አልፈጀባቸውም ። በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ አምስት “ ልጃገረድ ” ጸሐፊዎችና ዐሥራ አራት ወንድ ሠራተኞች ነበሩ። ከጥቂቶች ሽማግሌዎችና አዛውንት ባለትዳሮች በተቀር ሁሉም ጐልማሶችና ኮረዶች ናቸው ። ከቢሮ ጸሐፊ ሌላም የሚፈለግ ሙያ አለ—ሴትነት ። በእንደዚህ ያለ አካባቢ ውስጥ ቁርሾ መፈጠሩ የማይቀር ነው ። ሴቶች በቀላሉ ይኳረፋሉ ። ወንዶቹ ቱግ ቱግ ይልባቸዋል ። አሉባልታው ሽሙጡ ፤ በዚያው ልክ ነው ። በበቀለ መሥሪያ ቤት ነገሩ እስከዚህ የናረ መስሎ ባይታይም አልፎ አልፎ ጾጥታው ይደፈርስ ነው ።

በቀለ ቁልቢ ደርሶ በተመለሰ ሰሞን—ስለት አልነበረውም—ሦስት ከሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የተመረጡ ሹማምንት ፣ የክፍሉ የበላይ ሹም አቶ ጢፌና እርሱ የዘገየንና የዓለሙን ጠብ ለመመልከት ከሰዓት በኋላ ኮሚቴ

ተቀመጡ ። ለኮሚቴው የተመረጠበት ምክንያት መጀመሪያ አልገባውም ነበር ።

አቶ ጤፉ መነጽራቸውን አስተካከሉና ፋይላቸውን ያገላብጡ ጀመር ። « እንደምታውቂት » አሉ « ዘገየ ከሆስፒታል ገና አልወጣም ። ቊስሉ ብርቱ ነው ተብሏል ። ዓለሙ ለጊዜው በዋስ ቢለቀቅም ዘገየ ፍርድ ቤት መሄዱ አይቀርም ። ከሁሉም የሚከፋው የመሥሪያ ቤታችን ስም መጥፋት ነው ። ቢቻል እንዲታረቁ እናደርጋለን ። ባይቻልም ወደ ፊት በመሥሪያ ቤታችን ውስጥ እንዳይደገም የነገሩን መነሻ ማጣራትና አጥፊውን ማወቅ ይኖርብናል »

ቃጭል ደወሉና ዘበኛውን አዛለችን ጥራት አሉት ። እየተሽኮረመመች ገባች ።

« ጠቡ ሲነሣ ስለ ነበርሽ ነገሩን አሳምረሽ ታውቂያለሽ ። በይ ንገሪን » አሉ አቶ ጤፉ ።

« ምኑን ? » ስትል አንገቷን እንዳቀረቀረች ጠየቀች ።

« ቁጭ በይ ። ዘገየና ዓለሙ የተጣሉበትን »

« እንዲሁ ነው የተጣሉት »

« እንዲሁ ከመሬት ተነሥተው አልተደባደቡም ። ማለቴ ነገሩ የተነሣው እንዴት ነው ? » አቶ ጤፉ መንገሪያ ሰጧት ።

« በመጀመሪያ አቶ ዘገየ አንድ የሚጻፍ ደብዳቤ አመጣና ለነጻነት ሰጣት ። በኋላ ደግሞ ዓለሙ ሌላ ጽሑፍ አምጥቶ የሚያስቸኩል ነውና ቶሎ ምችልኝ አላት » ንግግሯን አቋረጠች ።

« በኋላስ ? »

« በኋላ አቶ ዘገየ መጡና ለምን መጀመሪያ የሰጠሁሽን የኔን አስቀምጠሽ የሌላ ትጽፊያለሽ ብለው ሲቈጡ አቶ ዓለሙ ሰሙና ያዘዝኳት እኔ ! ለምን ትቈጣታለህ አሏቸው ። ከዚያም አንድ አንድ ሲባባሉ ቈዩና አቶ ዘገየ አቶ ዓለሙን ሌላ ቦታ ታቅፈሀት ዞር ። ይህ ግን መሥሪያ ቤት ነው ! ሲሏቸው ድብድብ ጀመሩ ። »

« እሺ » አሉ አንደኛው የኮሚቴ አባል ።

« ይኸው ነው » አለች አዛለች ።

« ዓለሙና ነጻነት ምን ግንኙነት እንዳላቸው ታውቂያለሽ ? » ሲሉ አቶ ጤፉ ጠየቋት ።

« የዘገየን አስቀምጣ የዓለሙን በመጀመሪያ ለምን ጻፈች ? »

« እኔ እንጃ ! »

« በሥራ መደባችሁ መሠረት አንቺ የምትሠሪው የዓለሙን ሲሆን ! ለዘገየ ደግሞ ነጻነት ናት ። እንዴት ነው የተቀያየራችሁት ? » ሲሉ አቶ ጤፉ መልሰው ጠየቋት ።

« አቶ ዓለሙ ብዙ ጊዜ እንዲሁ ያደርጋሉ »
ስትል መለሰች ።

በቀለ የሴራው አዝማሚያ ገባው ። ማነው ሴረኛ ?
ሴራውስ በማን ላይ ነው ? ከመቅጽበት በአእምሮው
ነገሩን ሊተረትረው ሞከረ ። ባንድ በኩል አዛለች ዓለ
ሙን ለመበቀል ያደረገችው ሊሆን ይችላል ። አንድ ጊዜ
አፍላ ወዳጁ ነበረች ። አሁን ግን ችላ ወደ ማለቱ ነው ።
ሴቶች ይህ የማይወጡት ሽንፈት ነው ። ሀልዎናቸውን
ለማስታወቅ ያገኙትን ይሰነዝራሉ ። በእርሱም ላይ ቢሆን
ቴም አላት ። አንድ ቀን የጻፈችለትን ደብዳቤ ሲያነብ
ከቢሮዋቸው በራፍ አውቶሞቢሎች ተጋጭተው « ውይ
በቅዬ ! » ብላ ከአንገቱ ተጠምጥማ ከንፈሯን ፈርቅዳ
ስትጋብዘው « አሁን እኮ አደጋው አልፏል » በማለት
እጅዋን ፈርቅቆ ሲያስለቅቅ ከፊቷ ላይ ያነበበውን
ቁጭት ከቶ አይረሳውም ። ከቢሮው ተፈናጥራ ስትወጣ
ከዐይኗ ላይ የጥላቻ እሳት የሚታጠል ይመስል ነበር ።
ወይስ የአቶ ጢፌ ሴራ ይሆን ? በማን ላይ ? በነፃነት ?

በቀለ አንድ ሐሳብ መጣበት ፤ « ጽሑፉ እንግሊዝኛ
አይደል የነበረው ? » ሲል ጠየቃት ። አዛለች ትምህርቷን
ከሁለተኛ ክፍል አቋርጣ ፤ በአሻሻጭነት አራት ዓመት
ያህል ሠልጥና በደንበኞቿ በኩል አንድ ቀን ራሷን
የቢሮ ጸሐፊ ያደረገች ሙሉ ናት ። የምትውለው ከአ



ለቆች ጋራ ስለ ሆነ ፤ የጸሐፊዎቹ ሁሉ አለቃ ልሁን
ትላለች ። ችግሩ በእንግሊዝኛ አንዲት መሥመር መም
ታት አትችልም ።

ዓለሙ ደብዳቤውን ለነጻነት የሰጠበት ምክንያት
ለበቀለ ይገባዋል ።

« አዎ » ብላ አዛለች መለሰች ።

« ታዲያ አንቺ እንግሊዝኛ አትችዪ ? » ሲል በማ
ሾፍ መልሶ ጠየቃት ።

« አሁን እያቅተኝም » አለች ።

« በይ ይበቃሻል ። ወደ ቢሮሽ ተመለሽ » ሲሉ አቶ
ጢፌ መስቀልኛውን ክርክር አቋረጡት ።

« ወንዶቹ እኮ ምን አጠፉ ? ዐይን እያዩ ነው የሚ
ቀርቡት » አሉና ጢፌ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

በቀለ ሰውነቱን ከውስጥ እሳት የወረረው መሰለው ።
እሃ ! - ነገሩ በነጻነት ላይ ነው ። ምን አደረገቻቸው ?
ለሞላው ! ሴት እንአዛለች ለመቶም ይበቃሉ ።

« እኮ ታዲያ ነገሩን በበለጠ ለማጣራት እርሷ ለምን
ቀርባ አትጠየቅም » ሲል ሐሳብ አቀረበ ። ነጻነትን
ማለቱ ነው ።

« የሚያስፈልግ አይመስለኝም ። ቢሆንስ እርሷ
ልታምን ኖራለች ! » ብለው ዘጉበት ። በቀለ በልቡ የም
ሬት ሣቅ ሣቀ ፤ በኮሚቴውስ ያስቀመጡት ዐውቀው ሊያ

ፈዘበት ሳይሆን ይቀራል ? አስቸኳይ ቀጠሮ እንዳለ በት ይቅርታ በመጠየቅ ስብሰባውን አቋርጦ ወጣ ። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ከመኪናው ውስጥ ሆኖ ነጻነትን ጠበቃት ። አልመጣችም ። ተኩል አለፈ ። ሰውነቱ እንደ መንዘፍዘፍ ይቃጣው ጀመር ። ምን ነካት ? በመጨረሻ ለአንድ ሰዓት ዐሥር ጉዳይ ያህል ሲሆን እየተወራጨች መጣች ። ከአንድ ጭራቅ የምትሸሽ ትመስላለች ። ዐይኗን አፍጥጣ ፥ ከንፈሯን ገርበብ አድርጋ ድርቅ ብላ ቁጭ አለች ።

« እንዴ ! እንዴ ! » አለች ከጊዜ በኋላ ። የድንጋጤም የመገረምም ነበር ።

አሁንም ቁይታ ቁይታ « እንዴ ! እንዴ ለጉድ አይደለም እንዴ ! » አለች ። በቀለ የሚናገረውን አጣ ። ከበድንነቷ ስትነቃ አፏን ነቅነቅ አደረገችና « ወይ የሰው ነገር ! » በመገረም ሣቅ አለች ።

« ማነው እሱ ? »

« አቶ ጤፉ ናቸዋ »

« ምን አደረጉሽ ? ምን አደረጓት ? እንደ ወረቀት ነው የምበጫጭቃቸው » ብሎ በልቡ ዛተ ።

« ምንም አላደረጉኝም »

« ታዲያ ምንድነው እንደዚህ ያንቀጠቀጠሽ ? »

« ታሪኩን ብነግርህ ኮ »



« ከፈቀድሽ ልስማው »

« በዐሥራ ሁለት ሰዓት ሠራተኞቹ ሲወጡ ፥ ለሥራ እፈልግሻለሁ ብለው እቢሮቸው ድረስ አስጠሩኝ ከዚያም ገባሁና እንደ ቆምኩ ከሳሎኑ እንድቀመጥ ጋብዘውኝ አንቺ ልጅ አስቸግረሽን ቀረሽ አይደለ ! አሉኝ ። ምን አስቸገርኩ አልኳቸው ። « ታውቂው የለም » አሉ ። አሁን በሠራተኞቻችን ላይ የፈጠርሽው መዘዝ ከሥራ ሊያስወጣሽ ይችላል ። እኔ ግን ፋይሉን እሠርዝልሻለሁ ። ብለው ወደኔ ሲጠጉ ከተቀመጥኩበት ተነሣሁ ፤ እንድቀመጥ መልሰው አዘዙኝ ። ከዚያም እንደምታውቂው የደመወዝ ድልደላው ጊዜ ተቃርቧል ። አሁንስ አልዘልሽም ፤ በኔ ይሁንብሽ ፤ በፊትም ቢሆን አንችው ነሽ ” ብለው በድንገት ከአንገቴ ላይ ተጠመጠሙ ። ስተናነቃቸው ጊዜ ለቀቅ አደረጉኝና ምነው ልጄ እስከዚህ ፈራሽኝ ወይስ ንቀት ነው ? ፀጉሬን አትይ ። ሰውነቴ ጉልማሳ ነው ፤ እረ ማንንም ጉረምሳ አስንቃለሁ ! ባታውቂኝ ነው ነጻነት ። ደግሞ ስለ ልጅም ሆነ ስለ ሌላ ምንም የሚያሠጋሽ ነገር የለም ። አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ እናደርጋለን ብለው አሁንም እንደ ገና ክንዴን ለቀም አደረጉኝ ። ኡኡኡ እላለሁ ብዬ በማስፈራራት ነጥቄያቸው ስወጣ ፥ ግዴለም ቆይ ! ከማንም ጨምላቃ ጉረምሳ ጋራ ስትጨማለቂ ግን — ብለው ሲሳደቡ ሰማኋ

ቸው ። » ታሪኳን ስትጨርስ በሰፊው ተንፍሳ አሁንም እንደ ገና ነገሩ አሣቃት ። በቀለ ግን አፉን መሮት ነበር ። አቶ ጧፌ ጥንቃቄ ማድረግ የጀመሩት ወይኒቱ የተባለ ችው ሥራ በጀመረች በአምስት ወር ሆዷ ተቀብዶ ከሥራ ከጠፋች በኋላ መሆን አለበት ሲል አሰበ ። ጥቂት እንደ ተንሸራሸሩ « ወንድ አስጠላኝ ልጄ » አለች እንደ ዋዛ ።

« እኔንም ጭምር » ሲል ጠየቃት ።

« አንተም እንደ ሌሎቹ ወንዶች ትሆን !» ብላ ራሷን መልሳ ጠየቀችው ። ከጥያቄም ይልቅ የጥርጣሬ አነጋ ገር ነበር ።

« ወንድ ነኝ ! ሥጋ የለበሰ ወንድ መሆኔን ዐውቀሽ መቀበል አለብሽ ። ግን ራሴን ማመስገን አይሁንብኝና ከሌሎቹ ትንሽ ጠፈፍ ያልኩ ነኝ ለማለት እደፍራለሁ » አለና መለሰላት ።

ይህ በሆነ ከአንድ ወር በኋላ ነጻነት ሌላ ሥራ ፈልጋ—ፈልገ—ውመሥሪያ ቤቱን ለቀቀች ። ከሁለት ወር በኋላ ደግሞ ራሱ መዛወር አልቀረለትም ። የዚያው ተመሳሳይ ሤራ ድጋሚ ነበር ።

ተላላኪው ሰዎች ይፈልግዎታል ብሎ ሲነግረው በቀለ አቀርቅሮ ሥራውን ያከናውን ነበር ። ሲወጣ ሁለት



ደንበኛ ፖሊሶችና አንድ ሲቪል የለበሰ ነጭ ለባሽ ሆነው አገኛቸው ።

« አቶ በቀለ እርስዎ ነዎት ጌታዬ ? » ሲል ሲቪል የለበሰው ጠየቀ ። በቀለ በአዎንታ ራሱን አወዛወዘ ።

« ወንጀለኛ ምርመራ ድረስ ይፈለጋሉ ። » ወንጀለኛ ምርመራ ? ለምን ? ፖሊስ ጣቢያንኮ ረግጦት አያው ቅም ። ግንኙነቱ ቢበዛ ከትራፊክ ፖሊስ ጋራ ነበር ።

« እሺ እናንተ ሂዱ ። እኔ በመኪና ከዚያው ድረስ እመጣለሁ » አላቸው ።

« የለም ጌታዬ አብረውን ነው የሚሄዱት » ሲል ሲቪል የለበሰው መለሰ ።

« እሺ በመኪና እንሂድ ! »

« ጭቅጭቅ ባያበዙ ምናለበት ! መኪናዋ አታስፈ ልገንም ። » አሁን አነጋገሩ ቊጣና ትእዛዝ የተቀላቀለ በት ነበር ። እንደ አራዳ ሌባ በፖሊስ ታጅቦ መሄዱ ለበቀለ የመጨረሻው ውርደትና ጥቃት ሆኖ ተሰማው ። ነፍስ ገደልኩ ? ቋንጃ ቈረጥኩ ? ከብት ነዳሁ ? የምትሠሩ ትን አታውቁትም ልበል ? እያለ በሆዱ አመናጨቃቸው ።

የርሱን ፋይል የያዘው መኰንን ለጊዜው አልተገ ኘም ። ተረኛው ፖሊስ ነገ ጧት ይገባሉ ብሎ ነገረው ።

« እኮ ወንጀሌ አይነገረኝም ? » በቀለ በንዴት ደጋ ግሞ ጠየቀ ።

« ጌታዬ ! ቀስ ብለው ይደርሱበት የለ ! አሁን ዐረፍ ቢሉ ሳይሻል ይቀራል ? » የፖሊሱ ማጽናናት ፌዝ ነበረበት ።

« አሆ ! ይገርማል ! በጣም ይገርማል » ሲጋራ በሲጋራ ላይ እያቀጣጠለ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሲንጎራደድ ቈይቶ ታከተውና ከአንዱ ወንበር ላይ ዘፍ አለ ። አንዱ አሳቢ ፖሊስ በአግዳሚ ወንበር ላይ አርጌ ቡትቶና ፍራሽ ዘርግቶ መኝታ አበጀለት ። በቀለ ግን በማመስገን ፈንታ ገርሞት ሣቀ።

ወንጀሉ ምን እንደ ሆነ ሊያስብ ሞከረ ። ስሞኑን ምን ሠርቼ ነበር ? ምን አጥፍቻለሁ ? ቈይ እስቲ ! ምንም ነገር ትዝ አላለውም ። የራሱን ይዞታ ተወውና ስለ ነጻነት ይጨነቅ ገባ ። ስትሠቃይ ነው የምታድር ። የቤት እንጀት ። ያውም የርሷ ለስላሳ እንጀት ።

« እባካችሁ ባይሆን መንደር ሄዳችሁ ልትነግሩልኝ ትችላላችሁ ? » አለና ለመነ ።

« የት ነው ? »

« ሾላ »

« አይ ። ሁሉም ተረኛ ነው »

በአምስት ሰዓት ላይ ሰው ይፈልግሃል ሲባል በቀለ አንድ ፓኬት ሲጋራ አገባዶ ነበር ። ነጻነት ነበረች ።



« ምን አመጣሽ በውድቅት ? በምንስ መጣሽ ? » አጠያየቁ የምክር ቍጣ ነበር ።

« የጎረቤት መኪና ለምኜ » አለችው ፤ በወረቀት የተጠቀለለውን ሳንድዊችና ፓኬት ሲጋራ እየሰጠች ። ያለቀሰችበት ዐይኗ በርበሬ መስሏል ። እንደሠጋው በየፖሊስ ጣቢያው ስትንከራተት አምሽታለች ።

« በቃ ደኅና ነኝ ሂጂ » አላት አሁንም በቊጣ ። በሆዱ ግን ባትለየው በወደደ ነበር ።

በበነጋው ጧት የተባለው መኰንን ሲተካ ስሙንና አድራሻውን መዝግቦ « ይህ የርስዎ አይደለም » ሲል አንድ ብጣሽ ወረቀት ከፋይሉ ውስጥ አውጥቶ አሳየው ። ነው ።

« ጽሑፉም ? »

« አዎ »

« ምስጢሩ ምን እንደ ሆነ ያስረዱናል ? » ሲል መኰንኑ ግንባሩን ወደ ላይ አኰፋትሮ ጠየቀው ። በዚህ ጊዜ ነው በቀለ ጕዳዩ የተገለጠለት ። ጅሎች ! ጅሎች ። መንጋ ጅል ! አለ በሆዱ ። ሣቁ ከውስጥ ይኵረኰረው ጀመር ። ክሱ በዚያ ወረቀት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ለእርግጥ የሚያሥቅ ነበር ።

በቀለ በትምህርት ቤት ሳለ ፤ ከአንድ ጓደኛው ጋራ አኅዝ በማስገባትና ፊደል በማለዋወጥ እንደ ቀልድ

እንድ የምስጢር አጻጻፍ ፈጥረው ነበር ። በድንገት ለሚ
መለከተው ልዩ ኮድ (ምልክት) ይመስላል ። ሁለቱም
ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ ፤ የጥንቱን ጊዜ ለማስታ
ወስም ይሁን ፣ እንዲያው ለጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ በዚሁ
ዐይነት ብዙ ጊዜ ይጻጻፋሉ ። አሁን ለመረጃ የቀረ
በለት ይህ ደብዳቤም ለዚያው ጓደኛው የጻፈለት ነበር ።
በምስጢር መልክቱም የነጻነትን ጉዳይ ተርኮለታል ።
ግን አላከውም ነበር ። ከሰሙኑ በታች ሁለት ቀን እንዳ
ስቀመጠው ፤ በኋላ ቢፈልገው አጥቶታል ። ምናልባት
በስሕተት እቅርጫቱ ውስጥ ተቀላቅሎ ወድቋል በማለት
ችላ ብሎት ነበር ። በማን ተላልፎ ወደ ፖሊስ ቢሮ እንደ
ደረሰ በኋላም ሊያረጋግጠው ያልቻለ ሤራ ነው ። በቀለ
እየማቀና እያፌዘ ነገሩን ለመኰንኑ አስረዳው ።

ሆኖም በሐረር ከተማ ከሚገኘው ጓደኛው ዘንድ
ነገሩን አጣርተው እስኪያረጋግጡ ሁለት ቀን በዚያው
እንደ ታሰረ ሰንብቶ በሦስተኛው ቀን ለማንኛውም ዋስ
አስጠርተው ከይቅርታ ጋራ ሸኙት ።

ቢሮ ተመልሶ ሲገባ “ አሆ ! ኧረ እንኳን ደኅና
መጣህ ! አሁንስ አበዙት ! ” እያሉ ቢቀበሉትም ትዝብ
ታቸው ሲሽማቀቅ ይሰማው ነበር ።

በነርሱ ሐሳብማ ዓለም በቃኝ ከርሞ ነበር ።

« ይህንን መሥሪያ ቤት መልቀቅ አለብኝ » አላት
ለነጻነት በኋላ ።



« ለምን » ስትል ጠየቀችው ።

« ሰው እምብዛም ባልወድም በማንም ላይ ጥላቻ
አርግጬ አላውቅም ነበር ። ታምኛለሽ ? አሁን ግን ፊታ
ቸውን ሳይ ብቻ ሊያስታውከኝ ይቃጣኛል ። በርግጥም
አንድ ቀን ሽንት ቤት ገብቼ አስታውኬአለሁ ። እንዴት
ታዲያ አብሬያቸው ልኖር እችላለሁ ? » አለና መልሶ
ጠየቃት ።

« ሥራው ደኅና ነበር ። በቀለ ፤ በኔ ምክንያት እኮ
ነው ! »

« አንቺ ምን አጠፋሽ ? ሁሉም አንቺን አፈቀሩ »
አላት እንደ ቀልድ ።

« ኧረ ፍቅራቸውን ጅብ ይብላው ! አንተም እን
ዲህ ትላለህ በቀለ ! » ስትል ገሠጸችውና ሌላ ጨዋታ
ጀመሩ ።

ምዕራፍ ፬ ።

## ኮሮ ትርጉም ሲያገኝ ።

እንድ መልካም ዓመት አለፈ ። ዓመት ? ዓመት
ምን ያህል ጊዜ ነው ? ገና መከበሩ ፣ ሁዳዴ መጾሙ ፣
ክረምት ገብቶ መወጣቱ መለኪያ ቢሆን ነው እንጂ
ለበቀለና ለነጻነት በሮ የጠፋ ቅጽበት ብቻ ነበር ።

አዲሱ ሥራው ተስማምቶታል ። የአለቃ ግልምጫ፣ የሥራ ባልደረባ ጉጥጫ፣ የጸሐፊ እሉባልታ የለበትም ። ከሁሉም እርይታ የሰጠው ከጸሐፊው ጋራ ያለው ግን ኙነት ነው ። እበልጅነት ተናሥቷል ። ፈልጎ አይደለም ።

እንደ ተቀጠረ ሰሞን ቅሬት ነበረች ። በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ « ወንድ ልጅ የሆነ እንደሁ ክርስትናውን ሳንተ ስጥቻለሁ » አለችው ።

« ለኔ ? » በመደነቅ ጠየቃት ።

« አለበለዚያስ ለታቦት እሰጠዋለሁ » ስትል ዘጋችበት ። ለምን እንደ መረጠችው ግን ምናልባት ከዚያ በፊት እንደ ዋዛ ሳታጫውተው አልቀረችም ።

« እንዴት ያለ ጠባይ አለህ ? » አለችው አንድ ቀን ።

« በምን ? » ሲል ጠየቃት ።

« ካጋጠሙኝ አለቆች ሁሉ የተለየ ነህ ፤ በመጀመሪያ የምትንቀኝ መስሎኝ ነበር ። በኋላ እንደ ተረዳሁት ግን ሥራንና ጾታን ለይተህ የምትመለከት ይመስለኛል ። » አለችው እንደ ማፈር እየቃጣት ።

« ሌሎቹ አለቆች ምን ይሠራሉ ? » ሲል እንደማያውቅ በፈዝ ጠየቃት ።

« ባክህ ዝም በል » አለችውና ሥራዋን ቀጠለች ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከባለቤቷ ጋራ አስተዋወቀችው ።



መንፈሱ በፈካበት በዚህ ጊዜ መካከል አንድ ቀን ብቻ ጀንበር የጠለቀች መስሎት ነበር ። ከዓመት የረዘመ ቀን ነበር ።

ማታውኑ ከነጸነት ጋራ ተኳርፈው ተለያይተዋል ። በምን እንደ ተኳረፉ በትክክል አያስታውሰውም ። ቀላል ነገር መሆን አለበት ። አልበደላትም ። በእርግጥ አልበደለችውም ። በመኪና ውስጥ ተቀምጠው ደኅና ይጨዋወቱ ነበር ። የማይጥም ቃል ተናገሯት ። ኖሮ ይሆናል ። ምን ነበር እሱ ?

« እንግዲህ አትጨቅጭቀኝ » ብላው ነበር ። ከዚያ በኋላ አልተነጋገሩም ። ፊቷን ወደ ውጭ መልሳ በመስታወቱ የፒያሳን ሱቅ እየተመለከተች በአርምሞ ከቤቷ አደረሳት ።

ለወትሮው እጅዋን በድግ አድርጎ በመሳም « ደኅና እደሪ እሺ ? » ሲል ይሸኛት ነበር ። « አንተም እንዲሁ » ብላው ትገባለች ። በዚያ ማታ ግን ከመኪናው ወጥታ ከፊቱ ስትርቅ አልተሰነባበቱም ። ዞር ብላ ፈገግታዋን አላሳየችውም ነበር ። እርሱም አገጩን ከመሪው ላይ አስደግፎ ጫን ከተነፈሰ በኋላ መኪናውን አዙሮ ተመልሷል ። የተለያዩት እንዲህ ነበር ።

ሌሊቱ የዘለዓለም ጨለማ ሆኖበት አደረ ። እስከ ስድስት ሰዓት ብዐይኑ እንቅልፍ ዝር አላለም ። በሰባት

ትንሽ እንጎላቸ ። በስምንት መልሶ ብንን አለ ። በዐሥር ሰዓት ላይ ደግሞ በውንና በእንቅልፍ መካከል መዋር ቅዠት አስደንግጦታል ።

ጧት እንደተለመደው ሥራ ገባና ቴሌፎኑን ወደ ርሱ ጠጋ አድርጎ ይጠባበቅ ጀመር ። እጆቹ ከጠረጴዛው ላይ የተቈለለውን ፋይል ያገላብጣሉ ። ዐይኖቹ ወረቀቱን አፍጥጠው ይመለከታሉ ። ግን አያነቡም ። አሳቡ አያይም ። መንፈሱ አያይም ።

ሰዓቱን ተመለከተ ። ሦስት ከሩብ ይላል ። እንደሌሊቱ ቀኑም ቆመ ! በሩብ ሰዓት ውስጥ ነገሩ ይለያል ። የዕለቱን ጋዜጣ ሳበና ያነብ ጀመር ። ግን ዐይኑ የሚያየው በቀለም የተጨማለቀ ወረቀት መሆኑን ብቻ ነበር ። እንደ ገና ሰዓቱን ተመለከተ ። ለአራት ሐያ አምስት ጕዳይ ሆኗል ። ጨነቀው ። ተነሣና በክፍሉ ውስጥ ይንቈራጠጥ ገባ ። ከመስኮቱ ወደ በሩ ፤ ከበሩ ወደ መስኮቱ መሄድ ፤ መምጣት ፤ መዞር ፤ መመለስ ፤ ከንፈሩን ይበላል ። ወረቀት እያነሣ ይጥላል ። በመስኮት ወጣ ብሎ ይመለከታል ። አሁንም መልሶ ይንጐራደዳል ።

መልሶ መላልሶ ግን ዐይኑ ከቴሌፎኑ ጭንቅላት ላይ ያርፋል ። አንድ ጊዜ በጆሮው ውስጥ የቴሌፎን ደወል የሰማ መሰሎት ነበር ።

ሆኖም ቈይቶ ቴሌፎኑ በገሃድ ክሊል አለ ።



ጸሐፊ አበልጂ እታገኝ « አቶ ተቅዋመ ይፈልግሃል » አለችና አዛወረችለት ። ተቅዋመ ጓደኛው ነበር ።

« እህ በቁ እንደ ምን አደርክ ? » አለና ጨዋታ ጀመረ ።

« ደኅና ነኝ »

« ታዲያስ ምን ወሬ አለ ? »

« ምንም » አለና ትንሽ ቈይቶ «አሁን ሥራ በዝቶብኛል በኋላ እደውልልሃለሁ » ሲል ዘጋበት ። ምን ወሬ አለ ? ጨዋታ ? እ እ ! ምን ሰው ያስቸግራሉ ? ከመሬት ተነሥቶ ተመረረ ።

እንደ ገና መንጐራደዱን ቀጠለ ። አሁን ግን የጊዜው መርዘምም ሆነ ማጠር አልታወቀውም ። በቈሙተኝቶ ነበር ። በአምስት ሰዓት ላይ መልሶ ነቃ ። አላስችለው አለና ቴሌፎኑን አንሥቶ አዞረ ።

« ገብታለች ? » ሲል ጠየቀ ።

« ላገናኝህ ? » አለችው የመሥሪያ ቤቱ አፕሬተር ።

ግድየለም ተይው አለና ዘጋ ። መግደርደርም ነው ። እርሷ ካልፈቀደች ለምን አስከፋታለሁ የማለትም ነው ። ብቻ ደኅንነቷ አጽናናው ።

« ባታመር ኖሮ እስከ አሁን ትደውል ነበር » አለ ብቻውን እየተንጎራደደ ። የሚያመልካት እርሱ ቢሆንም የርሱ ቴሌፎን ቀጥታ በመሆኑ እንድትደውልለት በቃል

ያልተነጋገሩበት የአሳብ ውለታ ገብተዋል ። በዚሁ መው ረት ሁልጊዜ ጧት ጧት በሦስት ሰዓት ተኩል ላይ ያለማስታጐል ትደውልለት ነበር ። « እንደምን አደርክ ? እንደምን አደርሽ ? » ለመባባል ብቻ ነው እንጂ ብዙም የሚጨዋወቱት ወሬ የለም ። እታገኘ አሁንም ደግማ ሌላ የወንድ ጥሪ አስተላለፈችለት ። ሁለተኛ የለሁም ሲል አዘዛትና ዘጋ ። ትንሽ ቈይታ ደወለችለት ።

« የለሁም አላልኩሽም ? » ሲል ደነፋባት ።

« ዋ ! ብትነጋገር ይሻልሃል ? » ስትል እንደፌዝ ዛተችበት ። ዐወቀ ።

« እንደምን አደርክ ? » ያ የገነት ዜማ መጣለት ።

« ውይ ! ምነው ልጂ ? » አለ ደኅንነቷን ሳይጠይቅ ። የምቀ እፎይታ ነበር ።

« ልቅሶ አርፍጂ በአምስት ሰዓት ገደማ እኮ ነው የገባሁት ። ከዚያም የሚያስቸኩል ደብዳቤ ነበር » ስትል አስረዳችው ።

እታገኘ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ቢሮው ስትገባ ፣ ተዝ ናንቶ ተቀምጦ በፈገግታ ሲጋራ ያጨሳል ።

« ትወዳታለህ አይደል ? » ከቀያቂ ይልቅ መግለጫ ነበር ።

« ማንን ? » ግንባሩን ኮፍተር አድርጎ የማያውቅ መሰለ ።



« ዋና ተግደርዳሪ ነህ ። ጢፍን ለጌኛ አሉ ። ልጂ ቅድምስ በጣም አሲደንግጠኸኝ ነበር » ስትል በእኅት ነት ዐይን ተመለከተችው ።

« ትወዳታለህ አልሽኝ ? ዋዘኛ ጥያቄ ነው ። መል ሱም ቀላል ቃላት ብቻ ነው ። መውደድ አይደለም ታገኘ ። አመልካታለሁ እንጂ ! » ቃላት የማይገልጠው ኑዛዜ ከውስጥ ወደ ላይ ይገፋው ጀመር ።

« ታዲያ ለምን አታገባትም ? » ስትል ጠየቀችው ።

አታገባትም ? ጥያቄው እንደ ጕድ አስገረመው ። ከዚያ በፊት ፈጽሞ ያላሰበው ነገር ነበር ። ወይም ሊያስበው አል ፈለገም ። ነፃነትን እንደ ጣዖት ያመልካታል እንጂ እንደ ሴት በሚስትነት ሊመኛት ሕሊናው አልደፈረለትም ።

« እንጃ ! » አለ ግድግዳውን አፍጥጦ እየተመለከተ። ጥቂት ካሰበ በኋላ « እታገኘ እዚኮ በጓዳ አትወሰንም ። ምሉዕናት ። ያኔ ፍቅርም በባልነት አይከለልም ። የለም ሚስቴ ትሁን ማለት ኀጢአት ይመስለኛል » ።

« እንዴ እውነትም ጕደኛ ነህ » እታገኘ ከትከት ብላ ሣቀችበት ። « ምንድን ነው ኀጢአቱ ? » ባጭሩ የአ ንተ የፍቅር ስሜት የሚያፈቅሩትን አለማግኘት ነው ። ባለማግኘቱ መሠቃየት ነው ። ትንሽ ትንሽ አንብቤአ ለሁ ። ሮማንቲክ ይሉታል ። የለም ! በቀለ ብዙ እያነበ

ብክ ነው መሰለኝ እውነተኛው ዓለም ተማቶብሃል ። እኛ እንደምናውቀው ግን የፍቅር ማሳረጊያው ጋብቻ ነው ። በርጂ በኩል ሆነህ ብትመለከተውስ ? ለፍቅርህ ራስን ለዘለዓለም ከመስጠት የተሻለ ምን መግለጫ አለ ? ካለበለዚያማ ይህ ጸጋ ስትራራቁ ጠፋ ማለት ነው » አለችው ።

« የአንቺ ፍቅር ጋብቻ ሆነሽ ? » ሲል አሾፈባት። አንድ ጊዜ ያጫወተችውን የፍቅራን ወጤት ታሪክ መጥቀሱ ነበር - እታገኝ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን ልትጨርስ ገደማ አንድ ሰው አጫት ። ደኅና ባል የሚሆን ሰው ዐይነት ነው ። እንደ ተሰማትም በጣም ይወዳት ነበር ። እንደዚሁ የሚወደው ወደኮሬያ የዘመተ ትንሽ ወንድም ደግሞ ነበረው ። ቅኑ እጮኛ ለሁለቱ ባለው ፍቅር ፤ ለእርጂ ስለወንድሙ ጀግንነት ፣ ጠባይ መልክ እያሞጋገሰ ይግታታል ። ለወንድሙ በሚልክ ለት ደብዳቤ ሁሉ ደግሞ ፣ ለታገኝ ስላለው ፍቅር ስለ ቍንጅናዋና ስለ ጠባይዋ ይተርክለታል ። በዚህ መካከል ሁለቱም ሳይታወቃቸው አንዱ ስለሌላው በስውር ሕሊናው ፍቅር አርፎባቸዋል ። ከኮሬ ሲመለስ ፤ ከእጮኛዋ ጋራ በባቡር ጣቢያ ሊቀበሉት ወርደው ነበር ። ሁለቱም የሠሩትን አያውቁትም ። ገና ከባቡሩ ብቅ ሲል ከሥጋ ወንድሙ ቀድማ ስትሮጥ ፤ እርሱም እጇን ዘር



ግቶ ሲቀበላት አንድ ሆነ ። እጮኛዋ በመገረም ተመለከታቸው ። ምናልባት ከቶ አላሰበም ። እታገኝ ግን በገቢርም ባይሆን በሐሳብ ማመንዘሯ ሲሰማት እውነተኛ ሚስት ልትሆነው እንደማትችል በመገንዘብ ቀለበቷን መልሳ ከሁለቱም መለያየቱን መረጠች ። ከዚያም ለፍቅር ሳይሆን ለትዳር ስትል ሌላ አግብታ ምስት ወልዳለች ።

« የኔው የተለየ ነው» አለችው ታሪኳን መጥቀሱ እንደ ሆነ ወዲያው ገብቷት ፤

« እባክሽ ሁሉም ያው ነው» አለና መልሶ « ግን እውነቱን ለመናገር ምናልባት ያላሰብኩበት ራሴን ለርጂ የተገባሁ አድርጌ ስለማልገምተው ይሆናል » አሁንም ጣራ ጣራውን እያየ አሰበ ።

« ላንተ ይመስልሃል ። ግን እርቧ ደግሞ ካንተ የተሻለ አታገኝም ይሆናል ። »

« እኔ እንጃ ! » ግራ የሚያጋባ ጥያቄ የቀረበለት መሰለ ።

« ልጇ ራስክን እንኳ ትተማመነው ነበር ። ከርቧ ላይ ስትደርስ ምነው ሐሞትህ ተንጠባጠበ ? » አነጋገሯ የትዝብት ዐይነት ነበር ።

« ደግሞ ኮ ቀለበት አላት » አለ ።

« የምን ቀለበት ? » እታገኘ መብረቅ እንደ ወረደ ያህል ደነገጠች ፤ « በቀለ አንተም እንደ ሌሎቹ ? » እርሱንም አስደነገጠችው ።

« የለም ! አንቺ የምታስቢው ዐይነት አይደለም ። ያጨላት ሳትወድ እየገረፉ ነው ። የባቷን ጠባሳ አሳይታኛለች ። ከመገናኘታችን በፊት አንሥቶ ቀለበቱ እንዲመለስ ከመጠየቅ አልቦዘነችም ። እንዲያውም ሥራ የያዘችበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው ። ራሷን ለመቻል»

« ስለዚህ ? » የእታገኘ ጥያቄ ቀጥል ማለት ነበር ።

« ማለቴ አላጭበረበርነውም ። የርሱ እንዳልሆነች ልቡ ሲያውቀው እንዲሁ ነው እልህ ገትሮ የያዘው » አላት ።

« እንደማታገባው እርግጠኛ ነህ ? » ግንባሯን ክፍተር አድርጋ ጠየቀችው ።

« መቶ በመቶ » ነጻነትን ከራሱ ይበልጥ እንደሚያምኑት ያህል በመልሱ አላመናታም ።

« ይህ ከሆነ ለምን መፍትሔ አንሻለትም ? » ትክብላ አየችው

« ለምሳሌ ? » አላት ።

«ቀለበቱን እንዲመልስ ጠይቀው ። የሁለታችሁ ሕይወት የተቈራኘ መሆኑን አሳምነው »



« ትቃዣለሽ እታገኘ ! » አስገራሚ የሕልም ታሪክ የሰማ መሰለው ።

« ለምን አይቻልም ? » አለች አሁንም በተረጋጋ አነጋገር ። « አንድ ኢትዮጵያዊ አድርጓል አሉ ። እንዲያውም ከተጋቡ በኋላ ነው ። ከመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል ይባላል ። »

በቀለ ሲጋራ አቀጣጠለና በጢሱ ውስጥ ምስጢር የሚሻ ይመስል ጥቂት አሰበ ። ምናልባት ልክ ናት ። ለምን ነጻነትን ማግባት አልፈለግሁም ነበር ? ፈልጌ ነበር ? እርሷን ፈርቼ ነው ? ወይስ ራሴን እፈራዋለሁ ? ናፍቆት ፍቅር ነው ። አለማግኘትም ፍቅር ነው ። ግን ምን ያህል ጊዜ እችለው ነበር ?

« እንሞክረው በመሞከራችን የምንከሥረው ነገር የለም » አለ በመጨረሻ ። በሕይወቱ ላይ አንድ ትልቅ ውሳኔ ማድረጉ ነበር ።

ምዕራፍ ፭ ።

## የብልጥ ብልጥ ።

« ቡና ነው ሻይ ይሻልዎታል ? » አለ በቀለ የቴሌፎኑን ጭንቅላት እያነሣ ። የተዝናና ፣ የተረጋጋ ለመምሰል መሞከሩ ነበር ፤ ግን ሰውነቱ ሲቅበጠበጥ ተሰማው ።

ጀኛነም ይውረድ ! ማነውና እርሱ ! ምንድነውና ! እል
በሆዱ ራሱን ሲያጽናና ። ከጠረጴዛው ተነግና ከእን
ግዳ መቀበያው ፎቴ ላይ ከጉባኑ ፊት ለፊት ተቀመጠ።
በቢሮው ውስጥ እንዲገኝ ለማድረግ ያለ የሌለ ችሎ
ታውን ጠይቆበታል ። ከእታገኙ ጋራ እየተማከረ ያወ
ጡት ፕላን ነበር ። ለነጻነት እምኛ ቀራቢ የሆን !
እርጂም በቅርብ የምታውቀው አንድ ሰው ነበር ። ጉዳ
ዩን ግልጥ አድርገው ነገሩትና በቀለን እንዴት ሲያገኘ
ኘው እንደሚችል ጠየቁት ። ሰውዬው መላ ለመምታት
ጊዜ አልወሰደበትም ። እምኛዋ ሰሙ ተሾመ ይባላል ።
ያለበት ሥራ ስላልተስማማው ሌላ በመፈለግ ላይ ነበር።
በበቀለ መሥሪያ ቤት ክፍት ቦታ እንዳለና እርሱም ሊረ
ዳው እንደሚችል መጠቆም ብቻ ይበቃል ። በሩን አን
ኳኩቶ ራሱ ይመጣል ። ነጻነትን እንዲሰጠው መጠየቅ
እንሶ በውሸት ማታለሉ ድርብ ወንጀል አይሆንም !
በቀለ በመጀመሪያ ሐሳቡን አልወደደውም ነበር ። እታገ
ኙና ሰውዬው ደግሞ በነገር እየተቀባበሉ የምርጫ ካርታ
ውን አቀረቡለት ። ስለ ሕሊናው ጥያቄ በጣም የሚ
ጨነቅ ከሆነ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጐ መተውና
ተአምር እስኪወርድ መጠበቅ ነው ። በቀለ በተአምር
የሚያምን ሰው አይደለም ። ስለዚህም በሐሳባቸው መስ
ማማት ግድ ሆነበት ።



በቀለ ሲጋራ አቀጣጠለና ጉባኑን በጥሞና አስተዋ
ለው ። ተክለ ቁመናው ደኅና ነው ። እንዲያውም ጠፈፍ
ካለው አለባበሱና ደጉስ ካለው አካላቱ ጋራ እርሱ ላይ
ሽል አይቀርም ። ነፃነት ለምን ጠላችው ? ከተፈጥሮው
ውስጥ ተፈጥሮዋ የተጸየፈው ምን ይሆን ? ፍቅርና ጥላቻ
በጣም አስገራሚ ስሜት ነው ። ምንም የሚከተለው
የተፈጥሮ ሕግና ሥርዐት የለውም ። ከዳር ሆነው ቢመ
ለከቱት የሚያሥቅ ጅልነት ይመስላል ! ግን ከውስጡ
ነኛ ! እንዲህ በመሆኑም ደስ ይለኛል ፤ አለ በቀለ በሐ
ሳቡ ።

ቡናው መጣ ። « እርስዎ አያውቁኝም ይሆናል
እንጂ እኔ በዝና ዐውቅዎታለሁ » አለ በቀለ ስኳሩን
እያማሰለ ። እንደ ዋዛ ለመሆን በሞከረ መጠን እንደ ዋዛ
ለመሆን መሞከሩ ያስጨንቀዋል ።

« ይሆናል ። » ተሾመ ግን ምንም ስሜት አላሳየም ።
አያውቅም ? ወይስ እያወቀ ለመጫወት ነው ? ባያው
ቅስ ያወቀ ጊዜ ምን ይሰማው ይሆን ? ተጠንቀቅ አለው
በቀለን አእምሮው ። የአንዲት ቃል ስሕተት ነጻነትን
ሊያሳጣው ይችላል ። በአንዳችም ዐይነት አገላለጽ ተሾ
መን ካስቈጣ የሕይወት አክንባሎው ተደፋ ማለት ነው።

« አዎ ነጻነት ብዙ ጊዜ ታነሣዎታለች » አለው
ጥቂት ጊዜ በኋላ መልሶ ። ተሾመ ግን ስቅጥጥ አላለም።

ብቻ ትኩር አድርጎ ተመለከቱ ፡ የመጣው ይምጣ ቶሎ ተናግሮት ይውጣለት ! በቀለን ስሜቱ አጣደፈው ፡ « ቀለበታችሁ ጥሩ ውጤት አለመስጠቱ የሚያሳዝን ነው ፡፡ » በቀለ አንደበቱን ሊያለሰልስ ሞከረ ፡

« የምን ውጤት ? » ተሾመ አሁን ትንሽ ተነካ ፡፡

« ልትመልሱ አይደል ? » ጥያቄውን እንደ ዋዛ ጣል አደረገ ፡፡

« ማነው የሚል ? » የተሾመ ጥያቄ ጉጥሜ ጭምር ነበር ፡

« እንደምሰማው እርሷ አልተስማማችበትም ፡፡ »

« ተስማማች አልተስማማች ! » ተሾመ ወደቊጣ ተጠጋ ፡፡

« ታዲያ መቸስ ትዳር እንዲህ ብሎ አይመሠረት ፡፡ ዋናው የርሷ ፍላጎት ነው ፡፡ » በቀለ ሰውነቱ እየተረጋጋ መሄድ ጀመረለት ፡ ተሾመ በፈንታው ተቊነጠነጠ ፡

« እኔ የመጣሁት ለሌላ ጉዳይ ነበር ፡ ለዚህ ፤ የነገር አባቷ ሳይበቁ አይቀርም ፡ ስለ መልካም ምክርዎና አሳብዎ አመሰግናለሁ » ተሾመ ሊሄድ ቃጣ ፡ በቀለ ዘሎ ሊተናነቀው ምንም አልቀረ ፡ አንድ ነገር ሳይወ ሰን ከዚያ በራፍ መውጣት የለበትም ፡

« የለም ! አቶ ተሾመ ይቈዩ አይቆጡ ፡ ምናልባት በግልጥ ብንወያየው ይሻላል ፡ እኔ ከተፈጥሮዬ ግልጥ



ነኝ ፡፡ ነጻነትን የት ታውቃታለህ ይበሉኝ ፡ ቀለበት እን ድመልስ የምታማልድበት ምን ምክንያት አለህ ብለው ይጠይቁኝ ፡ እነግርዎታለሁ ፡ በጣም ዐውቃታለሁ ፡ ከርስዎ ይበልጥ ዐውቃታለሁ ፡ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚፈልገውን ቃል ልናገረው አልችልም ፡፡ » የተሾመ ፊት በርበሬ እየመሰለ ሄደ ፡ ከግንባሩ ላይ ሁለት ደም ሥሮች ግትር ብለው ወጡ ፡ የተቀመጠበትን ወን በር ድጋፍ አጥብቆ ጨበጠው ፡ አስተያየቱ የመጠራጠ ርም ፥ የመደነቅም የመጸየፍም ነበር ፡ ንዴቱ ነው ጥቃቱ ? አለ በቀለ በሆዱ ፡ « ግን በሆድዎ እንደሚያ ስቡኝ ዐይነት የማንንም እጮኛ እየዞርኩ የማበላሽ ዐይ ነት አይደለሁም እንደ ወንድም ነው የጠበኩልዎ ! »

« እንዲህ አርጎም ጥበቃ የለ ፡ ምነው ባታስቀኝ ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ » ተሾመ በምሬት ከት አለ ፡

« እርሷንም እኔንም እንደ ፈለጉ ይወንጅሉን ፡ ሕሊ ናችን ንጹሕ ነው ፡ ይህ አልቆጨኝም ፡ ግን እርሷ የርስዎ አይደለችም ፡ እርስዎም የርሷ ሊሆኑ አይች ሉም ፡ ተጋቡ ፡ ግን እንዴት ነው በኅብረት ኑሮዋችሁ የምትደሰቱት ? እኔም ሌላ ላገባ እችላለሁ ፡ ምንድነው ጥቅሙ ? ሁለታችን ለርስ በርሳችን ነው] የተፈጠርን ፡ ይህንን ቢገነዘቡልኝ »

« እንደዚህ አይደል ጠበኩልህ የምትለኝ » የተሾመ አነጋገር ከቍጣ ይልቅ ፌዝ ነበር ።

« አይ ! ፍቅር ሌላ ነገር ነው ። ሰው ወዶ አይፈቃቀርም »

« እኮ አሁን ምንድን ነው የምትለው ? » ተሾመ ርግጥ እርጎ ጠየቀ ።

« ለኔ ይተውልኝ » ። በቀለ በመጨረሻ ወጣለት ። ያበጠው ይፈንዳ ! የፍቅር አምላክ የሚባል ነገር ካለም ልቦናውን ያራራለታል ። እርሱ ባወቀ ይከሥትለት !

በቀለ የተጠባበቀው ቡጢ ኖር እንደሆን የተሾመ ሣቅ የባሰ አስደነገጠው ።

« እንዴ ! እንዴ ! አታፍርም ስትናገር ! » አሣሣቁ የዕብድ መሰለ ።

« ምኑ ነው የሚያሳፍር ? ከመስረቅ መጠየቅ ይሻላል ብዬ ነው » ግን የተሾመ አኳኋን መለዋወጥ በቀለን በአቀራረቡ ግራ አጋባው ።

« የሰረቀ ይፈረድበታል » የተሾመ የሽሙጥ አነጋገር በቀለን አናደደው ።

« አየ እኔ መቼም የሚገባኝ እንደሆነ ብዬ ነው እንጂ » በቀለ ተስፋ ወደ መቍረጡ ተቃረበ ። « እሺ » አለ በተዳከመ ድምፅ ። ተሾመ ተነሥቶ እንደሚወጣ መጠባበቁ ነበር ።



« አይምሰልህ ! » አለ ተሾመ ከተቀመጠበት እየተነ ነቀ ። « ከሥራ እንዲሁ አልቀርም ። ለዛሬ ዘመን የል ገረድ ሽርሙጣ የሚገባውን ወግ ትፈጽማለች ። ዋጋ ን ታገኛለች ። »

ጥቃቱን ! አለመወደዱን በገላዋ ሊበቀል ነው የሚ ልገው ? ገንዘቡ ነው የቈጨው ? በቀለ በአእምሮው ቂት አሰላሰለ ። ችግሩ ገንዘብ ነክ ከሆነ ተስፋ አለ ። ዚያ ጭንቅላት ውስጥ የተቋጠረውን ምስጢር ለማን ብ የሚሻ ይመስል ተሾመን በጥሞና አስተዋለው ። ጥቂት ጊዜ ያህል እንደዚሁ ተያዩ ። ምናልባት የብል ት ውድድር ነበር ።

« ብዙ ከሥረዋል ? » አጠያየቁ እንደ ተቈርቋሪ ዳጅ ነበር ።

« አዎ ! » አለ ተሾመ ሲያመነታ ።

« ምን ያህል ይሆናል »

ተሾመ ሒሳቡን እንደሚመረምር ጸጉሩን እከክ እከክ ደረገና « ባጭሩ ወደ ሁለት ሺህ ብር ገደማ ይሆናል » አለ ።

« የከሠሩት ቢመለስልዎስ ? »

ተሾመ እንቢ ሊል የቃጣ መሰለ ። ግን ጥቂት ሰበና « ምናልባት » አለ እያመነታ ። በቀለ በሆዱ ኩን ታል ተነፈሰ ። ለካ ይኸም ኖራል ?

« እኔ እከፍልዎታለሁ »

« በምን ምክንያት ? »

« በምንም ። ማለት ፣ ዘመዶቼ ከፈሉ እርስዋ ከ
ለች ወይም እኔ ለርስዎ ምን ልዩነት ያመጣል ? »

« ያንተን ገንዘብ አልፈልግም »

አየ የሀበሻ ግብዝነት አለ በቀለ በሆዱ « ይ
ቅስ በከንቱ እንጨቃጨቅ ። አሁኑኑ በቼክ ሁለት ሺ
ብር ልጻፍልዎ » የተሾመን ለስላሳ ነጥብ አግኝቶበታል
በቀለ አሸናፊነት ተሰማው ። የቼኩን ደብተር ከኪ
አወጣና ገልጦ ብዕሩን ቀሰረ ። ጥቂት ጊዜ በዝም
ተፋጠጡ ።

« መጻፌ ነው » የሚያስፈራራ መሰለ ።

ተሾመ መልስ አልሰጠም ።

ጻፈና በትንፋሹ አድርቆ «ይኸው ፤ ከአራት ቀ
በኋላ ሊመነዝሩት ይችላሉ ። » አለው ።

ተሾመ ቼኩን ተቀበለና አይቶ « እሺ ፤ ገንዘቡ
ከወሰድኩ በኋላ ሐሳቤን ብለውጥስ » ሲል ፈገግ ብ
ጠየቀው ።

« አይ አምንዎታለሁ ። ጌዋ ልጅ ስምምነት ነው
አለ ።



ከበራፉ ላይ ሲደርስ ዞር አለና « ስትገዛት ያረከስካት አይመስልህም ? » ሲል አፈዘ ።

ከሦስት ቀን በኋላ ነጻነት ደስታ እየተናነቃት ቀለበቱ መመለሱን እንደ አዲስ ነገር አበሰረችው ።

« አይደረግም ? » እንዳላወቀ ሁሉ ደነገጠ ።

« ደስ አላለህም ? » አለችና ጠየቀችው ።

« ያንን ያህል ስትለምኘው ኖረሽ ድንገት እሺ ማለቱ አስገረመኝ እንጂ » አላት ።

« እሱስ እኔንም ገርሞኛል ። ግን እንደ ሰማሁት እንዲት ልጅ ወዶ ሊያገባት ይፈልጋል አሉ » ስትለው ይበልጥ ደነገጠ ።

« ነው እንዴ ? » የዛሬ ወንድ ሞኝ የለውም ። አሞኝቼ አሸነፍኩ ሲል መበለጡ ደነቀው ። ለካስ ነገሩ ሌላ ኖሯል ። ግን ገንዘቡ አልቈጨውም ።

በቀለ አስቀድሞ የሚያዘጋጀው ነገር እስኪጠናቀቅ ድረስ እጇን መጠየቅ አልታየውም ። በልብ ፤ ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ ። ሲያርስ መፈጸም ብቻ ነው ። በመጀመሪያ ግን አንዲት ቤት መሥራት ነበረበት ። « ጨረቃን ልስ ጣት ባልችል ኪራይ ቤት ውስጥስ አላስገባትም » አለ በሐሳቡ ። እንደ ሕፃንም ለጫጉላቸው ሽርሽር ስለሚሄዱ በት ስፍራ ፣ ስለሚወልዷቸው ልጆች ብዛት ፣ ስለ ቤት ዕቃው አቀማመጥ ያልም ጀመር ። ጧት ከነፒጃማው ማድ ቤት ገብቶ የተጠበሰ ዕንቍላልና የፈላውን ወተት

በትሬ ይዞ ነጻነት ከመኝታዋ እንዳለች ሲያቁርሳት በዐይን ሕሊናው እየታየው ይሥቃል ። ይህም ፈረንጅነት ነው ። ግን ሚስቱን የሚያፈቅር ፣ ሚስቱን አክባክቦ የሚይዝ ፈረንጅ ብቻ መሆን አለበት ?

በመካከሉ ለሥራ ጉዳይ ወደ አውሮፓ የሚሄድ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

## የኦቴሎ ቁራኛ ።

በቀለ ከትምህርት ቤት ጓደኛው ከአበበ ጋራ በድንገት የተገናኘው በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ አፕሬቲቭ ጠጥቶ ከቡና ቤት ሲወጣ ነበር ። የጠጣውም ራቱን እንዲያስበላው አልነበረም ። ምሳውን የዋጠው በስንት ጭንቅ ነበር ። እህል አስጠልቶት ሰንብቷል ። የነጻነትን ገጽ ካየ አራት ቀን ሆኖት ነበር ። ሰሞኑን ሊሄድ ነው ። በዚህም ምክንያት ሰውነቱ ታውኳል ። ራቱን እንደ ማይበላ ያውቀው ነበር ። አፕሬቲቭ ያዘዘ እንዲያው ስሜቱ ቢሻለው ብሎ ነበር ።

« እንደ ምን አሉ ጌታዬ ! መኪናዎን ከዚያ ቆማ አየሁና ( ከቢሮው በራቁ ) መቼም ከዚህ አይጠፉ ብዬ ነውን » አለው በቀልድ አነጋገር እጁን እየጨበጠ ።



« አለነው » አለ በቀለ በታከተ አነጋገር ፤

« ምነው ጌታዬ? ፊትዎ ጠውልጓል ። ጤናም አይደሉ?» መቼም ጨዋታ ያውቃል « ያመመዎት ይመስላሉ ። ይህ ሐኪም የማያውቀው በሽታ ። በፍቅር መያዝ» አለ ሁለቱም ወደ መኪናው እያመሩ ።

« ደርሰው ዐወቁላቸው» አለ በሆዱ ። ምን በፍቅር መያዝ? እስከ ቁንጮው ነው እንጂ የተዘፈዘፈበት

« መቼም እንግዲህ የመንዚኑን እንከፍላለን » አለ እያሾፈ ከመኪናው ውስጥ ሲገቡ ። አስነሡና ፒያሳን ዞረው ከዚያው ቡና ቤት በራፍ አቆሙ ።

« የመንዚኑን » ሲል ጠየቀው ።

« አንተኮ መቼ ነው የሚወጣህ? ዘለዓለም በሰው ግብግብ ልትኖር ? አልበዛም እንዴ !» መኪናውን ከፍተው ሲወጡ « የራሴን ራሴ እጋብዛለሁ » አለና አበበ ተከታትለው ቡና ቤቱ ገቡ ። በቀለ አፔሬቲቭ አዘዘ ።

« ቢሬታ ኖ ኖ ኖ ቀይ ቢሬታ ስንት ነው ? ሥልሳ አምስት ሳንቲም ? የለም ! አፕሬቲቭ !» ሲጨርሱ « በል እንግዲህ » ሲል አግባባውና ሃምሳ ብር ሲመነዝር ራሱን ይዞ ጮኸ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን አበበ በእጁ አንድ ወረቀት ይዞ ነበር ። አንድ የውጭ አገር የሙዚቃ ባንድ መምጣቱን የሚያውጅ ማስታወቂያ ነው ።

« አንተ መቼም ቀደም ብለህ አይተኸዋል » አለ ወረቀቱን እያገላበጠ « ራስ ሆቴል ጋብዟቸዋል ። በዚያም ቀን እኔ እርስዎን ጋብዤዎታለሁ ። ከሁለት ልጃ ገረድ ጋራ » ።

« ከመጠጡ ጋራ ? » ሲል በቀለ ጠየቀ ።

« መግቢያውም ሁሉም ። ሦስት ራስዎን የመጡ እንደሁ » አለ ።

« ፍቅረኛየን ብቻ ይዤ ብመጣስ ? »

« እያ እርሱ የራስህ ጉዳይ ነው ። መግቢያውንም ትከፍላለህ » አለ ።

ከዚያም ወደ ቤቱ አቅጣጫ ሲነዱ ስለ ሴቶች ጨዋታ ተጀመረ ።

« ዋና አሳሳች ነህ ። እንዲያው መንፈሳዊ ትመስላለህ ። ግን ስንቱን ልጃ ገረድ ነው በመኪናህ የምትጭነው ? » አለ አበበ ።

« መንፈ/.ዊ አይደለሁም ። ግን ሞራሊስት ነኝ ። ታምናለህ ? እንዳቸውንም አልነካኋቸውም » ብሎ መለሰለት ።

« ርግጥ ርግጥ የፕሪንስፕል ሰው ነዎት » ሲል አሾፈና አንዲት አስደሳች ልጅ መኖሯን ከነመሥሪያ ቤቷ አመለከተው ።



« ተወኝ ! መብራቱ አይጥፋ ነው የምትል አሉ » አለ እያዳነቀ ።

« ታዲያ እርስዎስ ? » በቀለ በፈዝ ጠየቀ ።

« አንድ ጓደኛዬ ስለ ነካት ነው ። እኔ ወንድምህ ደግሞ በእንደዚህ ያለው ነገር በጣም ሞራሊስት ነኝ» አለ ።

« እንግዲያው እኔም ፍቅረኛዬን ባስረክብዎት ይታመናሏ » ሲል በቀለ እንደ ዋዛ ጠየቀው ።

« እስከዚህ ድረስ ? ምንስ ቢሆን አብረን አድገን» አበበ ራሱን ነቀነቀ ። በቀለ ስለነጻነት አጫወተው ።

በቀለ የግል ኑሮውን ለማንም ማውራት ከተፈሮው አይወድም ነበር ። የፍቅሩን ምስጢር ለእናቱ ልጅ እንኳ አላጫወተውም ። በዚያን ምሽት ግን የሰሞኑ ናፍቆት ስሜቱን ነፍቶትም ይሁን አፕሬቲቩ ገፋፍቶት ፉአበበ ሲተርክለት ቤቱን አልፈው ወደ ነጻነት ቤት አቅጣጫ አመሩ ። ሳይታወቀው ነው ። እየታወቀውም ነው ። አሁንም የርሷን ቤት ሰፈር አልፈው ሾላ ደርሰው ሲመለሱ ከፊታቸው ላይ ማን ድቅን ይላል ! እርሷ ፤ አንድ ተማሪ ቢጤና አንድ ጉልማሳ በጉንና ጉኗ ሆነው ወደ ሾላ አቅጣጫ ይወጣሉ ።

«ያቻትልህ !» አለው በተወጠረ አንደበት ። ግን ፍጥነቱን ሳይቀንስ መቶ ሜትር ያህል ነድቶ አዞሮ ቢመ

ለስ የውሃ ሽታ ሆኑ ። መኪናውን አቁመው በአቅራቢው ባሕር ዛፍ ውስጥ ሁሉ ፈለጉ ። ምንም ።

« ተደብቃ ነው » አለ ። በእርግጥም የሚያሰኝ ነበር። በአቅራቢያው አንድ ቪላ ብቻ ነበር ። ከዚያም ገብታ ለች እንዳይል የምታወቀው ቤት አለመሆኑን ያውቅ ነበር ። ብዙ አሰበ ። አጎቷ ከውጭ አገር መጥተው ሰን ብተው ነበር ። ከዘመድ ቤት ተጠርተው ከርሳቸው ጋር ለማምሸት ይሆን ? አንዱ ወንድ አሽከራቸው መስሎ ታል ። እኮ ታዲያ እንዴት በድንገት ተሠወረች ? በዚያ ውድቅት ጨለማ በዚያ የሾላ ባሕር ዛፍ ውስጥ በዶም እንደ ሰከረ አውሬ ወዲያና ወዲህ ሲንከራወት አደጋ እንዳይደርስበት አበበ ክንዱን ይዞ አወጣውና መኪናዋን ከባሕር ዛፍ ሥር አቁመው ይጠባበቁ ጀመር ።

« ይገባኛል ! እኔም ደርሶብኝ ነበር » አለ አበበ ባዘ ኔታ ። ሁለቱም ሲጋራ አቀጣጥለው ያጨሳሉ ።

ሲጋራውን በሲጋራ ለኩሰው ። « በጣም ቆንጆ አይ ደለችም ። ግን ንጹሕ ናት ። ፍጹም ናት ። ፍጹምነቷም ——» ንግግሩን እንጠጥልጥሎ ተወው ።

« በቀለ በጣም የዋህ አትሁን በሰው ዘንድ ፍጹም ነት የለም ። ታዲያ ፍጹም የመሰለችው የመጨረሻዋ



አሰለጥ ልትሆን ትችላለች» አለ አበበ አሁንም በአዘ ኔታ እነጋገር ።

« እህና እሱ ኮ ነው እኔም የከነከነኝ » በቀለ በሕ ልም ውስጥ የሚነጋገር መሰለ ።

ከአንድ ሰዓት ተኩል እንሥቶ እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ጠበቁ ። አልተመለሱም ። አንድ ፓኬት - ባለድ ሞት ጨርሶ ሌላ ገዝቶ መጣ ።

«አሁን ብንሄድ ይሻላል ። ተደብቃ ከሆነ አናገ ኛትም ። ግን ኮ ያጠፋህ አንተነህ በቀለ ። ወዲያው አቁ መህ እኔን ብታወርደኝ ኖሮ » ኖሮ ! ኖሮ ! በእርግጥም ደደብነቱ አናደደው ። ግን በዚያን ጊዜ በመኪናው መብ ራት ገጥታዋን ሲያይ ሌላ ማሰብ አልቻለም ነበር ።

« ትቸኩላለህ እንዴ » ብሎ ጠየቀው ።

« አየ እኔስ ቤቴ ነው የምገባው ። ግን ሌላ ቀንም ልናረጋግጥ እንችላለን» ።

« እስቲ ትንሽ እንቁይ» በቀለ ሞተሩን አስነሥቶ መልሶ አጠፋው ።

« እኔም እንዳንተው ነኝ ። አንድን ነገር ወዲያው ካላረጋገጥኩት አላርፍም» አለ አበበ ።

« እኮ አሁኑኑ ለመቍረጥ እፈልጋለሁ ። ቀስ በቀስ ዘወትር ከምሞት አንዴ ብሞት ይሻለኛል» ከንፈሩን

ይበላው ጀመር ። ስለ ጋብቻ ካሰበ ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይህ መድረሱ ይበልጥ አናደደው ።

« ደግሞ ኮ ከአሁን በፊት ቀለበት መልሳለች » አለ እንደ ተጸጸተ ያህል ።

« እሱን ፍራልኝ » ሲል አበበ አባባሰው ።

እስከ አራት ሰዓት ከጠበቁ በኋላ የጓደኛውን መቍነጥነጥ ተመልክቶ « አንተን ላድርስህና እኔ ተመልሼ እመጣለሁ» አለ በቀለ ።

« ዐብደሃል ? »

« ቤት ገብቼ እጠይቃለሁ »

« ከቤቷ ጋራ ከተዋወቅህስ ደኅና » አለና አበበ ወረደ ። ርግጥ ወንድሞቿን ያውቃቸዋል ። ያውቁታል ። ግን በደንበኛው አልተዋወቀም ። ሐሳቡ በሚቀጥለው ወር ሽማግሌ ለመላክ ነበር ። እንደ ዋሸለትም ቤት አልሄደም ። ከዚያው የባሕር ዛፍ ሥር እስከ አምስት ሰዓት ሲጠብቅ አምሽቶ በመንገዱ ዐሥር ጊዜ ያህል ተመላልሶ እግረ መንገዱን ሁለት አፕሬቲቭ ጠጥቶ ከክፍሉ ገባ ።

ከተፈጥሮው ደኅና እንቅልፍ ነበረው ። አንዴ ከተጋደመ ሌባ ቢሰርቀው ስንኳ አይሰማም ። የዚያን ሌሊት ግን ዐይኑ አልከደን አለ ። ከንክሩማህ መጽሐፍ መቶ ኀምሳ ገጽ ያህል አንብቦ አደረ ። ግን ካነበበው



የሚያስታውሰው ትልቅ ዓላማና ተግባር ያለው ወንድ በሴት ወጥመድ ውስጥ መግባት የለበትም የሚለውን ክፍል ብቻ ነው ። እውነት ሊሆን ይችላል ። ግን ሴትም ኮ ትልቅ ዓላማ ትሆናለች ። የርሱ ዓላማ እርሷ ነበረች ። ሙዚቃ -- ድርሰት --ሥዕል የሚገለጥለት የርስዋን ፈገግታ ሲያይ ብቻ ነበር ።

በበነጋው ጧት በአንድ ሰዓት ተነሥቶ ከተማውን በመኪና ሲያዳርስ አረፈደና በሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ቢሮ ገባ ። እስከ አምስት በቡናና በሲጋራ ዋለ ። ደወለላት ።

« አሎ!» ድምፁዋ የተለወጠ መሰለው።ጀሮው ነው ?

« ምነው ጤናም አይደለሽ ? »

« ደህና ነኝ »

« እህ ! »

« እህ ! »

« እኔስ ምግብም አልተበላልኝ ። ብታይኝ ከስቻለሁ » ሊጠይቃት ያሰበው ሁሉ ቀረ ።

« ወትሮማ ወፍራሙ » ስትል ሣቀች ።

« ዛሬም ፊትሽን አላየው »

« አይመስለኝም »

« ውይ እንዴት ነው የናፈቅሽኝ ! »

« ኤሾ ! »

« በያ ሣቂ ምናለበት »

« እሺ ! »

« ታዲያስ እንገናኛለን ? »

« እንጃ » ይህም ተስፋ ነው ። ምናልባት ።

« ኧረ እስቲ » አለ ለዘብ ባለ አነጋገር »

« ትናንት ማታ በሾላ በእግርሽ ስትኳትኝ ያየሁሽ መሰለኝ ። ሁለት ጐረምሶች አብረው ነበሩ » ።

« እኔስ እንደ ሄድኩ ከቤት አልወጣሁም » አለች ።

« አይቾሻለሁ ኧረ ! »

« የለም »

« ሙት ? »

« ተድላ ይሙት ! ምን አስዋሸኝ » ቈጣ አለችበት ።

« እንግዲያው ዐይኔ ነው » ብሎ አቆላመጣት ።

« አኬ ! » ተባብለው ዘጋቹ ።

ማን ይታመናል ? ዐይኑን ይመነው ወይስ የርሱዋን ቃል ? ጸጕሯን ፡ ዐይኗን ፡ አፍንጫዋን ፡ ያን ሹሩባ በገሃድ ዐይኑ አይቶት ነበር ። ርግጠኛ ነው ። ካለበ ለዚያ ዐይኑ የሌለ ምትሐት ይመለከታል ማለት ነው። ጤናማም አይደለም ማለት ነው ። አማኑኤል መመርመር ሳያስፈልገው ይቀራል ? ለጓደኛው ደወለና ታሪኩን አጫወተው ።



« እርስዋ ለመሆኗ ርግጠኛ ከሆንክ ዋሽታለች ማለት ነው ። ከዋሸችም ሸፍጣሃለች ማለት ነው » አለው ።

« እኮ ማረጋገጥ አለብኝ »

« መከታተል ተዋ ! » ሲል መከረው ።

ቀጥሎ ለእታገኝ አማከራት ። በሕይወቱ ሙሉ እንደዚያን ቀን ግራ ገብቶት አያውቅም ። አእምሮው ተዘበራረቀበት ። አንድ ሰው ከፊቱ ላይ አንድ ነገር ተደቅኖ ቢያይ ፤ ያ ነገር የለም ሲባል በርግጥ የአእምሮ ጤነኝነት አይሰማውም ። የተሳሳተ ነገር አለ ።

« በቀለ » አለች እታገኝ አንገቷን ደፋ አድርጋ ፤ « አንተ መልአክ ለመሆን ብትሞክር ፤ ለመሆን ደግሞ አትችልም - ሌላው ሁሉ መልአክ እንዲሆን አትተማመን ፤ በኋላ በጣም ትሳቀቃለህ » ።

« ምን ማለትሽ ነው ። እርሷ ናት ነው የምትይው ? ቊጣውን በርስዋ ላይ ሊወጣ ከጀለ ። ሰው የለም ማለት ነው ? እስከዚህ ዝቅ ብለናል እንዴ ? ለምን ተስፋው እንዲነጥፍ ያደርጋሉ ?

« አልወጣኝም ። ግን ልትሆንም ላትሆንም ትችላለች ። ጕዳዩን በጠቅላላ በሰው ልጅ ደካማነት ተፈጥሮ መገመት አለብህ » ። የማጽናኛ ገጥታ ልታሳየው ሞከረች ።

« ልትሆን ትችላለች ላትሆንም ትችላለች ። ይህማ ያሻማል- እታገኝ ፡ »በቀለ ራሱን ነቀነቀ ።

እንደወጣች ለአበበ እንደገና ደወለና « በላ ጓደኝ ነትህን እንየው ። ድቲክቲቨ እንብቤአለሁ ትላለህ» ብሎ በጉን እንዲያጣራለት ተመካጠሩ ።

ማምሻውን በቀጠሮ ከዚያው ቡና ቤት ተገናኙ ፕላን አወጡ ። አበበ በአፈጻጸሙ እምብዛም የሚቸገር አልመሰለም ።

በቀለ ሊሄድ ዋዜማ ፤ ከነጻነት ጋራ ከመኪና ውስጥ ሆነው ቡና እየጠጡ የሚያመጣላትን ዕቃ ሲያማርጡ « ወር ? ወር ሙሉስ ረዘመ በቅዬ » አለችው ።

« አሁን ይህችን በመሰለች ንጽሕት ፍጥረት ላይ ምን አሰብኩ እባካችሁ ? የመጨረሻው እስቀያሚ ጭራቅ ነኝ » በቀለ ክፉኛ ተጸጸተ ። የጭንቅላቱን ቆሻሻነት ተጸየፈው ። የአቴሎ ቍራኛ ። ሲሰንባበቱ በዐይኗ ዕንባ ችፍፍ አለባት ። በመሐረሟ እያመጠጠች ፤ « በል ደኅና ሁን ልቅበጥ ደግሞ እንዳትል ። እይዞህ ለየሱስዬ ደግሞ እጸልይልሃለሁ » አለችው ። መመርመር ቀርቶ በሄደችበት ዝር እንዳይል ለማስጠንቀቅ ማታ አበበን ቢፈልገው አጣውና ጧቱን በረረ ።